MARYLAND

የአሽከርካሪዎች መመሪያ

MDOT MARYLAND DEPARTMENT OF TRANSPORTATION

MOTOR VEHICLE ADMINISTRATION



ለበለጠ መረጃ፤ ወደ ሚከተለው ይሂዱ፡
mva.maryland.gov

6601 Ritchie Highway N.E.
Glen Burnie, MD 21062

410-768-7000
የመስማት ችግር ላለባቸው ሰዎች TTY፤ 1-800-492-4575

MarylandMVA

MD_MVA

October 2025 Edition

የቅጂ መብት

© የሜሪላንድ የሞተር ተሽከርካሪ አስተዳደር፣ 2025

ሁሉም መብቶች የተጠበቁ ናቸው።

የሜሪላንድ የትራንስፖርት መምሪያ፣ የሞተር ተሽከርካሪ አስተዳደር (MDOT/MVA) የዚህ ስራ የቅጂ መብት ባለቤት ነው። ከ MDOT/MVA ግልጽ የጽሁፍ ፍቃድ ከሌለ የዚህ መጽሐፍ ክፍል በማንኛውም መልኩ፣ በኤሌክትሮኒክስ ወይም በሜካኒካል፣ ፎቶ ኮፒ ማድረግ፣ ድምጽን መቅዳት፣ ወይም በማንኛውም የመረጃ ማከማቻ እና ማግኛ ስርዓት ማባዛት ወይም ማስተላለፍ አይፈቀድም።

ሁሉም ይዘቶች በነጻ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ እና ለሜሪላንድ ተሽከርካሪ ህግ ጥናት የታሰቡ ናቸው። የዚህን ቁስ ማንኛውም ያለፍቃድ የሚደረግ ደግሞ ማተም፣ መጠቀም፣ ማሰራጨት ወይም መሸጥ የተከለከለ ነው።

እባክዎን የዚህን ማኑዋል ቅጂ ስለማዘጋጀት ወይም ስለማሰራጨት ማንኛውንም ጥያቄዎች ካሉ ለሚከተለው ያቅርቡ፡- MVA አስተዳዳሪ፣ 6601 Ritchie Highway N.E.፣ Glen Burnie, MD 21062።

DL-002 (10_25)

የአስተዳዳሪ መልእክት

ውድ የወደፊት አሽከርካሪ:

የ Maryland መንጃ ፍቃድ ለማግኘት እርምጃዎችን ሊወስዱ ነው። ይህ ለማንኛውም አዲስ አሽከርካሪ አስደሳች ጊዜ ነውነው! ማሽከርከር ልዩ መብት መሆኑን ማስታወስ ጠቃሚ ነው፤ እናም ሁሉም ሰው በመንገዳችን ላይ ደህንነቱ እንዲጠበቅ በማድረግ ረገድ እርስዎ ሚና ይጫወታሉ። መታወቅ ያለባቸው ብዙጠቃሚ ነገሮች አሉ – ይህ መመሪያ የእርስዎ መመሪያ ነው።

ህይወትን የሚያድን አሽከርካሪ ይሁኑ

በ Maryland መንገዶች ሲጓዙ፤ በተለያየ ዕድሜ ላይ ያሉ እና የተለያየ የክህሎት ደረጃ ያላቸው አሽከርካሪዎች ያገኛሉ። ግን ሁላችንም አንድ የሚያመሳስለን ነገር አለን፡– ህይወትን የሚያድን አሽከርካሪ የመሆን ሀላፊነት። ይህም ማለት የእራስዎን እና የሌሎችን የመንገድ ላይ ደህንነት መጠበቅ ማለት ነው።

እንደ አዲስ አሽከርካሪ የሚከተሉትን ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው፡–

- ጊዜ ይውሰዱ።
- የመንገድ ደንቦችን ይረዱ።
- ያዳምጡ እናም ከአስተማሪዎችዎ እና አሰልጣኞቾ ይማሩ።
- ሌሎች አሽከርካሪዎችን እና ተሳፋሪዎችን በአክብሮት ይያዙ።

ልክ እንደሌሎች አዳዲስ የምትማሯቸው ችሎታዎች፤ በተለያዩ መንገዶች፣ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ እና በተለያዩ አከባቢዎች ውስጥ በይበልጥ በመለማመድ፤ በማሽከርከር የተሻሉ ይሆናሉ። ለምሳሌ፤ በመጥፎ የአየር ሁኔታ፣ በከባድ ትራፊክ እና በቀን በተለያየ ጊዜ ማሽከርከር።

እያንዳንዳችን ከመሪ በስተጀርባ በሆንን ቁጥር ያለብን ሃላፊነት፡–

- አልኮሆል ሳይጠጡ ያሽከርክሩ።
- ያስተውሉ።
- የመቀመጫ ቀበቶ ይሰሩ።
- የፍጥነት ወሰኖችን ይከተሉ።
- ሞተር ብስክሌቶች መኖራቸውን ሁለት ጊዜ ይቃኙ።
- መንገዱን ለእግረኞች (የሚራመዱ ሰዎች) እና ብስክሌት ነጂዎች ያጋሩ።

ከመሪ ጀርባ አስተማማኝ ምርጫዎችን ማድረግ የእርስዎ ውሳኔ ነው፡፡ እንደ አለመታደል ሆኖ፤ በየቀኑ በሺዎች የሚቆጠሩ አሽከርካሪዎች ትኩረታቸውን በመከፋፈል ወይም በማዳከም፣ በመፍጠን ወይም በመንገድ ላይ ካሉ ሌሎች ሰዎች ጋር ጠብ በመጫር ለማሽከርከር ይወስናሉ። ይህ እራሳቸውን እና ሌሎችን አደጋ ላይ ይጥላል። ሁላችንም እርስ በርሳችን መተያየት አለብን።

የ Maryland የትራንስፖርት ሞተር ተሽከርካሪ መምሪያ (MVA) ለአሽከርካሪ ደህንነት ቁርጠኛ ነው። ግባችን በ Maryland መንገዶች ላይ ዜሮ አደጋ (ምንም ሞት) ላይ መድረስ ነው፤ ምክንያቱም የአንድ ህይወት መጥፋት እንኳን በጣም ብዙ ነው።

ይህንን መመሪያ ካነበቡ በኋላ፤ የእኛን የበይነ መረብ የአሽከርካሪዎች ፈተናን በመውሰድ ስለ መንገድ ህጎች ያለዎትን ግንዛቤ ይፈትሹ። በ MVA ድህረ ገጽ mva.maryland.gov/drivers ላይ ይገኛል።

እርስዎን ለማገልገል በጉጉት እንጠባበቃለን።

ደህንነትዎን ይጠብቁ፤

Administrator, MDOT MVA

የማውጫ ሰንጠረዥ

ክፍል 1: የማሽከርከር ፈተናዎች መስፈርቶች 7

1. የእይታ ምርመራ 7
2. የእውቀት ፈተና 7
3. የማሽከርከር ችሎታ ፈተና 7
4. ሪፖርት ሊደረጉ የሚችሉ የሕክምና ሁኔታዎች 8

ክፍል 2: የፍቃድ መስፈርቶች እና ሂደት 9

1. ጀማሪ አሽከርካሪ/ተመራቂ የፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት .9
2. የተማሪ የትምህርት ፍቃድ 9
3. ጊዜያዊ ፈቃድ 10
4. የመንጃ ፍቃድ 10
5. ለአካለ መጠን ላልደረሰ ሰው ለፈቃድ ማመልከቻ ተባባሪ ፈራሚ 10
6. ለአካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ፈቃድ የጋራ ፈራሚ ስረዛ 11
7. ከአገር ውጪ ፍቃዶች 11
8. ለሁሉም ደንበኞች ትክክለኛነት 11

ክፍል 3: መሰረታዊ ማሽከርከር 13

1. በመከላከል ያሽከርክሩ 13
2. የመንገድ ቅድሚያ መብት 13
3. የተሽከርካሪ ፍጥነትን መረዳት 14
4. የመከተያ ርቀት 14
5. የማቆሚያ ርቀት 15
6. በመስመር ማሽከርከር 15
7. መዞር 15
8. U-turn 15
9. ማለፍ 15
10. አጠቃላይ የመኪና ማቆሚያ ደንቦች 16

ክፍል 4፡ ምልክቶች፣ ማስተላለፊያዎች እና የእግረኛ መንገድ ምልክቶች 17

1. የትራፊክ ምልክቶች 17
   - የተሽከርካሪ ምልክቶች 18
   - የእግረኛ መሻገሪያ ምልክቶች 19
2. የትራፊክ ምልክቶች 20
   - ቀለሞች & ቅርጾች 20
   - የቁጥጥር ምልክቶች 21
   - የማስጠንቀቂያ ምልክቶች 22
   - ሌሎች የትራፊክ ምልክት ዓይነቶች 23
4. የእግረኛ መንገድ ምልክቶች 24
   - የመስመር ምልክቶች ዓይነቶች 24
   - ሌሎች የእግረኛ መንገድ ምልክቶች 25
   - የእግረኛ እና የብስክሌት መንገድ ምልክት ማድረጊያዎች 25

ክፍል 5፡ የማሽከርከር ሁኔታዎች 27

1. በዝቅተኛ እይታ ማሽከርከር 27
2. በሌሊት ማሽከርከር 27
3. ጭጋግ ውስጥ ማሽከርከር 28
4. በመጥፎ የአየር ሁኔታ ውስጥ ማሽከርከር 28
5. መንሸራተት 29
6. ሃይድሮፕላኒንግ (Hydroplaning) 29
7. የአውራ ጎዳና-ባቡር መንገድ ማቋረጫዎች 29
8. የስራ ቀጠና ደህንነት 30
9. የትራፊክ ክበቦች (አደባባዮች) 30
10. በግዛት መካከል መንዳት እና ውስን ተደራሽ አውራ ጎዳናዎች 31
11. የቀብር ስነ-ስርዓት 31
12. ቀስ ብለው የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች 31

ክፍል 6፣ አደገኛ የመንዳት ባህሪያት 33

1. አልኮሆል፣ አደንዛዥ ዕፅ እና ማሽከርከር....................33
2. በምገደኝነት ማሽከርከር እና የመንገድ ቁጣ 33
3. በመዘናጋት ማሽከርከር 34
4. በድብታ መንዳት 34

ክፍል 7፣ መንገዱን መጋራት 37

1. ለእግረኛ የመንገድ ቅድሚያ መስጠት 37
2. የአደጋ ጊዜ ተሽከርካሪዎች 37
3. ትላልቅ መኪናዎች እና አውቶቡሶች 37
4. የትምህርት ቤት አውቶቡሶች 38
5. ሞተር ሳይክሎች...39
6. ብስክሌቶች...39
7. Mopeds እና Scooters ተሽከርካሪዎች..................41
8. የተሽከርካሪ ቴክኖሎጂዎችን መረዳት........................41

ክፍል 8፣ መጋጨቶች እና የትራፊክ ማቆሚያዎች. . 43

1. መጋጨቶች..43
2. የመንገድ ዳር ድንገተኛ አደጋዎች 44
3. የትራፊክ ማቆሚያዎች...44
4. የመሻገር ህግ...45

ክፍል 9፣ ሌሎች ገደቦች፣ ጥሰቶች እና ቅጣቶች . . . 47

1. ገደቦች..47
2. የመድሃኒት ወይም የአልኮሆል ምርመራ - አስገዳጅ ስምምነት 47
3. የሐሰት ወይም የተጭበረበረ መታወቂያ ካርድ፣ የመንጃ ፍቃድ ወይም የተማሪ መማሪያ ፍቃድ ማግኘት...........47
4. አስተዳደራዊ እርምጃዎች...48
5. ቅጣቶች...48
6. የአካል ጉዳተኞች የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን፣ የፍቃድ ሰሌዳዎችን እና የማሳወቂያ ካርዶች አጠቃቀም..........49

ክፍል 10፡ ሌላ ጠቃሚ መረጃ 51

1. ለ MVA ሪፖርት ለማድረግ የሕክምና ሁኔታዎች..........51
2. ተቆጣጣሪ ሹፌር - መስፈርቶች እና ኃላፊነቶች 51
3. የአካል ክፍሎች ለጋሽ..51
4. ድምጽ ለመስጠት ይመዝገቡ 51
5. የኢንሹራንስ መስፈርቶች...52
6. የመቀመጫ ቀበቶ ህግ...52
7. የልጆች ደህንነት መቀመጫዎች 52
8. የአየር ቦርሳዎች...52
9. ፍሬን በፀረ- መቆለፊያ የፍሬን ሲስተም (Braking with Anti-lock Braking System) (ABS)............52
10. የጆሮ ማዳመጫዎችን ማድረግ የተከለከለ ነው..............52
11. ትይዩ የመኪና ማቆሚያ..52
12. ወደፊት የሚያስገባ የመኪና ማቆሚያ፣ ወደ ኋላ የሚያስገባ የመኪና ማቆሚያ እና ባለ ሶስት ነጥብ መታጠፊያ 53
13. የብስክሌት ነጂዎች ህጎች እና ምክሮች 53
14. ዝቅተኛ ፍጥነት ያላቸው የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች (ፍቺዎች) 54

በ Maryland ውስጥ ህይወትን ከሚያድኑ አሽከርካሪዎች ጋር ይገናኙ።

ህይወትን የሚያድን አሽከርካሪ ይሁኑ

በመመሪያው ውስጥ፤ የኛ “አሽከርካሪ ይሁኑ” የሚሉ ደስ የሚያሰኙ ሰዎች፤ ስለ Maryland ደህንነቱ የተጠበቀ የማሽከርከር ዘመቻዎች ይነግሩዎታል፤ እና ጠቃሚ የደህንነት ምክሮችን ይሰጣሉ! ስለ “አሽከርካሪ ይሁኑ” ዘመቻ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፤ የሚከተለውን ይጎብኙ፥
ZeroDeathsMD.gov.

ክፍል 1: የማሽከርከር ፈተናዎች መስፈርቶች

ሞተር ተሽከርካሪ ከመንዳትዎ በፊት የመንጃ ፍቃድ ማግኘት አለብዎት። መኪኖች፣ ቫኖች እና የጭነት መኪናዎች የሞተር ተሽከርካሪዎች ምሳሌዎች ናቸው። መንጃ ፍቃድ ለማግኘት አንዳንድ ፈተናዎችን መውሰድ እና ማለፍ አለቦት። እነዚህ ፈተናዎች የፈቃድ መስፈርቶች ተብለው ይጠራሉ። የፈቃድ መስፈርቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፥

- የእይታ ምርመራ።
- የእውቀት ፈተና።
- የማሽከርከር ችሎታ ፈተና።

አንዳንድ ሰዎች ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ማሽከርከር እንደሚችሉ ለማሳየት ሌሎች መስፈርቶችን ሊያሟሉ ይችላሉ። የ Maryland የትራንስፖርት ሞተር ተሽከርካሪ መምሪያ (MVA) ሌሎች መስፈርቶችን ማሟላት ካለቦት ያሳውቀታል።

1. የእይታ ምርመራ

የእይታ ማጣሪያ ምን ያህል ማየት እንደሚችሉ ይፈትሻል። MVA ወይም የአይን ሐኪምዎ የማጣሪያ ምርመራ ማድረግ ይችላሉ።

ለመንጃ ፍቃድ ብቁ ለመሆን ሊኖርዎት የሚገባው፥

- የሁለትዮሽ እይታ::
- በእያንዳንዱ አይን ውስጥ ቢያንስ 20/40 የእይታ ጥራት::
- ቢያንስ 140 ዲግሪ ቀጣይነት ያለው የእይታ መስክ።

MVA ወይም የአይን ሐኪምዎ ይህ ምን ማለት እንደሆነ ማብራራት ይችላሉ። እነዚህን መስፈርቶች ካሟሉ ሊነግሩዎት ይችላሉ።

እነዚህን መስፈርቶች ለማሟላት መነጽር ወይም የመገናኛ ሌንሶች ካስፈለጎት፤ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ሁል ጊዜ መልበስ አለብዎት። ፈቃዶት እንዲህ ይላል።

የእይታ መስፈርቶችን ለማያሟሉ ሰዎች በ MVA ድህረ ገጽ ላይ ተጨማሪ መረጃ አለ።

2. የእውቀት ፈተና

የእውቀት ፈተናው ስለሚከተሉት የሚያውቁትን ለማየት ይፈትሻል፥

- የሞተር ተሽከርካሪ ህጎች::
- ደህንነቱ የተጠበቀ የማሽከርከር ልምዶች።
- የትራፊክ ምልክቶች::

ይህ መመሪያ የሚፈተኑበትን መረጃ ሁሉ ያካትታል። የእውቀት ፈተናውን የሚወስዱት በ MVA ቦታ ነው። በፈተናው ላይ 25 ጥያቄዎች አሉ። ፈተናውን ለመውሰድ 20 ደቂቃ ይኖርዎታል። ልዩ መስተንግዶዎች ካስፈለጎት ክፍል 2.Aን ይመልከቱ።

በ MVA ድህረ ገጽ ላይ የበይነ መረብ የአሽከርካሪዎች ፈተና አጋዥ ስልጠና አለ። መማሪያው ለእውቀት ፈተና ለመዘጋጀት የሚያግዙ የተግባር ጥያቄዎች አሉት። **እንዲሁም የእውቀት ፈተናውን ለማለፍ እንዲረዳዎ በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም መረጃዎች ማጥናት አለብዎት።**

3. የማሽከርከር ችሎታ ፈተና

የማሽከርከር ፈተናው በደህና እና በኃላፊነት የማሽከርከር ክህሎት እንዳለዎት ለማረጋገጥ MVA የሚፈትሽበት መንገድ ነው። ፈተናው በህዝብ መንገዶች ላይ ማሽከርከርን እና በፈተና ቦታ ላይ የሚሰጥ ልዩ ኮርስን ያካትታል።

የአሽከርካሪውን የክህሎት ፈተና ለመውሰድ ቀጠሮ ማስያዝ አለቦት። ቀጠሮ ለማስያዝ፣ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፥

- mva.maryland.gov ን ይጎብኙ እና “ቀጠሮ ያስይዙ” የሚለውን ይጫኑ ወይም
- በ 410-768-7000 ወይም 1-800-492-4575 (TTY መስማት ለተሳናቸው እና መስማት ለሚቸግራቸው) ይደውሉ።

ለፈተናው ያመጡትን ተሽከርካሪ ተጠቅመው የማሽከርከር ችሎታ ፈተናውን ይወስዳሉ። ለፈተና እንዲጠቀሙበት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፥

- ተሽከርካሪው ወቅታዊ ታርጋ እና ምዝገባ ሊኖረው ይገባል።
- ተሽከርካሪው መድን እንዳለው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሊኖርዎት ይገባል።

ተሽከርካሪው የሚከተሉትን መሆን አለበት

- ለማሽከርከር ደህንነቱ የተጠበቀ።
- የማየት ችሎታዎ ላይ ተጽእኖ ሊያደርጉ የሚችሉ ስንጥቆች ወይም ሌሎች ነገሮች በፊት መስታወት ላይ አይኑሩ።
- ቢያንስ ግማሽ ጋን ነዳጅ ይኑርዎት።

“ተቆጣጣሪ አሽከርካሪ” ወደ ፈተና ቦታው አብሮት መምጣት አለበት። የዚህ መመሪያ ክፍል 10 ተቆጣጣሪ አሽከርካሪዎች እነማን እንደሆኑ ይገልፃል። በፈተናው ወቅት በተሽከርካሪው ውስጥ የሚፈቀደው እርስዎ እና ምርመራውን የሚሰጥዎት ሰው ብቻ ነው። MVA ያጸደቀው አስተርጓሚ ካስፈለገት መኪናው ውስጥ ሊኖር ይችላል።

የእርስዎን እና የ MVA ሰራተኞችን ጤና እና ደህንነታቸውን ለመጠበቅ እንዲረዳዎት፥

- በፈተናው ወቅት አየር በተሽከርካሪው ውስጥ እንዲነፍስ እናበረታታዎታለን። ለምሳሌ፤ መስኮቶችን በመክፈት። ፈተናውን የሚሰጡት ሰው ሌሎች ነገሮችን ሊጠቁሞት ይችላል።
- ከፈለጉ በፈተና ወቅት ጭምብል ማድረግ ይችላሉ።
- ጥሩ ስሜት ካልተሰማዎት ቀጠሮዎን ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ አለብዎት።

4. ሪፖርት ሊደረጉ የሚችሉ የሕክምና ሁኔታዎች

የማሽከርከር ችሎታዎን ሊጎዳ የሚችል የጤና እክል ካለብዎት ለ MVA ማሳወቅ አለቦት። የግዛት ህግ ይህንን ይጠይቃል። ሪፖርት ማድረግ ያለብዎትን የሕክምና ሁኔታዎች ዝርዝር እና መቼ ሪፖርት እንደሚያደርጉ ክፍል 10ን ይመልከቱ።

የሀይዌይ ሰራተኞች በየአመቱ ከሁለት ሚሊዮን ፓውንድ በላይ ቆሻሻ ከመንግስት መንገዶች እንደሚያስወግዱ ያውቃሉ? ቆሻሻ የመጣል ቅጣቶች እስከ 1500 ዶላር ወይም ለ30 ቀናት እስራት ሊደርስ ይችላል።

ክፍል 2: የፍቃድ መስፈርቶች እና ሂደት

ይህ ክፍል የ Maryland መንጃ ፍቃድ ለማግኘት ምን ማድረግ እንዳለቦት ያብራራል። መረጃው “የንግድ ያልሆነ መንጃ ፍቃድ” ለሚፈልጉ ሰዎች ነው። የንግድ ያልሆነ የመንጃ ፍቃድ እንደ መኪኖች፣ ፒክአፕ መኪናዎች እና ቫኖች ያሉ መደበኛ ተሽከርካሪዎችን እንዲያሽከረክሩ ይፈቅድልዎታል። የ ክላስ C መንጃ ፍቃድ ተብሎም ይጠራል።

ሂደቱን ለመጀመር: ማንኛውንም MVA የሙሉ አገልግሎት ቢሮ ለመጎብኘት ቀጠሮ መያዝ አለቦት። ማመልከቻ በሚያስገቡበት ጊዜ:- ይዘው መምጣት አለብዎት:-

ዕድሜዎን የሚያረጋግጥ ሰነድ (መዝገብ)። ይህ ሙሉ ስምዎን ማካተት አለበት። ምሳሌዎች የእርስዎ የልደት የምስክር ወረቀት ወይም ፓስፖርት ናቸው።

- የእርስዎን ህጋዊ ሁኔታ የሚያረጋግጥ ሰነድ (ከ United States ውጭ ለተወለደ ማንኛውም ሰው)።
- የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር (SSN)፣ ወይም ለ SSN ብቁ እንዳልሆኑ የሚያሳይ ማረጋገጫ።
- በ Maryland ውስጥ መኖርዎን የሚያረጋግጡ ሁለት ሰነዶች።

ለእርስዎ በሰጠዎት ወኪል ድርጅት የተመሰከረላቸው ኦርጂናል ሰነዶችን ወይም ቅጂዎችን ይዘው መምጣት አለብዎት። MVA ፎቶ ኮፒዎችን፣ ኖተራይዝድ ቅጂዎችን፣ ወይም የተለወጠ ወይም የተሰረዘ መረጃ ያላቸውን ሰነዶች አይቀበልም።

MVA የሚቀበላቸውን ሙሉ ሰነዶች ዝርዝር ለማግኘት እባክዎን ድህረ ገጻችንን ይጎብኙ።

1. ጀማሪ አሽከርካሪ/ተመራቂ የፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት

ንግድ ነክ ያልሆነ የመንጃ ፍቃድ ለማግኘት የሚሄዱበት ሂደት የጀማሪ አሽከርካሪ/ተመራቂ የመንጃ ፍቃድ ስርዓት (Driver Licensing System) (GLS) ይባላል። ከዚህ በፊት የመንጃ ፍቃድ ኖሮት የማያውቅ ከሆነ በ GLS ሂደት ውስጥ ያልፋሉ። ለመንጃ ፍቃድ ለማመልከት ብቁ የሆኑ በሁሉም እድሜ ላሉ ሰዎች ተፈጻሚ ይሆናል። የተማሪ የትምህርት ፈቃድ እና ከዚያ ጊዜያዊ ፈቃድ በማግኘት ይጀምሩ። እነዚህ እርምጃዎች ለ መንጃ ፍቃድ “ከመመረቅዎ” በፊት የመንዳት ልምድ ይሰጡዎታል። የበለጠ ለማወቅ ማንበብዎን ይቀጥሉ

2. የተማሪ የትምህርት ፍቃድ

ንግድ ነክ ያልሆነ መንጃ ፈቃድ ኖሮት የማያውቅ ከሆነ የ 1 ኛ ዓይነት የለማጅ መማሪያ ፍቃድ ሊኖሮት ይገባል። ፈቃዱ እስከ 2 ዓመት ድረስ ይቆያል። ፈቃዱን ለማግኘት የእይታ እና የእውቀት ፈተና ማለፍ አለቦት።

ቀደም ሲል መንጃ ፍቃድ ካሎት እና የተለየ የመንጃ ፍቃድ አይነት የሚፈልጉ ከሆነ ለ 2 ተኛ የለማጅ የትምህርት ፍቃድ ማመልከት አለቦት። ቢያንስ 16 ዓመት ከ6 ወር መሆን አለቦት። የዓይነት 2 የለማጅ የትምህርት ፈቃድ እስከ 180 ቀናት ድረስ ይቆያል። ይህንን ፍቃድ ቢያንስ ለ14 ቀናት ካገኙ በኋላ፤ ለሙሉ ፍቃድ የማሽከርከር ፈተና መውሰድ ይችላሉ።

ለጊዜያዊ ፈቃድ ብቁ ከመሆንዎ በፊት የተማሪን የትምህርት ፈቃድ መያዝ ያለብዎት የጊዜ ገድብ በእድሜዎ ላይ የተመሰረተ ነው። ለፈቃድ የሚያመለክቱ ሰዎች “አመልካቾች” ይባላሉ።

ከ25 ዓመት በታች የሆኑ አመልካቾች፥

- ቢያንስ 15 ዓመት ከ9 ወር መሆን አለበት።
- ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ፤ ወላጅዎ ወይም ህጋዊ አሳዳጊዎ ማመልከቻውን በጋራ መፈረም አለባቸው።
- ከ16 ዓመት በታች ከሆኑ፤ የተሟላ የተማሪ ፈቃድ ትምህርት ቤት የመገኘት ማረጋገጫ ቅጽ ማቅረብ አለበት።

የተማሪ የስልጠና ፍቃድ እያሎት፤ የሚከተሉትን ማድረግ ያለብዎት፥

- የ Maryland የአሽከርካሪዎች ትምህርት መርሃ-ግብርን ያጠናቅቁ። ለአዲስ አሽከርካሪዎች፤ የሞተር ተሽከርካሪን ለማሽከርከር የሚያስፈልጉትን መረጃዎች እና ክህሎቶች እንዲማሩ ይረዳል። የ MVA ድህረ ገጽ ይህንን መርሃ-ግብር ለማስተማር የተፈቀደላቸው የአሽከርካሪዎች ትምህርት ቤቶችን ይዘረዝራል። **እና**
- ከተቆጣጣሪ አሽከርካሪ ጋር ቢያንስ 60 ሰአታት ማሽከርከር ይለማመዱ። እነዚህ የልምምድ ሰዓቶች ይባላሉ። ፀሐይ ከመጥለቋ 30 ደቂቃ በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ እና ፀሐይ ከወጣች 30 ደቂቃዎች በኋላ ባለው ጊዜ ውስጥ ቢያንስ 10 የልምምድ ሰዓታት መከሰት አለባቸው። **እና**
- የልምምድ ጊዜዎን ለመመዝገብ የተግባር እና የችሎታ ምዝገባ ማስታወሻ ይያዙ። የልምምድ እና የክህሎት ምዝገባዎች በ MVA ድህረ ገጽ ላይ ይገኛሉ።

እድሚያቸው 25 እና ከዚያ በላይ የሆኑ አመልካቾች፥

የተማሪ የስልጠና ፍቃድ እያሎት፤ የሚከተሉትን ማድረግ ያለብዎት፥

- የ Maryland የአሽከርካሪዎች ትምህርት መርሃ-ግብርን ያጠናቅቁ። **እና**
- ከተቆጣጣሪ ሹፌር ጋር ቢያንስ 14 ሰአታት ማሽከርከር ይለማመዱ። ፀሐይ ከመጥለቋ 30 ደቂቃ በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ እና ፀሐይ ከወጣች 30 ደቂቃዎች በኋላ ባለው ጊዜ ውስጥ ቢያንስ 3 የልምምድ ሰዓታት መከሰት አለባቸው። **እና**
- የልምምድ ጊዜዎን ለመመዝገብ የተግባር እና የችሎታ ምዝገባ ማስታወሻ ይያዙ። የልምምድ እና የክህሎት ምዝገባዎች በ MVA ድህረ ገጽ ላይ ይገኛሉ።

ለጊዜያዊ ፈቃድ ብቁ ከመሆንዎ በፊት ቢያንስ ለ 45 ቀናት ፈቃድ ሊኖርዎት ይገባል።

ጥሰቶች

በአንዳንድ ሁኔታዎች፤ ለጊዜያዊ ፈቃድ ብቁ ከመሆንዎ በፊት ፈቃድዎ ቀደም ብሎ ሊኖርዎት ይገባል፥

- በማንኛውም እድሜ፤ በወንጀል ከተከሰሱ ወይም የአመክሮ ጊዜ (Probation Before Judgement) (PBJ) ከተሰጥዎትዎ፤ የተማሪውን የስልጠና ፈቃድ ቢያንስ ለ9 ወራት ያህል ከተከሰሱበት ወይም ለደረሰበት ጥሰት PBJ ከተሰጠዎት በኋላ የተማሪዎችን የትምህርት ፈቃድ መያዝ አለበት። በማንኛውም ምክንያት ከታገዱ ይህ እንዲሁ ይሰራል። የማሽከርከር ክህሎት ፈተና ለመውሰድ ብቁ ከመሆንዎ በፊት የተቀሩትን የ GLS መስፈርቶች ማሟላት አለበት።
- ከ18 አመት በታች ከሆኑ፤ ለጊዜያዊ ፍቃድ ብቁ ከመሆንዎ በፊት ፈቃዱን ሳይጥስ ቢያንስ ለ9 ወራት መያዝ አለበት።
- የሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ ወይም GED ያሎት 18 ዓመት ከሆኑ፤ ወይም ከ19 እስከ 24 አመት የሆኑ ከሆነ፤ ለጊዜያዊ ፍቃድ ብቁ ከመሆኖ በፊት ያለ ምንም ጥሰት ፍቃዱን ቢያንስ ለ3 ወራት ያህል መያዝ አለበት።

3. ጊዜያዊ ፈቃድ

ጊዜያዊ የመንጃ ፍቃድ መንጃ ፍቃድ ላልያዙ አዲስ አሽከርካሪዎች ተሰጥቷል። ቁጥጥር ሳይደረግሎት ነገር ግን ከነ እገዳዎች እንዲነዱ ይፈቅድልዎታል። እገዳዎች እንደ ያለምንም ተሳፋሪዎች ማሽከርከር እና በምሽት አለማሽከርከር የመሳሰሉ ነገሮችን ያጠቃልላሉ። ለመደበኛ የመንጃ ፍቃድ ብቁ ከመሆንዎ በፊት ጊዜያዊ የመንጃ ፍቃድ ቢያንስ ለ18 ወራት መያዝ አለቦት።

ከተማሪ የስልጠና ፈቃድ ወደ ጊዜያዊ ለመመረቅ ከፈለጉ፤ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፥

- በ Maryland የተፈቀደውን የአሽከርካሪ ትምህርት መርሃ-ግብር በተሳካ ሁኔታ ማጥናቀቅ።
- የሚሰራ፣ ጊዜው ያላለፈበት የተማሪ ስልጥና ፍቃድ ይኑርዎት።
- ከላይ የተገለጸውን የጊዜ ገደብ ሳይጥሱ የተማሪን የስልጥና ፍቃድ ይያዙ።
- ከዚህ በላይ በተገለጸው ጊዜ ውስጥ በማናቸውም የመንቀሳቀስ ጥሰቶች ጥፋተኛ አይሁኑ ወይም የአመክሮ ጊዜ ማስጠንቀቂያ አይሰጡት።
- የተጠናቀቀ እና የተፈረመ የተግባር እና የክህሎት መዝገብ ያቅርቡ። ይህም ቢያንስ 60 የልምምድ ሰአታት ከተቆጣጣሪ ሹፌር ጋር ማሽከርከሮን (14 ግዜ 25 ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ) ማጠናቀቅዎን ማሳየት አለበት።
- የማሽከርከር ችሎታ ፈተናውን በተሳካ ሁኔታ ማለፍ።

4. የመንጃ ፍቃድ

የመንጃ ፍቃድ Graduated Driver Licensing System የመጨረሻ ደረጃ ነው።

ለመንጃ ፍቃድ ብቁ ለመሆን፤ ሊኖርዎት የሚገቡ ነገሮች፥

- ቢያንስ 18 አመት ይሁኑ።
- ቢያንስ ለ18 ወራት ጊዜያዊ ፈቃድ ይኑርት።
- ባለፋት 18 ወራት ውስጥ በማናቸውም የመንቀሳቀስ ጥሰቶች ያልተከሰሱ ወይም የአመክሮ ጊዜ ያልተሰጦት ይሁኑ።

እነዚህን ሁሉ መስፈርቶች ካሟሉ፤ MVA የጊዜያዊ ፈቃድዎን ወደ መንጃ ፍቃድ ወዲያውኑ ይቀይራል። ቅያሪውን የሚያሳይ ካርድ በፖስታ ይላክልዎታል። ካርዱን ከጊዜያዊ ፈቃድዎ ጋር መያዝ አለቦት።

5. ለአካለ መጠን ላልደረሰ ሰው ለፈቃድ ማመልከቻ ተባባሪ ፈራሚ

ከ18 አመት በታች ከሆኑ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጅ ኖት። ለአካለ መጠን ላልደረሱ ልጆች ወላጅ ወይም ህጋዊ ሞግዚት ማመልከቻቸውን በጋራ መፈረም አለበት። ያ

ማለት ሁለታችሁም ትፈርማላቸሁ። የእርስዎ ወላጅ ወይም አሳዳጊ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ አለቦት። የማስረጃዎች ምሳሌዎች፥

- የወላጅዎ ስም ያለበት ኦሪጅናል ወይም የተረጋገጠ የልደት የምስክር ወረቀት፤ ወይም
- ህጋዊ ሞግዚትነትን የሚያሳዩ የፍርድ ቤት ሰነዶች።

ባለትዳር ከሆኑ እና ባለቤትዎ 18 ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ፤ አብረው መፈረም ይችላሉ። ባለትዳር መሆንዎን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለብዎት።

ወላጅ፣ ህጋዊ አሳዳጊ ወይም የትዳር ጓደኛ ከሌልዎት፤ እድሜዎ ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ ኃላፊነት ያለው አዋቂ አብሮ መፈረም ይችላል። አዋቂ የስራ ቀጣሪ አንድ ምሳሌ ነው። በዚህ ሁኔታ፤ እንደ የወላጆችዎ ሞት የምስክር ወረቀት ወይም የነጻነት ማረጋገጫን የመሳሰሉ ማስረጃዎችን ማቅረብ ያስፈልግዎታል፡ ፡ ነጻ መውጣት ማለት ፍርድ ቤት ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች በወላጆቻቸው ቁጥጥር ስር እንዳይሆኑ ሲወስን ነው።

6. ለአካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ፈቃድ የጋራ ፈራሚ ስረዛ

አብሮ ፈራሚው ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅን ለ MVA የአስተዳደር ዳኝነት ክፍል የጽሁፍ ጥያቄ በማቅረብ ሊሰርዝ ይችላል። 18 ዓመት እስኪሞሉ ድረስ ፈቃድዎ እንደተሰረዘ ይቆያል፤ አብሮ ፈራሚ አብሮዎ አዲስ ማመልከቻ ካልፈረሙ በስተቀር። ከላይ የተገለጹትን መመዘኛዎች ማሟላት አለባቸው።

7. ከአገር ውጪ ፍቃዶች

የ Maryland ፍቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ አለቦት።

- የእይታ ምርመራ።
- የእውቀት ፈተና።
- የማሽከርከር ችሎታ ፈተና።
- በ MVA የተፈቀደ ሶስት ሰዓት የመንገድ ደህንነት መንዳት ትምህርት ፕሮግራም። የእነዚህን ዝርዝር በ MVA ድህረ ገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ።

ፈቃድዎ በእንግሊዝኛ የማይገኝ ከሆነ፣ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፥

- ዓለም አቀፍ ፈቃድ ይኑርዎት፤ ወይም
- ፈቃዶጭ ወደ እንግሊዝኛ እንዲተረጎም ያድርጉ።

የሰነድ ትርጉሞች በሚከተሉት መዘጋጀት አለባቸው (እና በደብዳቤው ራስጌ) ፥

- በ MVA ተቀባይነት ባለው አገልግሎት አቅራቢ ወይም በፍርድ ቤት ተርጓሚ፤ ወይም
- በትውልድ ሀገር ኤምባሲ።

እነዚህ ሰነዶች የሚከተሉትን መያዝ አለባቸው ፥

- የተተየበው/የታተመው የተርጓሚው ስም፣ እና
- ስልክ ቁጥር፣ እና
- የተርጓሚው ፊርማ

8. ለሁሉም ደንበኞች ትክክለኛነት

ለውጭ ቋንቋ ደንበኞች

MVA ይህ ለሚያስፈልጋቸው ደንበኞች በሌሎች ቋንቋዎች በርካታ ሰነዶችን እና ፈተናዎችን ያቀርባል። ይህ ስፓኒሽ፣ ኮሪያኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ቬትናምኛ፣ ኔፓልኛ እና ባህላዊ ቻይንኛን ይጨምራል።

በእንግሊዘኛ የመግባባት ችግር ካለቦት፤ MVA ን ሲጎበኙ አስተርጓሚ ልጠቀሙ ይችላሉ። በተለይም የእውቀት ፈተና ወይም የማሽከርከር ፈተና ሲወስዱ። የእውቀት ፈተናውን በሚናገሩት ቋንቋ ብናቀርብ፤ አስተርጓሚ ከመጠቀምዎ በፊት ቢያንስ 5 ጊዜ መውሰድ አለብዎት። በድረ-ገፃችን ላይ የተፈቀዱ አስተርጓሚዎችን ዝርዝር ማግኘት ይችላሉ።

ማስታወሻ፥ MVA አስተርጓሚ ለመጠቀም ክፍያ አይጠይቅም። ሆኖም ለአስተርጓሚው ለአገልግሎታቸው መክፈል አለቦት።

MVA ን ሲጎበኙ አስተርጓሚ እና/ወይም ተርጓሚ ካለዎት በጣቢያው ላይ የትርጉም እና/ወይም የትርጉም አገልግሎቶችን ከመስጠታቸው በፊት የሚሰራ የፎቶ መታወቂያ ካርድ (የግዛት መንጃ ፍቃድ ወይም መታወቂያ ካርድ) ማሳየት አለባቸው። የ MVA ሰራተኞች አስተርጓሚ/ተርጓሚው በእኛ ተቀባይነት ባለው ዝርዝር ውስጥ እንዳለ ያረጋግጣሉ።

ማስታወሻ፥ ለእውቀት/የችሎታ ፈተና አገልግሎት የሚሰጡ አስተርጓሚዎች ለሚፈተነው ደንበኛ ሌሎች አገልግሎቶችን ላይሰጡ ይችላሉ። ለምሳሌ፤ የመኖሪያ ፈቃድን ማረጋገጥ፣ የማሽከርከር ትምህርት ቤት ሥራን ማካሄድ፣ ወይም የሊዝ/የኪራይ ስምምነቶችን መስጠት አይችሉም።

ለአካል ጉዳተኛ ደንበኞች

MVA የእውቀት እና የአሽከርካሪ ብቃት ፈተናዎችን ለሚወስዱ የአካል ጉዳተኛ ደንበኞቹ መስተንግዶዎችን ይሰጣል። ይህ የሚያጠቃልለው፥

- ፈተና የመውሰጃ ተጨማሪ ጊዜ።
- የምልክት ቋንቋ ድጋፍ (የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ እና እውቅና ያላቸው መስማት የተሳናቸው ተርጓሚዎች)
- የቃል ፈተና
- ስክሪን አንባቢዎች
- የጆሮ ማዳመጫዎች
- የእይታ መርጃዎች

MVA በእያንዳንዱ ሰው ፍላጎት መሰረት መስተንግዶዎችን ያቀርባል። እባክዎን የደንበኞችን አገልግሎት ያግኙ፡ feedback.mva.maryland.gov

የእድገት አካል ጉዳተኝነት መግለጫ ካርድ

የእድገት አካል ጉዳተኝነት ካለብዎት፤ ከፈቃድዎ ጋር የእድገት ጉዳተኝነት መግለጫ ካርድ ለመያዝ መምረጥ ይችላሉ። የመንጃ ፍቃድ የሚያክል ሰማያዊ ካርድ ነው። ስለ አካል ጉዳተኝነትዎ፤ ከእርስዎ ጋር እንዴት በተሻለ ሁኔታ መግባባት እንደሚቻል፤ እና ለህግ አስከባሪ አካላት ሊያካፍሉት የሚፈልጓቸውን ሌሎች መረጃዎች ዝርዝር ለማቅረብ የሚያስችል ክፍት ቦታን ያካትታል።

የእድገት የአካል ጉዳተኝነት መግለጫ ካርድ መያዝ በፈቃደኝነት ነው – መፈለግዎን ይወስኑ። እርስዎ ወይም ወላጅዎ ወይም አሳዳጊዎ በማንኛውም የ MVA ቦታ የመረጃ ዴስክ በመጎብኘት ካርድ ማግኘት ይችላሉ። MVA ይህንን ካርድ ለማግኘት ስለ አካል ጉዳተኝነትዎ መረጃ ወይም ሰነድ እንዲያቀርቡ አይጠይቅዎትም።

ክፍል 3፡ መሰረታዊ ማሽከርከር

ከማሽከርከርዎ በፊት፥

- እርስዎ እና ተሽከርካሪዎ በጥሩ የማሽከርከር ሁኔታ ላይ መሆን አለብዎት።
- የሚሰራ የተማሪ ፈቃድ ወይም የመንጃ ፍቃድ፤ እና የተሽከርካሪ ምዝገባ ካርድ ከእርስዎ ጋር ሊኖርዎት ይገባል።
- መቀመጫዎን እና መስተዋትዎን ማስተካከል አለብዎት፤ እና
- እርስዎ እና ሁሉም ተሳፋሪዎች የመቀመጫ ቀበቶ መታጠቅዎን ያረጋግጡ።

1. በመከላከል ያሽከርክሩ

የመንዳት መሰረታዊ ህግ፤ በማንኛውም ጊዜ፤ አሽከርካሪው አደጋን ለማስወገድ ተሽከርካሪውን መቆጣጠር አለበት። የሞተር ተሽከርካሪን በሚያሽከረክሩበት ጊዜ፤ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ የማንቀሳቀስ ሃላፊነት አለብዎት። ይህ በራስዎ፣ በተሳፋሪዎችዎ እና መንገዱን በሚጠቀሙ ሌሎች ላይ የሚያደርሱትን አደጋዎች ይቀንሳል።

የእይታ ፍለጋ/የአሽከርካሪ ግንዛቤ

ደህንነቱ የተጠበቀ ሹፌር ለመሆን የማያቋርጥ ውሳኔዎችን ማድረግ አለብዎት። ይህንን ለማድረግ፤ በማንኛውም ጊዜ በተሽከርካሪዎ ዙሪያ ምን እንደሚፈጠር ማወቅ አለብዎት። አካባቢዎን ያለማቋረጥ መከታተል፤ ፍጥነትን እንዲቀይሩ ወይም መስመሮችን እንዲቀይሩ የሚያደርጉ ችግሮችን ለመለየት ይረዳዎታል። ይህ የተሽከርካሪዎን ፊት፣ ጎን እና ኋላ መመልከትን ይጨምራል።

ፊትለፊት በመፈለግ እና ፍጥነትን ለመለወጥ ወይም መስመሮችን ለመለወጥ በመዘጋጀት፤ የበለጠ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ማሽከርከር እና አደጋዎችን ለመለየት ጊዜ ማግኘት ይችላሉ። ይህ የመከላከል ማሽከርከር ይባላል።

የአደጋ ቁጥጥር

የሞተር ተሽከርካሪን መጠቀም አደጋ ሊያመጣ የሚችል እንቅስቃሴ ነው። አደጋን ሊያመጣ የሚችልን ነገር ለመቆጣጠር እና ደህንነቱ የተጠበቀ እና ኃላፊነት የሚሰማው አሽከርካሪ ለመሆን የሚከተሉትን ደረጃዎች ግንዛቤ ውስጥ ይክተቱ፥

- ፍጥነትዎን፣ ቦታዎን እና አቅጣጫዎን ወደሚከተለው ያስተካክሉ፥
- ለመንገድ ሁኔታዎች ምላሽ ይስጡ።
- ተሽከርካሪዎን ይቆጣጠሩ።
- በአካባቢዎ ለሚሆነው ነገር ምላሽ ለመስጠት ጊዜዎን ይጨምሩ።
- የመዞሪያ ምልክቶችን ወ.ዘ.ተ በመጠቀም ምን ለማድረግ እንዳሰቡ ለሌሎች አሽከርካሪዎች ያሳውቁ።
- በተሽከርካሪዎ እና መንገዱን በሚጠቀሙ ሌሎች ሰዎች መካከል ደህንነቱ የተጠበቀ ርቀት ይጠብቁ።
- ሌሎች አሽከርካሪዎች ማድረግ ያለባቸውን ያደርጋሉ ብለው አያስቡ።
- ሁሌም ይጠንቀቁ።

2. የመንገድ ቅድሚያ መብት

የመንገድ ቅድሚያ መብት ህጎች በመንገድ ላይ ያሉትን ሁሉ ደህንነት ለመጠበቅ ይረዳሉ። እነዚህ ህጎች ለሌሎች "የመንገድ ቅድሚያ መብትን መስጠት" እንዳለቦት ይገልፃሉ። የመንገዱን ቅድሚያ መብት መስጠት ማለት ሌሎች ተሽከርካሪዎች፣ ብስክሌተኞች ወይም እግረኞች ከፊትዎ እንዲሄዱ ወይም ከፊት ለፊትዎ ያለውን መንገድ እንዲያቋርጡ መፍቀድ ማለት ነው። መጀመሪያ እንዲሄዱ መፍቀድ ማለት ነው።

ምንም እንኳን ህጎቹ በተለያዩ ሁኔታዎች የመሄጃ መብትን ማን መስጠት እንዳለበት ቢገልጹም፤ የመንገድ ቅድሚያ መብት (በመጀመሪያ የመሄድ መብት) እንዳሎት በጭራሽ አያስቡ። ሁልጊዜ ሁኔታውን እና አጋጣሚዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት አለብዎት።

ለሚከተሉት የመንገድ ቅድሚያ መብት መስጠት አለቦት፥

- መስቀለኛ መንገድ ላይ ከእርስዎ በፊት ላለው ወይም ለሚመጣው አሽከርካሪ፡፡
- በቀኝዎ ላለው አሽከርካሪ፤ ሁለታችሁም በአንድ ጊዜ መስቀለኛ መንገድ ላይ ስትደርሱ፡፡
- በቀኝዎ ላለው አሽከርካሪ፤ የማቆሚያ ምልክቶች ያለው ባለ አራት መስቀለኛ መንገድ ላይ፡፡
- በመስቀለኛ መንገድ በማቋረት ላይ ላሉ እግረኞች፣ ብስክሌተኞች እና ሌሎች አሽከርካሪዎች።
- በ "T" መገናኛ ላይ ሲያቆሙ፤ ቀድሞውኑ በመንገድ ላይ ለሆነ አሽከርካሪ፡፡
- ለሌሎች አሽከርካሪዎች፤ ወደ መስቀለኛ መንገድ ሲጠጉ፤ ቅድሚያ ይስጡ የሚል ምልክት ወደ እርስዎ የሚመለከት ከሆነ፡፡

- በተቃራኒው የትራፊክ መስመር ላበ ላሉ አሽከርካሪዎች፤ ወደ ግራ ሲታጠፉ። ተቃራኒው የትራፊክ መስመር በተቃራኒ አቅጣጫ የሚሄዱ ተሽከርካሪዎች ያሉት ነው።
- ከመኪና መንገድ ወይም ከግል መንገድ ወደ ሚገቡበት መንገድ ላይ ላሉ አሽከርካሪዎች።
- በመግቢያ ወይም በፍጥነት መወጣጫ ላይ ከሆኑ፤ ቀድሞውኑ በአውራ ጎዳና ላይ ላሉ አሽከርካሪዎች።

3. የተሽከርካሪ ፍጥነትን መረዳት

በመንገዱ ላይ ያሉ ምልክቶች የፍጥነት ወሰኑ ምን እንደሆነ ይነግሩዎታል። የተለጠፈው የፍጥነት ወሰን በመልካም (ፍፁም) ሁኔታዎች ውስጥ በመንገድ ላይ ሊጓዙ የሚችሉት ከፍተኛው ህጋዊ ፍጥነት ነው። ከፍጥነት ወሰኑ በበለጠ ፍጥነት ማሽከርከር የለብዎትም። ሁል ጊዜ በአስተማማኝ ፍጥነት የመንዳት ሃላፊነት አለብዎት።

አብዛኛው ትራፊክ በሚንቀሳቀስበት ፍጥነት፤ እስከ ከፍተኛው የፍጥነት ወሰን ድረስ ማሽከርከር በጣም አስተማማኝ ነው። ከሌሎች ትራፊክ ባነሰ ፍጥነት መንዳት ሌሎች ተሽከርካሪዎች ያለማቋረጥ እንዲያልፉህ ያበረታታል። ይህ የመጋጨት እድሎችን ይጨምራል።

መፍጠን

ከፍጥነት ወሰኑ በላይ ማሽከርከር ከተለመዱት የተሽከርካሪ አደጋ መንስኤዎች አንዱ ነው። ከመጠን በላይ ፍጥነት ጊዜን አይቆጥብም እና ብዙውን ጊዜ ሰዎችን ለአደጋ የሚያጋልጡ ውሳኔዎችን ያመጣል። ከፍጥነት ወሰኑ በላይ ማሽከርከር ከባድ እና ብዙ ጊዜ አስከፊ ውጤት አለው፤ ምክንያቱም፦

- በኩርባዎች እና በመንገድ ላይ ባሉ መሰናክሎች ዙሪያ የመንዳት ቁጥጥር ችሎታዎን ይቀንሳል።
- ተሽከርካሪዎን ለማቆም ብዙ ጊዜ ይወስዳል።
- አደጋን ወይም አደገኛ ሁኔታን የማወቅ እና ምላሽ የመስጠት ችሎታዎን ይቀንሳል።
- ሌሎች ተሽከርካሪዎች፣ ብስክሌተኞች እና እግረኞች የእርሶን ርቀት በትክክል ሊወስኑ ስለማይችሉ የአደጋ ስጋትን ይጨምራል።
- በአደጋ ጊዜ ሃይልን እና ጉዳትን ይጨምራል፤ ይህም የበለጠ ከፍተኛ የአካል ጉዳት እና ሞት ያስከትላል።

ለሁኔታዎች ተስማሚ ፍጥነት

አስቸጋሪ (መጥፎ) ሁኔታዎችን በማወቅ፤ ፍጥነትዎን ማስተካከል አለብዎት። የ Maryland ተሽከርካሪ ህግ በተመጣጣኝ ፍጥነት እንዲያሽከረክሩ እና ያሉትን እና ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን እንዲያውቁ ያስገድድዎታል። በመንገድ ሁኔታ ላይ በመመስረት፤ ከተለጠፈው የፍጥነት ወሰን ብታች ቀስ ብለው ማሽከርከር ይችላሉ፤ ነገር ግን ከተለጠፈው የፍጥነት ወሰን በማንኛውም ከፍተኛ ፍጥነት ማሽከርከር ህገወጥ ነው።

ደህንነትዎን ለመጠበቅ በሚከተሉት ሁኔታዎች ፍጥነትዎን መቀነስ አለብዎት፦

- ሹል ኩርባዎች ወይም ኮረብታዎች – ለማየት አስቸጋሪ በሆነበት ቦታ።
- ተንሸራታች መንገዶች
- እግረኞች ወይም እንስሳት ሊኖሩባቸው በሚችሉ መንገዶች።
- የገበያ ማዕከሎች፣ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች እና የመሀል ከተማ አካባቢዎች።
- ከባድ ትራፊክ መጨናነቅ።
- ጠባብ ድልድዮች እና ዋሻዎች።
- የክፍያ አደባባዮች።
- ትምህርት ቤቶች፣ የመጫወቻ ሜዳዎች እና የመኖሪያ ጎዳናዎች።
- የባቡር ደረጃ መሻገሪያዎች። ይህም የባቡር ሀዲዶች ከመንገዱ ጋር እኩል በሆኑበት ቦታ ነው።

4. የመከተያ ርቀት

ሁልጊዜ በተሽከርካሪዎ እና ከፊትለፊትዎ ባለው መካከል ደህንነቱ የተጠበቀ ርቀት ይጠብቁ። አብዛኛዎቹ የኋላ ግጭቶች የሚከሰቱት በጣም በቅርበት በመከተል ነው። MVA ተስማሚ በሆነ የማሽከርከር ሁኔታ ውስጥ ቢያንስ ከ3 እስከ 4 ሰከንድ የመከተያ ርቀትን ይመክራል። ይህ ማለት ፊትለፊቶት ያለው መኪና ያለበት ተመሳሳይ የማመሳከሪያ ነጥብ ላይ ለመድረስ ከ 3 እስከ 4 ሰከንድ ይወስዳል። የማመሳከሪያ ነጥብ ፊትለፊት ላይ ያለ ነገር ነው፤ እንደ ድልድይ፣ መሻገሪያ፣ ምልክት ወይም የማይል ምልክት። በአስተማማኝ ርቀት እየተከተሉ እንደሆነ ለማወቅ የማመሳከሪያ ነጥብ ይምረጡ። ከፊቶት ያለው መኪና ያንን ነገር ሲያልፍ፤ 1 አንድ ሺህ፣ 2 ሺህ፣ 3 አንድ ሺህ፣ ወ.ዘ.ተ መቁጠር ይጀምሩ። መኪናዎ ነጥቡ ላይ ከመድረሱ በፊት 3 አንድ ሺህ ወይም ከዚያ በላይ ከደረሱ፤ ከፊት ለፊትዎ ካለው መኪና ቢያንስ 3 ሰከንድ ዘግይተው በደህና ርቀት ይጓዛሉ።

በተደጋጋሚ የሚያቆሙትን ተሽከርካሪዎች (አውቶብሶች፣ ማጓጓዣ ቫኖች)፤ በሚከተሉበት ጊዜ በተሽከርካሪዎ እና ከፊትለፊትዎ ባለው መካከል ያለውን ርቀት ወደ አራት ወይም አምስት ሰከንድ፤ እና አስፈላጊ ከሆነም የበለጠ ማሳደግ አለብዎት።

5. የማቆሚያ ርቀት

ደህንነቱ የተጠበቀ የመንዳት ፍጥነት ለመምረጥ እንዲረዳዎት ተሽከርካሪዎን ለማቆም የሚወስደው ርቀት አስፈላጊ ነው። የማቆሚያዎ ርቀት በብዙ ሁኔታዎች ላይ የሚመረኮዝ ሲሆን፤ የሚከተሉትን ይጨምራል፥

- አደገኛ ሁኔታ እንዳለ ለማየት የሚወስደው ጊዜ::
- የመንገዱ አይነት እና ሁኔታ::
- የጎማዎ ጥርሶች ሁኔታ::
- የመኪናዎ ፍሬን ሁኔታ::

6. በመስመር ማሽከርከር

ተሽከርካሪዎን በነጠላ መስመር ማሽከርከር አለብዎት። ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን እስካላረጋገጡ ድረስ መስመሮችን አይቀይሩ። በመስቀለኛ መንገድ ላይ በመስመሮች ላይ መንሸራተት ወይም የመስመር ለውጥ ማድረግ የለብዎትም።

በአጠቃላይ፤ ተሽከርካሪዎን ከመንገዱ መሃል በስተቀኝ በኩል ማቆየት አለቦት፤ ካልሆነ፥

- ወደ ተመሳሳይ አቅጣጫ የሚሄድ ሌላ መኪና እያለፉ ነው፤
- ይህን ማድረግ ችግር የለውም የሚል የትራፊክ ምልክት ወይም ማስተላለፊያ አለ፤ ወይም
- ቦታዎን በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲቀይሩ አስፈላጊ የሆነ ነገር በመንገድ ላይ አለ።

7. መዞር

በሚዞሩበት ጊዜ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፥

- መቼ መታጠፍ እንደሚችሉ የሚገልጹ ምልክቶችን እና ማስተላለፊያዎችን ይፈልጉ።
- የማዞሪያው ነጥብ ጋር ከመድረሶት በፊት ለመዞር ያቅዱ።
- ለሌሎች አሽከርካሪዎች ምን ለማድረግ እንዳሰቡ ለማሳወቅ ወደ መታጠፊያው ከመድረስዎ በፊት የመታጠፊያ ምልክትዎን ያብሩ።
- ለመዞር ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ተሽከርካሪዎን ከፊት፣ ከኋላ እና በሁለቱም በኩል ይመልከቱ።

አደጋን ለማስወገድ ተሽከርካሪዎን የመቆጣጠር ሃላፊነት አለብዎት።

8. U-turn

U-turns በጣም አደገኛ ሊሆሉ ይችላሉ፤ እና በሁሉም ቦታ ህጋዊ አይደሉም። U-turn መዞር ካለብዎት መጀመሪያ መዞር መፈቀዱን ያረጋግጡ። ከሆኑ፤ የግራ መታጠፊያ ምልክትዎን ያብሩ እና ያቁሙ እና ወደ እርስዎ ለሚመጣው ትራፊክ ቅድሚያ ይስጡ። መንገዱ ግልጽ ሲሆን፤ ወደ ተቃራኒው አቅጣጫ ወደሚጓዘው የውጭ ወይም የቀኝ መስመር ይዙሩ።

9. ማለፍ

ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ማለፍ ሲፈቀድ፤ የሚከተሉትን ማድረግ ያለብዎት፥

- ለማለፍ የሚያስፈልገውን ጊዜ እና ቦታ ይገምቱ እና ከማንኛውም ሌላ ተሽከርካሪ መንገድ ላይ ሳይደርሱ ማለፍ እንደሚችሉ ያረጋግጡ።
- በዙሪያዎ ያሉ አሽከርካሪዎች ምን ለማድረግ እንዳሰቡ እንዲያውቁ ከማለፍዎ በፊት የማዞሪያ ምልክትዎን ይጠቀሙ።
- ብዙ ቦታ ይልቀቁ እና በአስተማማኝ ርቀት በሌላኛው ተሽከርካሪ ዙሪያ ይሂዱ።
- ወደ መጡበት መስመር ከመመለሶት በፊት ያለፉትን ተሽከርካሪ ሁለቱንም የፊት መብራቶች በኋላ መመልከቻ መስታወቶት ይመልከቱ።

በአጠቃላይ፤ በሌላኛው ተሽከርካሪ በግራ በኩል ማለፍ አለብዎት። ነገር ግን፤ ደህንነቱ የተጠበቀ ከሆነ በቀኝ በኩል ማለፍ ይቻላል፤ በመንገዱ ላይ ይቆዩ እና፥

- ሌላኛው ተሽከርካሪ ወደ ግራ ሊታጠፍ ነው።
- በአንድ አቅጣጫ የሚጓዙ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ መስመሮች ያሉት ያልተዘጋ መንገድ ላይ ነዎት። ያልተዘጋ ማለት በመንገዱ ላይ ምንም አካፋይ መስመሮች፣ ምልክቶች ወይም ሌሎች ነገሮች የሉም ማለት ነው።
- ሁለት ወይም ከዚያ በላይ መስመሮች ያሉት ያልተዘጋ ባለ አንድ መንገድ ላይ ነዎት።

በሌላ ተሽከርካሪ በሚያልፉበት ጊዜ ለሌላው ተሽከርካሪ ቅድሚያ መስጠት አለቦት፤ እናም ፍጥነትዎን መጨመር የለብዎትም።

ማለፍ የማይችሉት፥

- ማለፍ በማይፈቀድበት ቀጠና ውስጥ ሲሆኑ::
- በመንገዱ መሃል ያለው ጠንካራ ቢጫ መስመር ከጎንዎ በሚገኝበት ቦታ::
- ድርብ ጠንካራ ቢጫ መስመሮች ባሉበት::

- በማለፍ ጊዜ የሌሎች ተሽከርካሪዎችን ደህንነቱ የተጠበቀ አሠራር የሚያደናቅፍ ከሆነ፡፡
- ወደ ኮረብታ ጫፍ ላይ ወይም ኩርባ መንገድ ላይ ሲቃረቡ፤ ፊትለፊት በግልጽ ማየት አይችሉም፡፡
- በ 100 ጫማ ርቀት ላይ ወዳለ ድልድይ፣ ከፍ ያለ መንገድ ወይም መሿለኪያ ሲቀርቡ፤ እይታዎ ሲከለል፡፡
- በ 100 ጫማ ርቀት ላይ፤ መሰቀለኛ መንገድ ወይም የባቡር ሀዲድ ደረጃ ሲያቋርጡ፡፡
- በመንገዱ ዳርቻ፤ ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ፡፡

10. አጠቃላይ የመኪና ማቆሚያ ደንቦች

ተሽከርካሪዎ በቆመበት ጊዜ አደጋ እንዳይደርስበት የማረጋገጥ ሃላፊነት አለብዎት። ይህ ማለት በማንም ላይ ጉዳት እንዳያስከትል ማለት ነው። ሁል ጊዜ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፥

- በግልፅ ለማቆምያ የተዘጋጁ ቦታዎች ላይ ያቁሙ።
- በመንገድ ላይ በሚያቆሙበት ጊዜ፤ ተሽከርካሪዎን በተቻለ መጠን ከትራፊክ ርቀው ያቁሙ። ኩርባ ካለ በተቻለ መጠን ወደ እሱ አስጠግተው ያቁሙ።
- በሚያቆሙበት ጊዜ የማቆምያዎ ፍሬን ይያዙ።
- ተሽከርካሪው በእጅ የሚሰራ ከሆነ ማርሽ ላይ፤ ወይም አውቶማቲክ ማስተላለፊያ ካለው ‘ፓርክ’ ላይ ያስቀምጡት።

- በሩን ከመክፈትዎ በፊት መስተዋቶችዎን እና ትራፊኩን ያረጋግጡ። ከወጡ በኋላ በተቻሎት ፍጥነት በሩን ይዝጉ።
- የመኪና ቁልፎችን ከእርስዎ ጋር ይውሰዱ። ከተሽከርካሪዎ በሚወጡበት ጊዜ ሁሉ በሮችን መቆለፍ ጥሩ ልማድ ነው።

“በቀኝ ይቆዩ” ምልክቶችን በሚያዩበት ቦታ፤ ተሽከርካሪ ሊያልፉ ካልሆነ በስተቀር በቀኝ በኩል ባለው መስመር ወይም መስመሮች ያሽከርክሩ።

ክፍል 4፡ ምልክቶች፣ ማስተላለፊያዎች እና የእግረኛ መንገድ ምልክቶች

ሁሉም ሰው የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን መታዘዝ አለበት። የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች ትራፊክን የሚቆጣጠሩ፣ የሚያስጠነቅቁ እና የሚመሩ የትራፊክ ማስተላለፊያዎች፣ ምልክቶች እና የመንገድ ምልክቶች (በመንገድ ላይ ያሉ መስመሮች) ናቸው። የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን አለማክበር የአደጋዎች ዋነኛ መንስኤ ነው።

ሁሉንም የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች መታዘዝ የማይኖርብዎት ብቸኛው ጊዜ ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የተለየ ነገር እንዲያደርጉ ሲነግሮት ነው፥

- የፖሊስ መኮንን ወይም ሌላ የአደጋ ጊዜ ሰራተኞች::
- የትምህርት ቤት መሻገሪያ ጠባቂ ዩኒፎርም የለበሰ ትምህርት ቤት አጠገብ ያለውን ትራፊክ ጥባቂ::

የትራፊክ ምልክት በማይሰራበት ጊዜ፥

- በግልጽ ምልክት ባለው የማቆሚያ መስመር ላይ ማቆም አለብዎት:: የማቆሚያ መስመር በመንገዱ ላይ የተቀባ ሰፊ ነጭ መስመር ሲሆን ይህም በመስቀለኛ መንገድ ላይ የት ማቆም እንዳለቦት ያሳያል።
- በግልጽ የተቀመጠ የማቆሚያ መስመር ከሌለ፤ ወደ እግረኛ መሻገሪያ ከመግባትዎ በፊት ማቆም አለብዎት።
- በግልጽ የተቀመጠ የማቆሚያ መስመር ወይም የእግረኛ መሻገሪያ መንገድ ከሌለ፤ ወደ መስቀላኛ መንገድ ከመግባትዎ በፊት ማቆም አለብዎት።
- በመስቀለኛ መንገድ ውስጥ ላሉ ተሽከርካሪዎች እና እግረኞች ቅድሚያ መስጠት አለቦት፤ እና ወደ መስቀለኛው መንገድ መግባት ደህንነቱ የተጠበቀ እስኪሆን ድረስ ቆመው ይጠብቁ።

1. የትራፊክ ምልክቶች

የተሽከርካሪ ምልክቶች



1. ቋሚ ቀይ ምልክት

በማቆሚያው መስመር ላይ ሙሉ ለሙሉ ይቁሙ:: በግልጽ የተቀመጠ የማቆሚያ መስመር ከሌለ፤ ከእግረኛ መሻገሪያ በፊት እና ወደ መስቀለኛ መንገድ ከመግባትዎ በፊት ማቆም አለብዎት። ምልክቱ ቀይ እስከሆነ ድረስ ቆመው ይጠብቁ::

ቀይ ማብራት የሚከለክል ምልክት ከሌለ በስተቀር፤ ሙሉ በሙሉ ካቆሙ በኋላ፤ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፥

- ወደ ቀኝ መታጠፍ፤ ወይም
- ከአንድ ባለ አንድ መንገድ ወደ ሌላ ባለ አንድ መንገድ ወደ ግራ መታጠፍ::

ቀይ መብራትን ሲያበሩ፤ የመንገዱን ቅድሚያ መብት ለእግረኞች እና ለሁሉም ሌሎች ትራፊክ መስጠት አለብዎት።



2. ቋሚ ቢጫ ምልክት

ይህ ማለት ምልክቱ ከአረንጓዴ ወደ ቀይ እየተቀየረ ነው:: በአስተማማኝ ሁኔታ ለማቆም ጊዜ ይሰጥዎታል:: በተጨማሪም በመስቀለኛ መንገድ ላይ ያሉት ተሽከርካሪዎች ምልክቱ ወደ ቀይ ከመቀየሩ በፊት በመስቀለኛው መንገድ በኩል እንዲያልፋ ጊዜ ይሰጣል። ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ለማቆም ወደ ለመስቀለኛው መንገድ በጣም ቅርብ ከሆኑ፤ በጥንቃቄ ወደ በመስቀለኛው መንገድ ይቀጥሉ።



3. ቋሚ አረንጓዴ ምልክት

በመስቀለኛው መንገድ ውስጥ ሌሎች ተሽከርካሪዎች አለመኖራቸውን በመጀመሪያ ካረጋገጡ በኋላ በጥንቃቄ ይቀጥሉ። ይህ ማለት ይጠንቀቁ እና ከፍተኛ ትኩረት ይስጡ። ደህንነቱ በተጠበቀ ጊዜ ለመቀጠል፤ ምልክት ወይም ሌላ ማስተላለፊያ መዞር ካልከለከለ በስተቀር ወደ ፊት

በመሄድ ወይም በመታጠፍ ወደ መስቀለኛው መንገድ መግባት ይችላሉ። በመስቀለኛ መንገድ ላሉ እግረኞች እና ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለቦት።



4. ቋሚ ቀይ ቀስት ምልክት

ቀስቱ ወደ ሚያመለክተው አቅጣጫ መሄድ ከፈለጉ፣ የማቆሚያው መስመር፣ የእግረኛ መሻገሪያ ወይም መስቀለኛ መንገድ ላይ ከመድረሱ በፊት ሙሉ በሙሉ ይቁሙ። ምልክቱ ቀይ እስከሆነ ድረስ ቆመው ይጠብቁ።



5. ቋሚ ቢጫ ቀስት ምልክት

ይህ ማለት ወደ ቀስቱ አቅጣጫ የመዞር ፍቃድ ያበቃል ማለት ነው። ፍጥነትዎን መቀነስ እና በጥንቃቄ መቀጠል አለብዎት።



6. ቋሚ አረንጓዴ ቀስት ምልክት

ወደ ቀስት ነጥቡ አቅጣጫ በጥንቃቄ ይቀጥሉ:: በመስቀለኛ መንገድ ላሉ ሁሉም እግረኞች እና ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ መሰጠት እንዳለቦት ያስታውሱ።



7. የሚያብለጨልጭ ቀይ ምልክት

በማቆሚያው መስመር ላይ ሙሉ ለሙሉ ይቁሙ:: በግልጽ የተቀመጠ የማቆሚያ መስመር ከሌለ፤ ከእግረኛ መሻገሪያ በፊት እና ወደ መስቀለኛ መንገድ ከመግባትዎ በፊት ማቆም አለብዎት። ቅድሚያ ለሁሉም ሌሎች ትራፊክ እና እግረኞች ይስጡ። የቀይ መብራት ምልክት ሲያበቃ እና መንገዱ ባዶ ሲሆን ይቀጥሉ።

የሚያብረቀርቅ ቀይ ምልክት በባቡር ሐዲድ ማቋረጫ ላይ የሚገኝ ከሆነ፤ ባቡር ባያዩም ሙሉ በሙሉ ማቆም አለብዎት። መንገዱ ግልጽ ሲሆን ይቀጥሉ::



8. የሚያብለጨልጭ ቢጫ ምልክት

ፍጥነትዎን መቀነስ እና በጥንቃቄ መቀጠል አለብዎት።



9. የሚያብለጨልጭ ቀይ ቀስት ምልክት

የማቆሚያው መስመር፣ የእግረኛ መሻገሪያ ወይም መስቀለኛ መንገድ ላይ ከመድረሶት በፊት ሙሉ በሙሉ ይቁሙ። ቅድሚያ ለሁሉም ሌሎች ትራፊክ እና እግረኞች ይስጡ። መንገዱ ግልጽ በሚሆንበት ጊዜ ወደ ቀስቱ አቅጣጫ ይቀጥሉ።

10. የመስመር አጠቃቀም ምልክቶች

በአንዳንድ መንገዶች፤ በአንዳንድ መስመሮች ውስጥ ያለው ትራፊክ በቀን ውስጥ በተወሰኑ ሰዓቶች ውስጥ በአንድ አቅጣጫ፤ እና በሌሎች ሰዓቶች ውስጥ በሌላ አቅጣጫ ሊንቀሳቀስ ይችላል። ይህም በቀን ውስጥ በተለያዩ ሰዓታት ውስጥ ያለው የትራፊክ ፍሰት ክብደት ላይ የተመሰረተ ነው። እነዚህ ተቀያያሪ መስመሮች ይባላሉ። የመስመር አጠቃቀም ምልክቶች በየትኛው አቅጣጫ መሄድ እንደሚችሉ ይነግሩዎታል። መስመሮቹ እና አቅጣጫቸው ምልክቶች፣ ማስተላለፊያዎች እና ቀለሞች ሊደረግባቸው ይችላል።

ቀይ “X” ምልክት ያለበት መስመር ላይ ማሽከርከር የለብዎትም።

አረንጓዴ ቀስት ምልክት ያለበት መስመር ላይ ማሽከርከር ይችላሉ።



የቋሚ ቢጫ “X” ምልክት ማለት፤ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ በተቻለ ፍጥነት ከመስመሩ መውጣት አለብዎት ማለት ነው።



የሚያብረቀርቅ ቢጫ “X” ምልክት ወይም ባለሁለት አቅጣጫ ወደ ግራ ታጠፊ ቀስቶች ማለት፤ መስመሩን ለግራ መታጠፊያ መጠቀም ይችላሉ። መስመሩን በተቃራኒ አቅጣጫ ከሚመጡ ወደ ግራ ከሚታጠፉ ተሽከርካሪዎች ጋር ይጋራሉ።

የእግረኛ መሻገሪያ ምልክቶች

የእግረኛ መሻገሪያ ምልክት ትራፊክን ስለሚያቆም፤ እግረኞች በደህንነት መንገዱን እንዲሻገሩ ያደርጋል። እግረኞች በመንገዱ ዳር ባለ ምሰሶ ላይ አንድ ቁልፍ በመጫን ምልክቱን ይጠቀማሉ። አሽከርካሪዎች እንዲያቆሙ እና ከዚያም እግረኞች እንዲሻገሩ ይነግራል። እግረኞች እና አሽከርካሪዎች የሚያዩዋቸው ምልክቶች ከታች አሉ።

እግረኞች

ይህንን ይመልከቱ	ይህንን ይመልከቱ
	ይቁሙ ለመሻገር ቁልፍ ይጫኑ
	ይጠብቁ!
	እየጠበቁ ይቆዩ
	ሁለቱንም መንገዶች ይመልከቱ ትራፊክ ከቆመ በኋላ መሻገር ይጀምሩ
	አይጀምሩ መሻገር ከጀመሩ ይጨርሱ
	ይቁሙ ትራፊክ መንቀሳቀስ ጀምሯል

አሽከርካሪዎች

ይህንን ይመልከቱ	ይህንን ይመልከቱ
	ይሂዱ
	የሚያብለጨልጭ ቢጫ ፍጥነት ይቀንሱ
	ደማቅ ቢጫ ለማቆም ይዘጋጁ
	ደማቅ ቀይ ይቁሙ!
	የሚያብለጨልጭ ቀይ ይቁሙ በጥንቃቄ ይቀጥሉ
	በጥንቃቄ ይቀጥሉ

2. የትራፊክ ምልክቶች

ቀለሞች & ቅርጾች

የትራፊክ ምልክቶች መረጃን ለማስተላለፍ ምልክቶችን እና ቃላትን ይጠቀማሉ። የትራፊክ ምልክቶችን ቅርጻቸውን እና ቀለሞቻቸውን እና በላያቸው ላይ ያሉትን ቃላት፣ ቁጥሮች ወይም ምልክቶች በፍጥነት መለየት መቻል አለብዎት። የትራፊክ ምልክት ዋናው የመደብ ቀለም ምን ዓይነት መረጃ እንዳለው በፍጥነት ይነግርዎታል።

ቀይ - ያቁሙ፣ ቅድሚያ ይስጡ፣ አይግቡ፣ ወይም የተሳሳተ መንገድ

ቢጫ - ፊትለፊት ምን እንደሚጠብቆት አጠቃላይ ማስጠንቀቂያ

ነጭ - የፍጥነት ወሰን፣ ቀኝን መያዝ፣ እና አንዳንድ የመመሪያ ምልክቶች

ብርቱካን - የግንባታ እና የጥገና ሥራ አካባቢ ማስጠንቀቂያ

አረንጓዴ - መድረሻዎች፣ ርቀቶች እና አቅጣጫዎች

ሰማያዊ - እንደ ምግብ፣ ነዳጅ ማደያ እና የእረፍት ቦታ ያሉ አገልግሎቶች ምልክቶች

ቡናማ - የመዝናኛ እና የባህል ፍላጎት ቦታዎች

ብርሃናማ ቢጫ-አረንጓዴ - ትምህርት ቤት፣ እግረኛ እና የብስክሌት ምልክቶች

ብርሃናማ ሮዝ - ድንገተኛ የትራፊክ አደጋዎች

ጥቁር - ባለ አንድ መንገድ ምልክቶች እና መልዕክቶችን የሚቀይሩ ምልክቶች

ባለ ስምንት ጎን፡ ይቁሙ

ባለ ስምንት ጎን (ስምንት ጎን ያለው) ቅርፅ ሁል ጊዜ ይቁሙ ማለት ነው። ሙሉ በሙሉ ማቆም አለብዎት።

ሦስት ማዕዘን ቅርጽ፡ ቅድሚያ ይስጡ

ለሌላ ተሽከርካሪዎች እና እግረኞች የመንገድ ቅድሚያ መብት ለመስጠት ቀስ ይበሉ እና አስፈላጊ ከሆነ ያቁሙ።

ድያመንድ (Diamond)፡ ማስጠንቀቂያ

እነዚህ ምልክቶች ከፊትለፊት ስለሚመጡ ልዩ ሁኔታዎች ወይም አደጋዎች ያስጠነቅቁዎታል። ፍጥነትዎን መቀነስ ሊኖርብዎት ይችላል፤ ስለዚህ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ ይሁኑ።

ጠበብ ያለ ባለ ሶስት ጎን ባንዲራ፡ ማለፍ አይቻልም

ማለፍ የማይቻልበትን ቀጠና መነሻ ያመለክታል። ሌሎች ተሽከርካሪዎችን አይለፉ።

አራት ማዕዘን፡ ተቆጣጣሪ ወይም መመሪያ

ቀጥ ያሉ ምልክቶች አብዛኛውን ጊዜ መመሪያ ይሰጥዎታል ወይም የመንገዱን ደንብ ይነግሩዎታል።

አግድም ምልክቶች አብዛኛውን ጊዜ አቅጣጫዎችን ወይም መረጃዎችን ይሰጣሉ።

አምስት ማዕዘን፡ የትምህርት ቤት አከባቢ እና የትምህርት ቤት መሻገሪያ

ባለ አምስት ጎን (አምስት ጎን ያላቸው) ቅርፅ ስለ ትምህርት ቤት አከባቢዎች ያስጠነቅቃል፤ እና የትምህርት ቤት ልጆች መንገዱን የሚያቋርጡባቸውን የትምህርት ቤት መሻገሪያዎችን ምልክት ያደርጋል።

ክብ፡ የባቡር ሀዲድ ማስጠንቀቂያ

ከፊትለፊት የባቡር ማቋረጫ እንዳለ ለማስጠንቀቅ ይጠቅማል።

መስቀልኛ ምልክት፡ የአውራ ጎዳና—ባቡር ደረጃ መሻገሪያ

የባቡር ማቋረጫ መንገድ ቦታን ይለያል።

ትራፔዞይድ (Trapezoid)

የመዝናኛ እና የባህል ፍላጎት ቦታዎች እና ብሔራዊ የደን መስመሮች

የቁጥጥር ምልክቶች

እነዚህ ምልክቶች ስለ የትራፊክ ህጎች ናቸው። እነሱን መታዘዝ አለብዎት።

1. ባለ 8-ጎን ምልክት፣ በቀይ ላይ ነጭ ፊደሎች

በመንገድ ላይ የሚያዩት ባለ 8 ጎን ምልክት፤ የማቆሚያ ምልክት ብቻ ነው። ወደ ማቆሚያ ምልክት ሲመጡ፦

- በማቆሚያው መስመር ላይ ሙሉ በሙሉ ማቆም አለብዎት።
- የማቆሚያ መስመር ከሌለ፤ ወደ እግረኛ መሻገሪያ መንገድ ከመግባትዎ በፊት ያቁሙ።
- የማቆሚያ መስመር ወይም የእግረኛ መሻገሪያ ከሌለ፤ ወደ መስቀለኛው መንገድ ከመግባትዎ በፊት ያቁሙ።

በመስቀለኛ መንገድ ውስጥ ላሉ ተሽከርካሪዎች እና እግረኞች ቅድሚያ መስጠት አለቦት፤ እና ወደ መስቀለኛው መንገድ ለመግባት እና ለመቀጠል ደህንነቱ የተጠበቀ እስኪሆን ድረስ ቆመው ይጠብቁ።

2. ባለ 3-ጎን ምልክት፣ በነጭ ላይ ቀይ ፊደሎች

የቅድሚያ መስጫ ምልክቱ እንደዚህ አይነት ቅርጽ ያለው ብቸኛው ምልክት ነው። ወደ ቅድሚያ መስጫ ምልክት ሲደርሱ ፍጥነትዎን ይቀንሱ። ወደ ግራ እና ቀኝ ይመልከቱ። ለእግረኞች፣ ለብስክሌቶች እና ለተሽከርካሪዎች ቅድሚያ ይስጡ። አንዴ ከተሽከርካሪዎች፣ ብስክሌቶች እና እግረኞች ጋር ከተስማሙ በኋላ፤ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ማድረግ ሲችሉ ብቻ መቀጠል ይችላሉ።

3. አራት ማዕዘን (ባለ 4-ጎን) ምልክቶች፤ በነጭ ላይ ጥቁር

እነዚህ ምልክቶች ትራፊክን ይቆጣጠራሉ። ይህ ምልክት ለተለጠፈበት የመንገድ ክፍል፤ ከፍተኛውን የፍጥነት ወሰን ይነግርዎታል።

ወደ ቀኝ መታጠፍ የለም

ወደ ግራ መታጠፍ የለም

U-Turn መዞር የለም

ምንም መዞር የለም

ወደ ግራ መታጠፍ ብቻ

አይግቡ

የመኪና ማቆሚያ የለም

በቀይ ላይ መዞር የለም

አይለፉ

ከመንገዱ አካፋይ በስተቀኝ በኩል ይቆዩ

ለግራ ታጣፊ በአረንጓዴ ላይ

የብስክሌት መስመር

የተሳሳተ መንገድ

ለአካል ጉዳተኞች የመኪና ማቆሚያ ፈቃድ የተያዘ

ባለ ሁለት ግራ መንገድ

በሁለቱም አቅጣጫ የሚጓዙ ተሽከርካሪዎች ወደ ግራ ለመታጠፍ መሃከለኛውን መስመር መጠቀም ይችላሉ።

ባለ አንድ መንገድ ትራፊክ ወደ ቀስቱ አቅጣጫ ብቻ መሄድ ይችላል።

ከፍተኛ ተሸካሚ ተሽከርካሪዎች

በመኪናዎት ውስጥ ምልክቱ ላይ ምልክት የተደረገበትን ያህል የሰዎች ብዛት ከጫኑ ብቻ ይህንን መስመር መጠቀም ይችላሉ

የማስጠንቀቂያ ምልክቶች

እነዚህ ምልክቶች ለአሽከርካሪዎች በመንገድ ላይ ስለሚመጡ ሁኔታዎች ይነግሮታል።

ከፊትለፊት ይቁሙ

ከፊትለፊት ቅድሚያ ይስጡ

ከፊትለፊት ምልክት

ወደ ቀኝ መታጠፍ

የእግረኛ መሻገሪያ

የትራፊክ ክበብ (አደባባይ ተብሎም ይጠራል)

የፍጥነት ወሰን

ከመወጣጫ መንገድ የፍጥነት ወሰን ይውጡ

ማለፊያ ቦታ የለም

ሁለት መንገዶች እየተዋሃዱ ነው

መንገዱ ከፊትለፊት ይከፋፈላል

የተከፋፈለ መንገድ ከፊትለፊት ያበቃል

የመንገድ ኩርባዎች

ሹል ማዞሪያዎች

የመንገድ ኩርባዎች

የጎን መንገድ ከፊትለፊት ይገባል

መስመሩ የግራ ውህደትን ያበቃል

መስቀለኛ መንገድ

“T” መስቀለኛ መንገድ ከፊትለፊት


የባቡር ሀዲድ ከ “T” መስቀለኛ መንገድ በፊት

ሸጣጣ ኮረብታ

እርጥብ በሚሆንበት ጊዜ የሚያንሸራትት

መስመሩ ያበቃል

የጭነት መኪና ማቋረጫ

የከባድ መኪና ማቋረጫ

የእግረኛ እና የብስክሌት መሻገሪያ

“አጋዘን ወይም ሌላ የዱር አራዊት መሻገሪያ”

ባንዲራ ከፊትለፊት

የመንገድ ስራ ከፊትለፊት

ተለዋጭ መንገድ

የትምህርት ቤት መሻገሪያ ከፊትለፊት

የትምህርት ቤት አውቶቡስ ማቆሚያ ከፊትለፊት

የስራ ዞን ጀምር

ገቢር የስራ ዞን ጨርስ

ብልጭ ድርግም በሚሉበት ጊዜ የሥራ ዞን ገቢር ነው (የተጨመሩ ቅጣቶች)

የላይ መስመር አጠቃቀም

እነዚህን ምልክቶች ከመንገድ በላይ ያያሉ። መድረሻዎች፣ አቅጣጫዎች እና መስመሮችን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል መረጃ ይሰጣሉ።

የመንገድ ምልክት ማድረጊያ ምልክቶች

አንዳንድ መንገዶች ቁጥር አላቸው:: የመንገድ ቁጥሮች ተብለው ይጠራሉ:: እነዚህ ምልክቶች የመንገዱን ቁጥር እና የመንገዱን አይነት ይለያሉ።

በግዛት መካከል | U.S. መንገድ | የግዛት መንገድ

የአገልግሎት መረጃ እና መመሪያ ምልክቶች

እነዚህን ምልክቶች የተወሰኑ መውጫዎችን ከወሰዱ፤ ሊያገኟቸው የሚችሏቸውን ንግዶች እና አገልግሎቶች ይለያሉ።

ማቆምና ማሽከርከር | የመድረሻ መመሪያ | የአጠቃላይ አገልግሎቶች ምልክት



ማረፊያ | ሆስፒታል | ነዳጅ | ምግብ | አየር ማረፊያ | ባቡር ጣቢያ

የርቀት ምልክት ማድረጊያ ምልክቶች

እነዚህ በእያንዳንዱ ማይል በግዛት መካከል ባሉ አውራ ጎዳናዎች ላይ ይገኛሉ። አንድ ሰው እንዲያገኝዎት ከፈለጉ ሊጠቀሙበት የሚችሉትን የአካባቢ መረጃ ይሰጣሉ። ለምሳሌ፤ ጎታች መኪና ወይም የድንገተኛ አደጋ ሰራተኞች

4. የእግረኛ መንገድ ምልክቶች

የመስመር ምልክቶች ዓይነቶች

የእግረኛ መንገድ ምልክቶች የመንገድ ላይ መስመሮች ናቸው ከመንገድ ራቅ ብለው መመልከት ሳይጠበቅብዎት ጠቃሚ መመሪያ እና መረጃ ይሰጣሉ። ሁሉንም የሚከተሉትን የእግረኛ መንገድ ምልክቶች ማወቅ እና ምን ማለት እንደሆነ መረዳት አለቦት። መስመሮች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በጣም ሰፊ ሊሆኑ ይችላሉ እና/ወይም የእርስዎን ትኩረት ለመሳብ እና መስመሮቹን ለማየት እንዲረዳዎ የሚያንፀባርቁ ጠቋሚዎች ተያይዘዋል።



ነጠላ የተሰበረ - ነጭ

ሁሉም ትራፊክ ወደ አንድ አቅጣጫ የሚሄዱባቸውን መንገዶችን ይለያል፤ እና ከአንድ መስመር ወደ ሌላው መሻገር ይፈቀዳል። ከአንድ በላይ መስመር ባላቸው መንገዶች ላይ ጥቅም ላይ ይውላል።



ነጠላ የተሰበረ - ቢጫ

ተሽከርካሪዎች በተቃራኒ አቅጣጫ የሚጓዙባቸውን መንገዶችን ይለያል፤ እና በሁለቱም አቅጣጫዎች በጥንቃቄ ማለፍ ይፈቀዳል። ባለ2-መስመር፤ ባለ 2-መንገድ መንገዶች ላይ እንደ መሃል መስመር ያገለግላል።



ነጠላ ድፍን - ነጭ

የመንገዱን ቀኝ ጠርዝ ምልክት ያደርጋል: : እንዲሁም ሁሉም ተሽከርካሪዎች ወደ አንድ አቅጣጫ የሚሄዱባቸውን መንገዶችን ይለያል፤ ነገር ግን የመስመርን መቀየር አይበረታታም።



ነጠላ ድፍን - ቢጫ

በተከፋፈሉ አውራ ጎዳናዎች፤ ባለአንድ መንገድ መንገዶች እና መወጣጫ መንገዶች ላይ የግራ ጠርዝ መስመሮችን ምልክት ያደርጋል። የተከፋፈለ አውራ ጎዳና በየአቅጣጫቸው በሚጓዙት ትራፊክ መካከል ጠባቂ ሀዲድ፣ የተዘረጋ መሬት ወይም ሌላ መከላከያ አለው።



ድርብ (ጎን ለጎን) የተሰበረ - ቢጫ

ተቀያያሪ መስመሮችን ጠርዞች ምልክት ያደርጋል – ትራፊክ በአንድ አቅጣጫ እና አንዳንድ ጊዜ በሌላ አቅጣጫ የሚፈስባቸው መንገዶች። የትራፊክ ምልክቶች እና ማስተላለፊያዎች በሚፈቅዱት መሰረት ወደ መስመሩ መግባት እና መውጣት ይችላሉ።



ድርብ (ጎን ለጎን) ድፍን - ነጭ

ሁሉም ትራፊክ ወደ አንድ አቅጣጫ የሚሄዱባቸውን መንገዶችን ይለያል እና መስመሮችን መቀየር አይፈቀድልዎትም። አጠቃላይ መስመሮችን ከ HOV መስመሮች ለመለየት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። እንዲሁም፤ በሁለቱም በኩል ማለፍ ከሚችሏቸው የሚጋርዱ ነገሮች ፊት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።



ድርብ (ጎን ለጎን) ድፍን - ቢጫ

ትራፊክ በተቃራኒ አቅጣጫ የሚሄድባቸውን መንገዶችን ይለያል እና በሁለቱም አቅጣጫ ማለፍ አይፈቀድም። ባለ ድርብ ጠንካራ ቢጫ መስመር ላይ ወደ ግራ መታጠፍ ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል፤ ወደ መኪና መንገድ ሲታጠፉ።



ድፍን በተጨማሪ የተሰበረ - ቢጫ

በአንድ አቅጣጫ ብቻ ማለፍ በሚፈቀድባቸው ባለሁለት አቅጣጫ መንገዶች ላይ ጥቅም ላይ ይውላል። በጥንቃቄ ማለፍ፥

- በተሰበረ መስመር ጎን ላይ ላለ ትራፊክ ይፈቀዳል።
- በድፍን መስመር በኩል ለትራፊክ አይፈቀድም።

እንዲሁም ባለ ሁለት አቅጣጫ የግራ መታጠፊያ መስመሮችን ጠርዞች ለማመልከት ጥቅም ላይ ይውላል – ድፍን መስመሮች በውጭ በኩል እና የተሰበሩ መስመሮች ከውስጥ በኩል ናቸው።



ነጠላ ነጠብጣብ - ቢጫ ወይም ነጭ

በመስቀለኛ መንገዶች ላይ መስመሮችን ይቀጥላል:: በመስቀለኛ መንገድ ላይ ያሉ አሽከርካሪዎች በመስመሩ ምልክቶች ውስጥ መቆየት አለባቸው።

ሌሎች የእግረኛ መንገድ ምልክቶች

ሌሎች የእግረኛ መንገድ ምልክቶች በአስተማማኝ ለማሽከርከር ወሳኝ ናቸው። በተጨማሪ እነሱን ማወቅ እና መረዳትም አስፈላጊ ነው.። እነሱም የሚከተሉትን ያካትታሉ፥

የማቆሚያ መስመር

ነጭ፣ ጠንካራ መስመር ተሽከርካሪው ለማቆም ወይም ለቀይ የትራፊክ ምልክት የት መቆም እንዳለበት ያሳያል።

ቅድሚያ መስጫ መስመር

ተሽከርካሪ ለሌሎች ተሽከርካሪዎች ወይም እግረኞች የት ቅድሚያ መሰጠት እንዳለበት የሚያሳዩ በመስመሩ ላይ ያሉ ትናንሽ ባል ሶስት መአዘን ረድፎች።

የቃል እና የምልክት ምልክቶች

የሚከተሉትን የሚነግርዎት ምልክቶች፥

- መስመርን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል::
- ስለ መስመር ቅነሳ (ለምሳሌ፤ መንገዱ ከሁለት መስመሮች ወደ አንድ ብቻ እየተቀየረ ነው)
- ወዴት አቅጣጫ ለመጓዝ::
- በዚያ መስመር ውስጥ እንዴት መንቀሳቀስ እንደሚችሉ ለማሳየት በቀስቶች ወይም በሌላ የቃላት መልእክቶች ጥቅም ላይ የሚውሉ ምልክቶች።
- ወደ ትምህርት ቤት አካባቢዎች እና የባቡር ማቋረጫዎች እየተቃረቡ መሆኑን የሚያስጠነቅቁ 'SCHOOL' እና 'RxR' ምልክቶች::



የእግረኛ እና የብስክሌት መንገድ ምልክት ማድረጊያዎች

አብዛኛዎቹ ብስክሌቶች ከሞተር ተሽከርካሪዎች ጋር የሚጋሯቸው የ Maryland መንገዶች፤ የተለየ የትራፊክ ምልክቶች ወይም የእግረኛ መንገድ ምልክቶች የሳቸውም። አንዳንድ መንገዶች የጋራ መጠቀሚያ መስመር ምልክቶች አሏቸው (ፎቶዎችን ይመልከቱ):: በአብዛኛው በከተሞች ውስጥ ናቸው:: እነዚህ ምልክቶች፥

- ብስክሌት ነጂዎች በመንገድ ላይ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለአሽከርካሪዎች ማስጠንቀቂያ ይሰጣሉ፤
- ለሳይክል ነጂዎች ወደ የት እንደሚነዱ ያሳውቃሉ፤ እና
- በተሳሳተ አቅጣጫ ብስክሌት መንዳትን አያበረታቱም::

አንዳንድ መንገዶች ለብስክሌት ብቻ የሆኑ መስመሮችን የሚያሳዩ የመንገድ ምልክቶች አሏቸው። ድፍን ወይም የተሰበረ ነጭ መስመሮች እነዚህን የብስክሌት መስመሮች ከሞተር ተሽከርካሪ መስመሮች ይለያሉ። የብስክሌት መስመሮችን በብስክሌት መስመር ምልክቶች ወይም በብስክሌት ምልክቶች እና ቀስቶች ምልክት ተደርጎባቸው ማየት ይችላሉ።



ትይዩ የመኪና ማቆሚያ ቦታ በሚፈቀድበት ቦታ፤ ተመሳሳይ መስመሮች የብስክሌት መስመሮችን ከተሽከርካሪ ማቆምያ መስመሮች ሊለዩ ይችላሉ።



የእግረኛ መሻገሪያ መስመሮች፤ እግረኞች የሚሻገሩበትን ቦታ የሚያሳዩ ነጭ፣ ድፍን መስመሮች ናቸው። የእግረኛ መሻገሪያዎች በነጭ፣ ድፍን መስመሮች መካከል ወይም በነሱ ምትክ ተጨማሪ መስመሮች ሊኖሯቸው ይችላል።



የዝግታ አሽከርካሪ ይሁኑ

እንደ ብሔራዊ የአውራ ጎዳና ትራፊክ ደህንነት አስተዳደር በሰዓት 65 ማይል ወይም ከዚያ በላይ የፍጥነት ወሰን ባለው መንገድ ላይ የሚደርስ አደጋ የሚከተለው ነው፥

- በ 45 ወይም በ 50 ማይል በሰዓት የፍጥነት ወሰን ባለው መንገድ ላይ፤ ከደረሰ አደጋ ይልቅ የመሞት እድሉ በእጥፍ ይበልጣል።
- በ40 ማይል በሰዓት ወይም ከዚያ በታች የፍጥነት ወሰን ባለው መንገድ ላይ ከደረሰ አደጋ ይልቅ፤ ሞትን ሊያስከትል የሚችልበት አምስት እጥፍ እድል አለው ማለት ይቻላል።

SLOW DOWN አሽከርካሪ ይሁኑ የፍጥነት ወሰኖችን እንዲያከብሩ ያሳስባል። የፍጥነት ፍላጎት ካለሎት፤ የቪዲዮ ጨዋታዎችን በመጫወት ይወሰኑ።

ቀብቶ የሚታጥቅ አሽከርካሪ ይሁኑ

በመኪና አደጋ ውስጥ ሞትን እና ከባድ ጉዳትን ለመከላከል የደህንነት ቀበቶ መታጠቅ ብቸኛው በጣም ውጤታማው መንገድ ነው። BUCKLED UP አሽከርካሪ ይሁኑ እና ቀበቶዎን ይታጠቁ – እያንዳንዱን ጉዞ፣ እያንዳንዱን ማሽከርከር፣ የፊት ወንበር ወይም የኋላ መቀመጫ የ Maryland ሹፌሮች እና ተሳፋሪዎች 90 ከመቶ ያህሉ ቀበቶዋቸውን ይታጠቃሉ፤ ግባችን ግን 100 ከመቶ ነው። በየአመቱ፤ በመቶዎች የሚቆጠሩ አሽከርካሪዎች እና መንገደኞች ቀበቶ ሳይታጠቁ በመንገዶቻችን ላይ ከባድ ጉዳት ይደርስባቸዋል ወይም ይሞታሉ። እነዚያ ሰዎች በአደጋ ጊዜ የታጠቁ ከሆነ አብዛኛዎቹን ጉዳቶች እና ሞት ማስቀረት ይቻል ነበር። ለመታጠቅ ሶስት ሰከንድ ይወስዳል ነገር ግን የህይወት ዘመን ለውጥ ሊያመጣ ይችላል።

ለበለጠ መረጃ፤ ይጎብኙ፥
ZeroDeathsMD.gov.

ክፍል 5፥ የማሽከርከር ሁኔታዎች

1. በዝቅተኛ እይታ ማሽከርከር

እይታ ማለት እንደ ተሽከርካሪዎች፣ እግረኞች፣ የመንገድ ምልክቶች፣ ማስተላለፊያዎች እና የእግረኛ መንገድ ምልክቶች ያሉ ሌሎች በዙሪያዎ ያሉትን ነገሮች በግልፅ የማየት ችሎታዎ ነው። የተቀነሰ ወይም ዝቅተኛ እይታ ማለት እነዚህን ነገሮች ማየት ከባድ ሲሆን ነው። የተለያዩ ነገሮች የእይታ መቀነስ ሊያስከትሉ ይችላሉ፤ ነገርግን በጣም የተለመዱት ጨለማ፣ ጭጋግ፣ ከባድ ዝናብ እና በረዶ ናቸው።

እይታ በሚቀንስበት ጊዜ ማሽከርከር፤ "ከተለመደው" ማሽከርከር የበለጠ ከባድ እና የበለጠ ትኩረት እና ዝግጅትን ይጠይቃል። በተቀነሰ የእይታ ሁኔታዎች ውስጥ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ያስታውሱ፥

- እንደ መመሪያ በመንገዱ ጠርዝ ወይም በቀኝ በኩል ያሉትን መስመሮች ይጠቀሙ።
- የቢጫ ንጣፍ ምልክቶች በቀኝዎ በኩል በጭራሽ መሆን የለባቸውም። ሁልጊዜ በግራ በኩል መሆን አለባቸው። ቢጫ በተቃራኒ አቅጣጫዎች የሚሄደውን ትራፊክ ለመከፋፈል ያገለግላል። የመንገዱን ግራ ጠርዝ ያመላክታል።
- ነጭ የመንገድ ምልክቶች የመንገዱን ቀኝ ጠርዝ ያመለክታሉ። በተመሳሳይ አቅጣጫ የሚጓዙትን ትራፊክም ይከፋፈላሉ።

የፊት መብራቶችዎን መቼ እንደሚጠቀሙ

የፊት መብራቶችዎን መቼ እና እንዴት እንደሚጠቀሙ ማወቅ በአስተማማኝ ሁኔታ ለማሽከርከር ወሳኝ ነው። እይታ ዝቅተኛ ሲሆን ለማየት እንዲረዳዎት የፊት መብራቶችን ይጠቀሙ። የፊት መብራቶችን መጠቀም ከፊት ለሚመጣው ትራፊክ እርስዎን ለማየት ይረዳል።

ያስታውሱ፥ መወጣጫ መንገዶች እና ድልድዮች ከመንገዶች በፊት ይቀዘቅዛሉ። እንዲሁም፤ የታረሱ መንገዶች በምሽት እንደገና ይቀዘቅዛሉ ወይም ቀን ላይ የቀለጡ በረዷማ ቦታዎች ሊኖራቸው ይችላል።

የፊት መብራትን ለመጠቀም አንዳንድ መሰረታዊ ህጎች አሉ፥

- በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ከተሽከርካሪዎ ፊት ለፊት ቢያንስ 1,000 ጫማ በግልፅ ለማየት በቂ ብርሃን በማይኖርበት ጊዜ የፊት መብራቶችዎን ማብራት አለብዎት።
- የምሽት ጊዜ፣ ጭጋጋማ ሁኔታዎች እና አውሎ ነፋሶች የፊት መብራቶችን ለመጠቀም አስፈላጊ ጊዜዎች ናቸው።
- በአስቸጋሪ የአየር ሁኔታ ውስጥ የንፋስ መከላከያ መጥረጊያዎችን ሲጠቀሙ የ Maryland ህግ የፊት መብራቶችዎን እንዲያበሩ ያስገድዳል። አስተማማኝ ያልሆነ የአየር ሁኔታ አደገኛ ሁኔታዎችን ሊያስከትል የሚችል መጥፎ የአየር ሁኔታ ነው።

ዝቅተኛ ጨረር ወይም ከፍተኛ ጨረር የፊት መብራቶች

በሚከተለው ጊዜ ዝቅተኛ ጨረሮችን ይጠቀሙ፥

- በመደበኛ የማሽከርከር ሁኔታዎች ውስጥ ማሽከርከር፣ እንደ የመንገድ መብራቶች ባሉት በመንገድ ላይ በምሽት እንደ መንዳት።
- በጭጋግ፣ በዝናብ፣ በበረዶ ወ.ዘ.ተ ማሽከርከር።
- ወደ መሿለኪያ ወይም የግንባታ ቦታ መግባት። (ህጉ ሁልጊዜ ይህንን አይጠይቅም፤ ነገር ግን ሌሎች አሽከርካሪዎች እና የግንባታ ሰራተኞች እርስዎን ለማየት ቀላል ያደርግላቸዋል።)

ሌሎች ተሽከርካሪዎችን እና ሰዎችን ለማየት እንዲችሉ የመንገድ መብራቶች በሌሉበት መንገዶች ላይ ከፍተኛ ጨረሮችን ይጠቀሙ። የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፥

- ወደ እርስዎ ወደሚመጡ ተሽከርካሪዎች ከመድረሶት ቢያንስ 500 ጫማ ቀድመው ወደ ዝቅተኛ ጨረሮች ይቀይሩ
- ከፊት ለፊትዎ 300 ጫማ ወይም ከዚያ ያነሰ ተሽከርካሪን ሲከተሉ ወደ ዝቅተኛ ጨረሮች ይቀይሩ።

2. በሌሊት ማሽከርከር

ሌሊት ማሽከርከር በቀን ከመንዳት የበለጠ አደገኛ እና ከባድ ነው። ሌሎች ተሽከርካሪዎች በምን ያህል ርቀት እንደሚገኙ እና ምን ያህል በፍጥነት እንደሚንቀሳቀሱ ለመገመት አስቸጋሪ

ነው። የፊት መብራቶችዎ እስከፈቀዱ ድረስ ብቻ ነው ማየት የሚችሉት። እርስዎም ማየት ስለማይችሉ በምሽት ተጨማሪ አደጋዎች አሉ። የት እንደሚሄዱ እና ሌሎች አሽከርካሪዎች ምን እየሰሩ እንደሆነ በግልፅ ለማየት አስቸጋሪ ያደርገዋል።

በምሽት በሚያሽከረክሩበት ጊዜ መከተል ያለብዎት አንዳንድ ምክሮች እነሆ፡-

- የፊት መብራቶችን መጠቀምዎን ያረጋግጡ እና ከፍተኛ ጨረሮችን መቼ መጠቀም እንዳለብዎት የጥቆማ አስተያየቶችን ይከተሉ።
- በተቃራኒው መስመር ወደ እርስዎ የሚመጣውን የትራፊክ መብራት አፍጥጠው አይመልከቱ። ይህ ለማየት እንዲያስቸግርዎ ያደርጋል። ይልቁንስ ከፊት ለፊትዎ ያለውን መንገድ ወይም ወደ ሚጓዙበት መስመር በትንሹ ወደ ቀኝ ይመልከቱ (የመስመሩ የቀኝ ጠርዝ ወይም የመንገዱን ጠርዝ መመልከት ይችላሉ)።
- በእርስዎ እና ከፊት ለፊት ባለው ተሽከርካሪ መካከል ያለውን ርቀት ይጨምሩ። ይህ ከፊት ለፊት ያለው ተሽከርካሪ በፍጥነት መቆም ካለበት አደጋን ለመከላከል ይረዳል።

3. ጭጋግ ውስጥ ማሽከርከር

በጭጋግ ውስጥ ለማሽከርከር ልዩ ጥንቃቄ የሚጠይቁ አንዳንድ አስቸጋሪ ነገሮች አሉ። ጭጋጋማ በሚሆንበት ጊዜ ለማሽከርከር አንዳንድ መመሪያዎች እና መስፈርቶች ከዚህ በታች አሉ፥

- መደበኛ የማሽከርከር ፍጥነትዎን ይቀንሱ።
- የፊትለፊት መብራቶችን ወይም የሌላ ተሽከርካሪን የኋላ መብራቶችን ሲመለከቱ ፍጥነትዎን የበለጠ ይቀንሱ። በፍጥነት ለማቆም ዝግጁ መሆን አለብዎት።
- ጭጋጉ በጣም ወፍራም ከሆነ ተሽከርካሪዎን በአስተማማኝ ሁኔታ ለማሽከርከር ካልቻሉ፤ ከመንገድ ላይ ሙሉ በሙሉ ወደ ደህና ቦታ ያቁሙ እና የአደጋ ጊዜ ብልጭታዎችን ያብሩ።
- ባለ ዝቅተኛ ጨረር የፊት መብራቶችን ብቻ ይጠቀሙ። እንዲሁም የጭጋግ መብራቶች ካሉዎት ይጠቀሙ።

4. በመጥፎ የአየር ሁኔታ ውስጥ ማሽከርከር

እርጥብ መንገዶች ተንሸራታች ሊሆኑ ይችላሉ፤ የሰበቃ መጠን ይቀንሳሉ እና የመጋጨትን እድል ይጨምራሉ። ሰበቃ ማለት ተሽከርካሪዎ እንዲጀምር፣ እንዲቆም እና አቅጣጫ እንዲቀይር የሚያደርግ በጎማዎ እና በመንገዱ መካከል ያለ መቆንጠጥ ነው። ጥሩ የሰበቃ ሁኔታ ሲኖርዎት ተሽከርካሪዎን በተሻለ ሁኔታ መቆጣጠር ይችላሉ።

መንገዶች በበረዶ እና/ወይም በበረድ ሲሸፈኑ አደጋዎች ይጨምራሉ። በአስቸጋሪ የአየር ሁኔታ ውስጥ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ፤ የበለጠ ትኩረት መስጠት እና በተሻለ ሁኔታ መዘጋጀት አለብዎት።

በአስቸጋሪ የአየር ሁኔታ ውስጥ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ፤ ሌሎች አሽከርካሪዎች ለሚያደርጉት ምላሽ ብቻ ሳይሆን አስቀድመው ማሰብ እና ደህንነትን ለመጠበቅ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነው። ይህ ግጭትን ለማስወገድ ይረዳዎታል። በአስቸጋሪ የአየር ሁኔታ ውስጥ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ደህንነትዎን ለመጠበቅ ማድረግ የሚችሏቸው አንዳንድ ነገሮች፥

- ደህንነቱ የተጠበቀ ርቀት ይጠብቁ - በእርስዎ እና ከፊት ለፊት ባለው መኪና መካከል የሚያስፈልገው ርቀት ከደረቅ መንገዶች ይልቅ በእርጥብ መንገዶች ላይ በጣም የላቀ ነው። መንገዱ በበረዶ ወይም በበረድ የተሸፈነ ሲሆን የበለጠ ርቀት ያስፈልግዎታል።
- ምላሽ ለመስጠት ብዙ ጊዜ እንዲኖርዎ ፍጥነትዎን ይቀንሱ።
- ጎማዎቹን የሰራው ኩባንያ በሚያቀርበው ምክር እና በተሽከርካሪዎ መመሪያዎች መሰረት፤ ጎማዎችዎ ጥሩ ጥርስ እንዳላቸው ያረጋግጡ።
- ተሽከርካሪዎ እንዲንሸራተት ስለሚያደርግ፤ ፍሬንዎን ከመምታት ይቆጠቡ። ተሽከርካሪዎ የፀረ-መቆለፊያ የፍሬን ስርዓት ከሌለው፤ መንሸራተትን ለመከላከል ፍሬኑን ይያዙ።
- መሪውን ከመንቀጥቀጥ ወይም ፍጥነትን ከመቀየር ይቆጠቡ።
- የንፋስ መከላከያ መጥረጊያዎችዎ በትክክል መስራታቸውን ያረጋግጡ።
- የፊት መብራቶችዎን ይጠቀሙ።

በበረዶ እና በበረድ ላይ ማሽከርከር

በበረዶ እና በበረድ ላይ "ሙሉ በሙሉ አስተማማኝ" ፍጥነት የሚባል ነገር የለም። በክረምት የአየር ሁኔታ፤ እያንዳንዱ መንገድ በፀሐይ፣ በጥላ፣ በመንገድ ላይ ባለው የጨው መጠን እና በሌሎች ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ሊለያይ ይችላል። የአደጋ ቦታዎችን አስቀድመው ይመልከቱ። በጥቁር (አስፋልት) መንገዶች ላይ ቀጭን የበረዶ ሽፋን ማየት በጣም ከባድ ወይም የማይቻል ሊሆን ይችላል። ይህ አንዳንድ ጊዜ ጥቁር በረድ ይባላል። በበረዶ ወይም በበረድ መቅለጥ እና እንደገና መቀዝቀዝ ይከሰታል። አደጋውን ካላወቁ ግጭትን ሊያስከትል ይችላል።

ባለአራት ጎማ ተሽከርካሪዎች በበረዶ እና በበረድ ላይ ሊንሸራተቱ ይችላሉ። በባለ አራት ጎማ ተሽከርካሪ የበለጠ ቁጥጥር ሊኖርዎት ይችላል፤ ነገር ግን በበረዶ ወይም በበረድ ላይ መንዳት ሁልጊዜ አደገኛ እና የማይታወቅ ነው። በማንኛውም ጊዜ በጣም መጠንቀቅ አለብዎት።

በበረዶ ወይም በበረድ ውስጥ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ምክሮች፥

- ፍጥነት ይቀንሱ፤ በበረዶ ወይም በበረድ በተሸፈነው መንገድ ላይ በመደበኛ ፍጥነት ማሽከርከር ለእርስዎ አስተማማኝ አያደርገውም።
- መስኮቶችዎን እና መብራቶችዎን ግልጽ ያድርጉ። ከመንዳትዎ በፊት ሁሉንም በረዶ ከተሽከርካሪዎ ያስወግዱ።
- በጣም በዝግታ ይጀምሩ፤ ከዚያ ምን ያህል ማቆም እንደሚችሉ ለማወቅ ፍሬንዎን በቀስታ ይፈትሹ።
- ወደ መስቀለኛ መንገድ ከመምጣትዎ ወይም ከመታጠፍዎ በፊት ፍጥነትዎን መቀነስ ይጀምሩ።
- የነዳጅ ጋንዎን እና የንፋስ መከላከያ ማጠቢያ ፈሳሽዎን ሙሉ ያድርጉ።
- የበረዶ ድንገተኛ አደጋ በሚታወጅበት ጊዜ ሰንሰለቶችን፣ የበረዶ ጎማዎችን ወይም ባለማዕዘን ጎማዎችን በተዘጋጁ የድንገተኛ አደጋ የበረዶ መስመሮች ላይ ይጠቀሙ።

የአደጋ ጊዜ መሳርያ አቅርቦቶች፥

በመኪናዎ ውስጥ የሚከተሉትን የሚያካትት የድንገተኛ አደጋ መሳርያ ማስቀመጥ አለበት፥

- ተቀጣጣይ
- የባትሪ ብርሃን እና ባትሪ ድንጋዮች
- የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ መሳርያዎች
- ብርድ ልብስ
- ደቃቅ ሸክላ ወይም አሸዋ (በበረዶ እና በበረድ ላይ ለሰበቃ)
- ትንሽ አካፋ እና የበረዶ መጥረጊያ

5. መንሸራተት

በጎማዎ እና በመንገዱ መካከል ያለ ሰበቃ ሁልጊዜ አንድ አይነት አይደለም። ለምሳሌ፤ አሸዋ፣ ጠጠር፣ ያልተስተካከሉ የጎዳና ንጣፎች፣ የዘይት መንሸራተቻዎች/መፍሰሻዎች፣ የፍጥነት መጨመር ወይም በመንገድ ላይ ያለው ውሃ የሰበቃ ችሎታን ይቀንሳል። ሰበቃ ሲቀንስ የመንሸራተት ወይም የመንከባበል እድሉ ይጨምራል።

ተሽከርካሪዎ መንሸራተት ከጀመረ፤ በተቻለ ፍጥነት ለመቆጣጠር ምን ማድረግ እንዳለበት ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። መሰረታዊ ህጎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፥

- ተሽከርካሪዎን እንደገና ለመቆጣጠር፤ እየተጠቀሙበት ያለውን የፍጥነት መቆጣጠሪያ (የነዳጅ መስጫ) ወይም የፍሬን መርገጫ ይልቀቁ።
- ወደ ሚንሸራተቱበት አቅጣጫ ይምሩ።
- ተሽከርካሪዎ እንዲሄድ ወደ ሚፈልጉበት ይመልከቱ።
- እንደገና ሰበቃ ከተሰማዎ በኋላ ብቻ የፍሬን መርገጫዎን ይጫኑ – ጎማዎችዎ መንገዱን እንደገና ቆንጥጠው ሲይዙ።
- የኋላ ጎማዎቹ የሰበቃ ችሎታ ካጡ ቀስ ብሎ ፍጥነትን መጨመር (ነዳጅ መስጫ ላይ መጫን) ሊረዳ ይችላል።

6. ሃይድሮፕላኒንግ (Hydroplaning)

በመንገድ ላይ ያለው ውሃ በአሽከርካሪዎች ላይ ችግር ይፈጥራል። የተሽከርካሪዎ ፍጥነት ሲጨምር እና በመንገዱ ላይ ያለው የውሃ መጠን ሲጨምር፤ በውሃ ንጣፍ ላይ ሊያሽከረከሩ ይችላሉ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ጎማዎችዎ ከመንገድ ጋር ግንኙነት ያጣሉ። ይህ "ሃይድሮፕላኒንግ" ይባላል። ሃይድሮፕላኒንግ የተሽከርካሪዎን የተወሰነ ወይም ሙሉ ቁጥጥር ሊያሳጣዎት ይችላል። ሃይድሮፕላኒንግን ለመከላከል ጎማዎችዎን በጥሩ ሁኔታ ያቆዩ፤ እና በእርጥብ መንገዶች ላይ ፍጥነትዎን ይቀንሱ። ከቁጥጥር ውጪ መሆን ከጀመሩ፥

- እግርዎን ከነዳጅ መስጫ ላይ ያንሱ።
- ፍሬንዎን አይያዙ።
- ተሽከርካሪዎ ቀጥ ብሎ እንዲሄድ ያድርጉ።
- መልሰው መቆጣጠር እስኪችሉ ድረስ ፍጥነትዎን ይቀንሱ።

7. የአውራ ጎዳና-ባቡር መንገድ ማቋረጫዎች

ያስተውሉ, ባቡሮች በፍጥነት ከጉዟቸው ማቆም አይችሉም. ስለዚህ በባቡር ማቋረጫዎች ላይ ስትጠጉ እና በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ተጨማሪ ጥንቃቄ ያድርጉ።

የባቡር -መንገድ ማቋረጫዎች ሲቃረቡ:-

- የባቡር ሀዲድ ማቋረጫዎችን ከመጠቀምዎ በፊት ሊቆሙ የሚችሉ ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ይመልከቱ። አውቶቡሶች፣ የትምህርት ቤት አውቶቡሶች እና አደገኛ ዕቃዎችን የሚጭኑ የጭነት መኪናዎች እያንዳንዳቸው የባቡር መንገድ ማቋረጫዎችን ከማቋረጣቸው በፊት በፊት መቆም በማለት መንገዳቸውን ማጤን አለባቸው።
- በማንኛውም ጊዜ ባቡር አለመኖሩን ያረጋግጡ። ባቡሮች ከየትኛውም አቅጣጫ ሊመጡ ይችላሉ, እና እነሱ ከሚታዩት በላይ ቅርብ እና በፍጥነት ሊጓዙ ይችላሉ።
- መግቢያዎች ዝግ ከሆኑ ወይም የማስጠንቀቂያ መብራቶች እየበሩ ከሆነ መንገዱ ለጊዜው ተዘግቷል። መግቢያዎቹ እስኪከፈቱ እና የማስጠንቀቂያ መብራቶች መብራት እስኪያቆሙ ድረስ ቆም ብለው ይጠብቁ።



- ባቡር ካለፈ በኋላ፣ መሻገሪያዎቹን ከመጠቀምዎ በፊት ሁለቱንም መንገዶች ይመልከቱ። ከመሻገርዎ በፊት ሁል ጊዜ መሻገሪያዎቹ ባዶ መሆናቸውን ያረጋግጡ። ሌላ ባቡር በሌላ መንገድ ሊመጣ ይችላል።
- ባቡሩ ከመድረሱ በፊት ሙሉ በሙሉ መሻገር ካልቻሉ በስተቀር መንገዱን ማቋረጥ አይጀምሩ። ከመሻገራችሁ በፊት ለተሽከርካሪዎ በሌላኛው የመሻገሪያው ክፍል ላይ ቦታ እንዳለ ያረጋግጡ።
- አጠገብ ድንገተኛ አደጋ ካጋጠመዎት ከተሽከርካሪዎ ይውጡ እና ከመንገዶቹ ይራቁ። በሰማያዊ እና በነጭ የአደጋ ጊዜ ማሳወቂያ ስርዓት (ENS) ምልክት ላይ ያለውን መረጃ በመጠቀም በባቡር ማቋረጫዎች ላይ ድንገተኛ አደጋዎችን እና የደህንነት ችግሮችን ሪፖርት ያድርጉ።

8. የስራ ቀጠና ደህንነት

.የስራ ቀጠና ማለት በግንባታ፣ ጥገና ወይም የፍጆታ ስራ የሚከናወንበት መንገድ ወይም ሀይዌይ ላይ ያለ ልዩ ቦታ ሲሆን በተለየ ሁኔታ እና በትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች ምልክቶች የተደረገበት ነው ይህ አካባቢ የትራፊክ ፍሰቱን እና ሰራተኞችን፣ ተሽከርካሪዎችን እና የተለያዩ መሳሪያዎችን አገልግሎት አቋርጦ ሊሆን ይችላል። በስራ ላይ ያሉ አካባቢዎች ጊዜያዊ ወይም የረዥም ጊዜ ሊሆኑ ይችላሉ፣ እና የተወሰኑ መንገዶች መዘጋት፣ ማዞሪያዎች እና ሌሎችም በተለመደው የትራፊክ ሁኔታ ላይ ለውጦች ሊስተዋሉ ይችላል።

በሥራ ላይ የሚሆኑ አካባቢዎች ቋሚ ሊሆኑ ይችላሉ፣ ለምሳሌ ድልድይ በሚሰፋበት ጊዜ እስኪያልቅ ድረስ አካባቢው ዝግ ይሆናል ፣ ወይም ልክ ንጣፍ በንጣፍ አንዱ ክፍል ሲያልቅ ሌላኛው የሚቀጥሉም ሊሆኑ ይችላሉ። በስራ ላይ ያሉ አካባቢዎች የማንጠብቃቸውና አስበን ተዘጋጅተን የማይመጡ ሁነቶች ፣ ለምሳሌ:-

- አዲስ የትራፊክ አመላካቾች
- ጊዜያዊ የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች (ምልክቶች፣ ኮኖች፣ በርሜሎች፣ ሲግናሎች፣ ወይም የእግረኛ መንገድ ምልክቶች)
- ጠባብ መስመሮች
- የመስመር ሽግግሮች
- የመስመር እና የመንገድ ዳርቻ መዘጋት
- የወለል ንጣፎች / ያልተስተካከሉ ወለሎች
- የተቀነሰ የእይታ ርቀት
- ተለዋጭ መንገዶች
- ቀስ በቀስ የሚንቀሳቀሱ መሳሪያዎች እና የግንባታ ተሽከርካሪዎች ወደ ትራፊክ እየተጣመሩ ሲገቡ

ብርቱካንማ ቀለም ለስራ ቀጠና መለያ ምልክት ነው። በሚያሽከረክሩበት ወቅት ከፊትለፊትዎ የብርቱካናማ ምልክቶችን ከተመለከቱ፣ ትኩረት በመስጠት ከፊት ለሚጠብቅዎ ያልተጠበቀ የመንዳት ሁኔታዎች እራስዎን ያዘጋጁ። በስራ ቀጠና መንገዶች አካባቢ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ እንደ ምልክቶች፣ ኮኖች፣ በርሜሎች፣ ሲግናሎች ወይም የእግረኛ መንገድ ምልክቶች ያሉ ጊዜያዊ የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን ይመልከቱ። በስራ ቀጠና ውስጥ በደህና ማሽከርከር እንዲችሉ ይረዳዎታል።

በስራ ቀጠናዎች የእርስዎን ደህንነት ግምት ውስጥ በማስገባት የተዘጋጁት ናቸው። በስራ ቀጠናዎች ውስጥ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ እነዚህን የደህንነት ደንቦች ይከተሉ፥

- ንቁ ይሁኑ – ለደህንነትዎ ቅድሚያ ይስጡ።
- በስራ ቀጠና ውስጥ ብልጭ ድርግም የሚሉ መብራቶች ማለት ሰራተኞች አሉ ማለት ነው። በትኩረት ሰጥተው ይከታተሉ - የስራ ቀጠና ምልክቶችን ያክብሩ፣ ፍጥነት ይቀንሱ እንዲሁም በስራ ላይ ያሉ ሰራተኞች መኖራቸውን ያጢኑ።
- ፍጥነትዎን ይከታተሉ – የተለጠፉትን የፍጥነት ወሰኖች ያክብሩ እና የፍጥነት ካሜራዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይወቁ። በሥራ ቀጥናዎች ውስጥ የፍጥነት መቀጮዎች በጣም ከፍተኛ ሊሆኑ ይችላሉ እና በስራ ላይ ያሉ ሰራተኞች ካሉ ደግሞ እጅግ ከፍ ያለ ሊሆን ይችላል። ብልጭ ድርግም የሚሉ ሰማያዊ መብራቶች አሉ ማለት የፍጥነት ካሜራዎች እየሰሩ መሆናቸውን ማመላከቻ ነው።
- ብልጭ ድርግም የሚሉ አረንጓዴ አብረቅራቂ መብራቶች የፈጣን መንገድ ጥገና የሚካሄድባቸው ተሽከርካሪ ወይም በስራ ቀጠናዎች ውስጥ እና በፊት ያሉ የአገልገሎት መሳሪያ ላይም ሊታዩ ይችላሉ።
- ያልተጠበቀውን ይጠብቁ – የስራ ቀጠና ሁኔታዎች በየጊዜው ስለሚለዋወጡ ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ ይሁኑ፣ ከፊትዎ ያለው ትራፊክ ከቆመ ሙሉ በሙሉ ማቆምን ጨምሮ።
- ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮችን ይቀንሱ - ሞባይል ስልኮችን ከመጠቀም፣ የሬዲዮ ጣቢያዎችን ከመቀየር፣ ከመብላት እና ሌሎች ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮችን ያስወግዱ።
- ሌሎችን ያክብሩ - በጥንቃቄ ይዋሃዱ፣ ተሽከርካሪዎችን ተጠግተው አያሽከርክሩ፣ እና ግዴታ ካልሆነበት በስተቀር መስመሮችን አይቀይሩ።
- የባንዲራ አቅጣጫዎችን ያክብሩ።

የስራ ቀጠናዎች መብራቶች	
አብረቅራቂ አምበር/ቢጫ መብራቶች	በስራ ላይ /ሰራተኞች ይገኛሉ
አብረቅራቂ ሰማያዊ መብራቶች	በስራ ላይ ያሉ ፍጥነት መቆጣጠሪያ ካሜራዎች አሉ
አብረቅራቂ አረንጓዴ መብራቶች	የፈጣን መንገድ በጥገና ተሽከርካሪዎች

9. የትራፊክ ክበቦች (አደባባዮች)

ወደ ትራፊክ ክበቦች የሚወስዱ መንገዶች ቅድሚያ የመስጠት ምልክት አላቸው። ወደ ትራፊክ ክበብ ሲመጡ ሁል ጊዜ በክበቡ ውስጥ ላለው ትራፊክ ቅድሚያ መስጠት አለብዎት። ልክ እንደሌሎች መስቀለኛ መንገዶች ወደ ትራፊክ ክበብ ሲቃረቡ ጥንቃቄ ያድርጉ። ወደ ትራፊክ ክበብ ሲመጡ፥



- ፍጥነትዎን ይቀንሱ።
- ክደሴቲቱ፤ በስተቀኝ ይያዙ።
- በእግረኛ መሻገሪያ ላይ እግረኞችን ይመልከቱ እና ቅድሚያ ይስጡ።
- በጥንቃቄ ወደ መስመሩ ይቅረቡ እና በትራፊክ ውስጥ ያለውን ክፍተት ይጠብቁ። ከትራፊክ አደባባዩ የሚወጡትን ተሽከርካሪዎች ይጠብቁ። በውስጡ ምንም ትራፊክ ከሌለ ወደ የትራፊክ ክበብ ለመግባት መጠበቅ አያስፈልግዎትም።

የትራፊክ አደባባዩ ከአንድ በላይ መስመር ካለው፤ በመስመርዎ ውስጥ ይቆዩ። ለመውጣት በሚዘጋጁበት ጊዜ፤ የቀኝ መታጠፊያ ምልክትዎን ያብሩ እና ለመውሰድ ካሰቡት መንገድ በፊት፤ መውጫውን ካለፋ በኋላ ወደ ውጭው መስመር ይሂዱ።

10. በግዛት መካከል መንዳት እና ውስን ተደራሽ አውራ ጎዳናዎች

“ውስን የመዳረሻ አውራ ጎዳናዎች” መስቀለኛ መንገዶች ወይም የትራፊክ መብራቶች የሌላቸው ሰፊ መንገዶች ናቸው። ወደ መንገድ የሚገቡበት እና የሚወጡባቸው፤ ውስን የሆነ ቁጥር ያላቸው ቦታዎች አሏቸው። “በግዛት መካከል” ከአንዱ ግዛት ወደ ሌላው የሚሻገር ውስን መዳረሻ ያለው የአውራ ጎዳና አይነት ነው። በሀይዌይ ላይ ካለው የትራፊክ ፍጥነት ይልቅ በቀርፋፋ እየነዱ ከሆነ በተቻለ መጠን በትክክለኛው መስመር ማሽከርከር አለብዎት።

ለሚገቡ ተሽከርካሪዎች ለሚገቡ ተሽከርካሪዎች



ወደ ግዛት መካከል እና ሌሎች ውስን የመዳረሻ አውራ ጎዳናዎች ብዙውን ጊዜ የሚደረሰው በመግቢያ መወጣጫዎች እና በፍጥነት መንገድ ነው። ወደ አውራ ጎዳናው ለመድረስ የመግቢያ መወጣጫውን ይጠቀማሉ። ቀደም ሲል ከነበረው የግዛት መካከል የትራፊክ ፍሰት ጋር ፍጥነትዎን ለማስተካከል፤ የፍጥነት መስመር ይጠቀማሉ። ወደ ግዛት መካከል ወይም ወደ ሌላ ውስን የመዳረሻ አውራ ጎዳና ሲገቡ፤ መግቢያውን እና አውራ ጎዳናውን የሚከፍሉትን ድፍን መስመሮች አያቋርጡ።

ለሚወጡ ተሽከርካሪዎች



ሊወስዱት ወዳሰቡት መውጫ ከመድረስዎ በፊት በደንብ ወደ ትክክለኛው መስመር ይግቡ። ወደ ፍጥነት መቀነሻ መስመር እንደገቡ ፍጥነት መቀነስ ይጀምሩ። የፍጥነት መቀነሻ መስመር ወደ መውጫው መወጣጫ ይመራዎታል እና ፍጥነት መቀነስ በመጀመር፤ አስተማማኝ ወደ ሆነ ፍጥነት እስኪደርሱ ጊዜ ይሰጥዎታል። ወደ ተለጠፈው የፍጥነት ወሰን ለመድረስ፤ እስከ መወጣጫው ድረስ ማቀዝቀዝዎን ይቀጥሉ። በተሳሳተ ቦታ ከወጡ፤ ከመውጫ መወጣጫው እስኪወጡ ድረስ ይቀጥሉ። ከዚያ ወደ መንገዱ እንደገና የሚገቡበትን መንገድ ይፈልጉ። በማንኛውም የአውራ ጎዳናው ክፍል ላይ በጭራሽ አያቁሙ እና ወደ ኋላ አይመለሱ።

ማቆም

ትራፊክ መጨናነቅ በሚኖርባቸው የግዛት መካከል መንገዶች ወይም በሌላ አውራ ጎዳናዎች ላይ እንዲያቆሙ አይፈቀድሎትም።

የመንገድ ዳርቻ ላይ ማቆም ይችላሉ፤ ነገር ግን ተሽከርካሪዎ ሲበላሽ (መሄድ ሲያቆም) ወይም ሌላ ድንገተኛ አደጋ ሲያጋጥም ብቻ ነው። የመንገድ ዳርቻ ላይ ማቆም ካለብዎት፤ ሌሎች አሽከርካሪዎችን ለማስጠንቀቅ እና ከቻሉ በተሽከርካሪዎ ውስጥ ለመቆየት የአደጋ ጊዜ ብልጭታዎችን ያብሩ። ትራፊክ በከፍተኛ ፍጥነት ስለሚጓዝ በግዛት መካከል ያሉ መንገዶች ውስጥ ወይም በሌላ አውራ ጎዳና ላይ መቆም ወይም መሄድ በጣም አደገኛ ነው።

11. የቀብር ስነ-ስርዓት

በቀብር ስነ-ስርዓት ላይ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ፤ የፊት መብራትዎን እና ብልጭ ድርግም የሚሉ የአደጋ መብራቶችን ማብራት አለብዎት ፤ስለሆነም ሌሎች ተሽከርካሪዎች የመንገድ ቅድሚያ መብት ይሰጡዎታል።

የቀብር ስነ-ስርዓት አካል ከሆኑ እና መብራቶቹ ካበሩ በቀይ የትራፊክ ምልክት ማለፍ ይችላሉ።

አረንጓዴ ምልክት ቢኖራቸውም ሌሎች ተሽከርካሪዎች በቀብር ስነ-ስርዓት ላይ ለተሽከርካሪዎች የመንገድ ቅድሚያ መብትን መስጠት አለባቸው። የስነ-ስርዓቱን መስመር ሳያቋርጡ በደህና መሄድ ካልቻሉ በስተቀር፤ ሁሉም በስነ-ስርዓቱ ላይ ያሉ ተሽከርካሪዎች እስኪያልፉ ድረስ ቅድሚያ መስጠት አለባቸው።

12. ቀስ ብለው የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች

በመንገድ ላይ ቀስ ብለው የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች ሊያጋጥምዎት ይችላሉ። ይህም ብስክሌቶችን፣ በፈረስ የሚጎተቱ ተሽከርካሪዎች እና የእርሻ ተሽከርካሪዎችን ይጨምራል። አንዳንዶቹ በሰዓት 25 ማይል ብቻ ወይም ከዚያ ባነሰ እየሄዱ መሆናቸውን ለማስጠንቀቅ በተሽከርካሪያቸው ጀርባ ላይ በዝግታ የሚንቀሳቀስ ምልክት (የሚታይ) ሊኖር ይችላል።

በዝግታ ከሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች አጠገብ ለመንዳት አንዳንድ ጠቃሚ ምክሮች እነሆ፥

- ማናቸውንም በጣም በዝግታ ፍጥነት ሊጓዙ የሚችሉ ተሽከርካሪዎችን በጽኑ ይገንዘቡ።
- አስፈላጊ ከሆነ የተሽከርካሪዎን ፍጥነት እና ቦታ ይለውጡ።
- አስተማማኝ ሲሆን ብቻ፤ በዝግታ የሚንቀሳቀሰውን ተሽከርካሪ ይለፉ።

አስተማማኝ ጊዜ ለመጠብቅ በዝግታ የሚንቀሳቀሰውን ተሽከርካሪ መከተል ካለብዎት፤ ሌሎች ከእርስዎ በኋላ የሚመጡትን ለማስጠንቀቅ የእርስዎን የአደጋ ጊዜ ብልጭታ ይጠቀሙ።

ክፍል 6፥ አደገኛ የመንዳት ባህሪያት

1. አልኮሆል፣ አደንዛዥ ዕፅ እና ማሽከርከር

ሰክሮ ማሽከርከር ወይም በአደንዛዥ እጽ ማሽከርከር ለሁሉም ሰው ደህንነት በጣም ከባድ አደጋ ነው። አልኮሆል እና አደንዛዥ እጾች የማሽከርከር ችሎታዎን ይቀንሳሉ። ይህ ማለት በአስተማማኝ ሁኔታ ለማሽከርከር በጣም አስቸጋሪ ወይም የማይቻል ያደርገዋል ማለት ነው።

የደም አልኮል ሙጅረት (Blood alcohol concentration) (BAC) በደምዎ ውስጥ ያለው የአልኮሆል መጠን መለኪያ ነው። Maryland አሽከርካሪዎች በአልኮል መጠጥ ተጽእኖ ስር እያሽከረከሩ እንደሆነ የሚያስበው፤ የደማቸው አልኮሆል መጠን .08 ወይም ከዚያ በላይ ሲሆን ነው።

ምንም እንኳን የ Maryland ሰክሮ የማሽከርከር ወሰን .08 ቢሆንም፤ ማንኛውም የአልኮል መጠን ተሽከርካሪን በአስተማማኝ ሁኔታ የማሽከርከር ችሎታዎ ላይ ተጽኖ ሊያረግ ይችላል። በጣም ባነሰ BAC፤ የእርስዎ ግምት እና አካላዊ ቅንጅት ሊዳከም ይችላል እና የወንጀል ክስ ሊያስከትል ይችላል። ለምሳሌ፤ የእርስዎ እይታ፣ ቀላል እንቅስቃሴዎችን የማድረግ ችሎታ እና የአጸፋ ምላሽ ጊዜ በአንድ መጠጥ ብቻ ሊጎዳ እና የአደጋ ስጋትን ሊጨምር ይችላል።

የራስዎን BAC ወይም አልኮል ምን ያህል የማሽከርከር ችሎታዎ ላይ ተጽእኖ እንዳለው ማወቅ በጣም ከባድ ነው። የጠጡትን መጠጥ ብዛት በቀላሉ ማወቅ አይችሉም፤ ምክንያቱም ሰውነትዎ አልኮልን በሚያዋህድበት መንገድ ላይ ብዙ ነገሮች ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ። ይህም የእርስዎን ክብደት፣ የሰውነትዎን ስብ መጠን፣ ከምን ያህል ጊዜ በፊት እንደበሉ እና ምን ያህል እንደበሉ ያጠቃልላል። እንዲሁም፤ የድካምዎ መጠን፣ ስሜትዎ እና መድሃኒቶች፤ አልኮል የማሽከርከር ችሎታዎ ላይ ያለው ተጽእኖ ላይ ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ።

ከ 21 ዓመት በታች – አልኮል አይፈቀድም

ገና 21 ዓመት ካልሆኖት፤ ማንኛውንም አልኮል መጠጣት በህግ የተከለከለ ነው። የህግ አስከባሪ አካላት ካቆምዎት እና መጠጥ ጠጥተው ከነበረ፤ ፍቃድዎት ይታገዳል ወይም ይሰረዛል። ያ ከሆነ፤ ማሽከርከር አይፈቀድልዎትም። በተጨማሪም፤ በፈቃድዎ ላይ ያለውን የአልኮል ገደብ በመጣስ ሊከሰሱ ይችላሉ።

ክፍት የአልኮል መያዣ እቃ

በተሽከርካሪው ውስጥ ተሳፋሪ አካባቢ በተከፈተ የአልኮል መያዣ እቃ ጋር ማሽከርከር በህግ የተከለከለ ነው። ክፍት መያዣ እቃ፤ ማንኛውም ክፍት ቆርቆሮ፣ ጠርሙስ፣ ሌላ ዓይነት መያዣ ወይም ማሸጊያ ነው። ክፍት፣ ባዶ ወይም የጎደሉ ጠርሙሶች/ቆርቆሮዎች ያሉት ባለ ስድስት-ጥቅል አልኮሆል እንደ ክፍት ዕቃ ሊቆጠር ይችላል።

የተሽከርካሪው የተሳፋሪ ቦታ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፥

- የአሽከርካሪ እና የተሳፋሪ መቀመጫዎች።
- አሽከርካሪው ወይም ተሳፋሪዎች ከተቀመጡበት ቦታ በቀላሉ መድረስ የሚችሉበት ቦታ።

ቁጥጥር የሚደረግባቸው አደገኛ ንጥረ ነገሮች (Controlled Dangerous Substances) (CDS) – ህገወጥ እና በሐኪም የታዘዙ መድሃኒቶች

ህገወጥ መድሃኒቶች፣ አንዳንድ በሐኪም የታዘዙ መድሃኒቶች እና የሚተነፈሱ ኬሚካሎች በአስተማማኝ ሁኔታ የመንዳት ችሎታዎ ላይ በእጅጉ ተጽእኖ ያሳድራሉ። በእርስዎ ንቃት፣ ትኩረት፣ ቅንጅት እና ምላሽ ጊዜ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ። ሁሉም መድሃኒቶች ርቀቶችን መገመትን እና በመንገድ ላይ ላሉ ምልክቶች እና ድምፆች ምላሽ መስጠትን አስቸጋሪ ያደርጋሉ ። በአደገኛ ንጥረ ነገሮች ቁጥጥር ስር ሆነው ካሽከረከሩ ፍቃድዎ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል።

በሀኪም ማዘዣ እና ያለሀኪም ማዘዣ በሚወሰዱ መድሀኒቶች ላይ ያሉ ማስጠንቀቂያዎችን በትኩረት ማጤን አስፈላጊ ነው። መድሀኒቶችን በሚወስዱበት ጊዜ መኪና እንዳያሽከረክሩ ወይም ከባድ ማሽኖችን እንዳይጠቀሙ የሚነግሩዎትን ማስጠንቀቂያዎች ይፈልጉ። አያሽከርክሩ የሚል መድሃኒት ከወሰዱ እና በአስተማማኝ ሁኔታ የመንዳት ችሎታዎን የሚቀንስ መድሃኒት ከወሰዱ በወንጀል ሊከሰሱ ይችላሉ።

ከልጆች ጋር ማሽከርከር

በተሽከርካሪዎ ውስጥ ልጅ አሳፍረው፤ ሰክረው ወይም አደንዛዥ ዕፅ ተጠቅመው በማሽከርከር ወንጀል ከተከሰሱ፤ ዳኛው የመቀጫ እና የእስር ጊዜዎን በእጥፍ ሊጨምር ይችላል።

2. በሞገደኛነት ማሽከርከር እና የመንገድ ቁጣ

በሞገደኛነት ማሽከርከር ምሳሌዎች፥ በፍጥነት ማሽከርከር፣ ተሽከርካሪዎችን ተጠግተው ማሽከርከር፣ የትራፊክ ምልክቶችን እና መሳሪያዎችን ችላ ማለት፣ ደህንነቱ ያልተጠበቀ የመስመር ለውጥ ማድረግ፣ የመንገድ ቅድሚያ



ለመጠጣት ካቀዱ፤ ላለማሽከርከር ያቅዱ።

መብት አለመስጠት፣ እና ደህንነቱ ባልተጠበቀ ወይም ህገወጥ በሆነ መንገድ ማለፍ። የተጨናነቁ መንገዶች፣ ያልተጠበቁ መጓተቶች፣ ጥድፊያ፣ የመንገድ ግንባታ እና ጭንቀት ሰዎች በሞገደኝነት እንዲያሽከረክሩ ያደርጋቸዋል።

መንገዱን የሚጠቀሙትን ሁሉ ማክበር እና መተባበር አለቦት። ሁሉንም ሰው ለመጠበቅ እና አደጋዎችን ለማስወገድ ሁሉንም ህጎች መከተል አለብዎት። በሞገደኝነት የማሽከርከር አጋጣሚ ውስጥ የመሳተፍን እድል ለመቀነስ አንዳንድ ምክሮች የሚከተሉትን ያካትታሉ፥

- ለመጓዝ ተጨማሪ ጊዜ ይፍቀዱ።
- ታጋሽ ይሁኑ።
- ትሁት ይሁኑ።
- በማሽከርከር ባህሪዎ ላይ ያተኩሩ።
- ሁል ጊዜ ፍላጎትዎን ያሳውቁ። (የመዞሪያ ምልክቶችን በመጠቀም ለሌሎች አሽከርካሪዎች ምን ለማድረግ እንዳሰቡ ያሳውቁ።)
- ሁሉንም የትራፊክ ህጎች፣ ምልክቶች፣ ማስተላለፊያዎች እና የእግረኛ መንገዶችን ያክብሩ።
- የመንገድ ቅድሚያ መብት ይስጡ።
- ከሌሎች አሽከርካሪዎች ጋር መወዳደርን ያስወግዱ።

3. በመዘናጋት ማሽከርከር

በአስተማማኝ ሁኔታ ለማሽከርከር ትኩረት መስጠት በጣም ጠቃሚ እና አስፈላጊ ነው። ስለ መንገዱ እና በዙሪያዎ ስላሉት ሌሎች ተሽከርካሪዎች ያለማቋረጥ መገንዘብ አለብዎት። ንቁ እና አደጋን ማስወገድ የሚችሉ ይሁኑ። ሌሎች ተሽከርካሪዎች ከፊት፣ ከኋላ እና ከእርስዎ ቀጥሎ የት እንዳሉ ያለማቋረጥ ያረጋግጡ።

"በመዘናጋት ማሽከርከር" አይኖችዎን፣ እጆችዎን ወይም በተለይም አእምሮዎን ከመንዳት ሲያርቁ ነው። በመዘናጋት ማሽከርከር ከምንም ነገር በላይ ለፖሊስ ሪፖርት የሚደረጉ ብዙ አደጋዎችን ያስከትላል። ማንኛውም የሚያዘናጋ ነገር፤ አደጋዎች እንዳይከሰቱ ሚያግዙ ነገሮችን እንዳያዩ እና እንዳይሰሙ ያደርግዎታል።

ብዙ እንቅስቃሴዎች በመዘናጋት ለማሽከርከር አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። አንዳንድ ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፥

- መብላት እና መጠጣት።
- ሬዲዮን ወይም ሌላ የሙዚቃ ምንጭ ማስተካከል።
- GPS ማስተካከል ወይም መሙላት።
- ከልጆች እና ከቤት እንስሳት ጋር ግንኙነት።
- በተሽከርካሪው ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ያልታሰሩ እቃዎች።
- በሞባይል ስልክ ማውራት እና መልእክት መላክ።
- ማጨስ።
- ሜካፕ መቀባት።
- መላጨት።
- ማንበብ።
- በተሽከርካሪው ውስጥ ከሌሎች ጋር መስተጋብር መፍጠር።

ሞባይሎች

በሚያሽከረክሩበት ወቅት የጽሑፍ መልእክትን ጨምሮ በእጅ የሚያዝ ሞባይል መጠቀም ሕገወጥ ነው። ይህ ማለት ስልክዎን በመያዝ መጠቀም አይችሉም ማለት ነው። በሚያሽከረክሩበት ጊዜ፤ ስልክዎን ሳይዙ (ከእጅ ነጻ) ለጥሪዎች መጠቀም ይችላሉ። ይህንን ካደረጉ፤ በተቻለ መጠን በትንሹ ሊጠቀሙበት ይገባል እናም ደህንነትዎን ለመጠበቅ የሚከተሉትን ያድርጉ፥

- የሞባይል ስልክዎን ለድንገተኛ ጊዜ ብቻ ይጠቀሙ፤ ከተቻለ፤ ተሳፋሪ እንዲደውል ያድርጉ።
- መደወል ካለብዎት፤ ከመንገድ ላይ ቀስ ብለው በመውጣት፤ እና ከመደወልዎ በፊት ያቁሙ።
- የድምጽ መልእክትዎ ገቢ ጥሪዎችን እንዲመልስ ያድርጉ።
- የስልክ ንግግሮችዎን አጭር ያድርጉ።

ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ፤ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ሞባይል ስልክ መጠቀም አይችሉም፤ ከእጅ ነጻም ቢሆን። ብቸኛው ልዩነት፤ ለ 911 የአደጋ ጊዜ ጥሪ ለማድረግ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

4. በድብታ መንዳት

በቂ እንቅልፍ አለማግኘትም ደህንነቱ ያልተጠበቀ ማሽከርከርን ያስከትላል። እንቅልፍ ልክ እንደ አደንዛዥ እጽ ወይም አልኮል የግብረመልስ ጊዜን ይቀንሳል፤ ግንዛቤን ይቀንሳል እና ውሳኔን ያበላሻል። ይህ በአደጋ ውስጥ የመሳተፍ እድሎዎን በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራል።

ጥሩ አጠቃላይ ህግ ሌሎች አሽከርካሪዎችን እና የመንገድ ተጠቃሚዎችን፤ እርስዎ መስተናገድ እንደሚፈልጉት አድርገው ማስተናገድ ነው።

አንዳንድ አሽከርካሪዎች ለእንቅልፍ ስሜት የመጋለጥ እድላቸው ከፍ ያለ ነው። ለምሳሌ በየቀኑ ብዙ ኪሎ ሜትሮችን የሚያሽከረክሩትን፣ የእንቅልፍ ችግር ያለባቸውን እና አንዳንድ መድሃኒቶችን የሚወስዱ ሰዎችን ያጠቃልላል።

ድብታ ውስጥ መሆንዎን የሚያሳዩ ምልክቶችን ማወቅ እና አደጋ እንዳይፈጠር እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነው። ከታች የተለመዱ “የአደጋ ምልክቶች” ዝርዝር እና በእንቅልፍ ስሜት ማሽከርከርን ለመቋቋም ጥሩ መመሪያ አለ።

እንቅልፍ የሚጫጫናቸው ሾፌሮች አደገኛ ምልክቶች

የሚከተሉት በእንቅልፍ ስሜት ውስጥ ነዎት እና ደህንነትዎን ለመጠበቅ እርምጃ መውሰድ ያለብዎት መሆኑን ያሳያሉ፥

- ዓይኖችዎ ይዘጋሉ ወይም ከትኩረት ውጭ ይሆናሉ።
- ጭንቅላትዎን ከፍ ለማድረግ ይቸገራሉ።
- ማዛጋት ማቆም አይችሉም።
- የሚንከራተቱ፣ ያልተገናኙ ሀሳቦች አሉዎት።
- የመጨረሻዎቹን ጥቂት ማይሎች ማሽከርከርዎን አያስታውሱም።
- መውጫዎት አምልጥዎታል።
- ከመንገድዎ ውጪ ማሽከርከርዎን ቀጥለዋል።
- ፍጥነትዎን በተደጋጋሚ ይቀያይራሉ።

በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ከደከሙ ወይም እንቅልፍ ከተሰማዎት፤ ዕረፍት ቢያደርጉ ወይም አሽከርካሪ ቢቀይሩ ይመረጣል። ድካም አእምሮዎን ያደበዝዛል እና ግበረመልስዎን ያቀዘቅዘዋል፤ ማሽከርከርን በጣም አደገኛ ያደርገዋል።

የትኩረት አሽከርካሪ ይሁኑ

አንድ ሶስተኛው ገዳይ የሆኑ አደጋዎች የሚከሰቱት በመዘናጋት በማሽከርከር ነው። የሞባይል ስልክ አጠቃቀም፤ በመዘናጋት ለማሽከርከር አንዱና ዋነኛው መንስኤ ነው። ነገር ግን፤ ሌሎች በመዘናጋት እንዲያሽከረክሩ በማድረግ ትኩረቶትን ከማሽከርከር ላይ የሚያነሱ ነገሮች ውስጥ መብላት፣ ሜካፕ መቀባት፣ ከልጆች ጋር ግንኙትት ማድረግ እና የሬዲዮ ጣቢያዎችን መቀየር ይገኙበታል። ትኩረት የሚከፋፍሉ ነገሮችን የሚከላከል እና በያዘው ተግባር ላይ FOCUSED አሽከርካሪ ይሁኑ – ማሽከርከር።

በእቅድ የሚያሽከረክር አሽከርካሪ ይሁኑ

በየአመቱ፤ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ጠጥተው ወይም አደንዛዥ እፅ ተጠቅመው በ Maryland መንገዶች በማሽከርከር ይታሰራሉ። አልኮሆል እና አደንዛዥ እጾች እንደተለመደው የማሽከርከር ችሎታዎ ወይም በብዙ አጋጣሚዎች እንደሚታየው፤ በአጠቃላይ የማሽከርከር ብቃትዎ ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ።
ከመውጣትዎ በፊት MAKE A PLAN አሽከርካሪ ይሁኑ እና በሰላም ወደ ቤትዎ ለመግባት እቅድ ያውጡ፤ እና የማይጠጣ አሽከርካሪ ይሹሙ። ጉድለት ባለበት ማሽከርከር ምክንያት መታሰር ትልቅ ቅጣት፣ የእስር ጊዜ እና በሺዎች የሚቆጠሩ የፍርድ ቤት ወጪዎችን ጨምሮ ከባድ መዘዞች አሉት። ከሁሉ የሚከፋው፤ ጉድለት ያለበት ማሽከርከር ብዙ ጊዜ ከባድ የአካል ጉዳት ወይም ሞት ያስከትላል፤ ሁለቱንም መልካም ውሳኔዎችን በማድረግ ማስቀረት ይቻላል።

ለበለጠ መረጃ፤ ይጎብኙ፥
ZeroDeathsMD.gov.

ክፍል 7፡ መንገዱን መጋራት

1. ለእግረኛ የመንገድ ቅድሚያ መስጠት

እግረኞች በመንገድ ማቋረጫዎች ላይ የመሄጃ መብት አላቸው፤ ነገርግን የትራፊክ መቆጣጠሪያ ምልክቶችን መታዘዝ አለባቸው። የትራፊክ ምልክት በማይኖርበት ጊዜ፤ ምልክት ባለው ወይም ምልክት በሌለው የእግረኛ መሻገሪያ ላይ ለእግረኞች ማቆም አለብዎት።

አሽከርካሪዎች በተለይ መስማት ለተሳናቸው፣ ማየት ለተሳናቸው ወይም የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው እግረኞች ንቁ መሆን አለባቸው። ትራፊክን የማየት ወይም የመስማት ችግር ሊኖርባቸው ይችላል እና መንገዱን ለማቋረጥ ተጨማሪ ጊዜ ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

በእግረኛ መሻገሪያ ማቋረጥ

የእግረኛ መሻገሪያ እግረኞች መንገድ የሚያቋርጡበት እና እንዲሻገሩ ለማድረግ አሽከርካሪዎች ማቆም ያለባቸው ቦታ ነው። አንዳንድ የእግረኛ መንገዶች በእግረኛ መንገድ ላይ ምልክት ተደርጎባቸዋል፤ ሌሎቹ ግን አልተደረጉም ብዙ መስቀለኛ መንገዶች ምልክት ባይደረግበትም የእግረኛ መንገድ አላቸው።

አንዳንድ መሰረታዊ ህጎች፥

- የትራፊክ ምልክት ሲኖር፤ አሽከርካሪዎች እና እግረኞች መታዘዝ አለባቸው።
- በእግረኛ መሻገሪያ ላይ የቆመን ማንኛውንም ተሽከርካሪ ማለፍ አይችሉም።
- አረንጓዴ ምልክት ሲያበሩ ለእግረኞች ቅድሚያ መስጠት አለብዎት።
- ከቆሙ በኋላ፤ ቀይ ምልክት ማብራት ሲፈቀድ ለእግረኞች ቅድሚያ መስጠት አለብዎት።

ያስታውሱ፣ የጭነት መኪናን መስተዋት ማየት ካልቻሉ፤ የጭነት መኪናው አሽከርካሪ ሊያይዎት አይችልም!

2. የአደጋ ጊዜ ተሽከርካሪዎች

እንደ ፖሊስ መኪና፣ አምቡላንስ እና የእሳት አደጋ መከላከያ ሞተሮች ያሉ የአደጋ ጊዜ ተሽከርካሪዎች፤ ሳይሪን እና ብልጭ ድርግም የሚሉ መብራቶችን ሲጠቀሙ የመንገድ ቅድሚያ መብት አላቸው። ምልክቶችን እየተጠቀመ የሚመጣን የድንገተኛ አደጋ መኪና ካዩ ወይም ከሰሙ በኋላ ወዲያውኑ፥

- በተቻለ መጠን ወደ መንገዱ ጠርዝ ይቅረቡ።
- ከመስቀለኛ መንገዶች ውጭ ይቆዩ፤ እና
- የድንገተኛ አደጋ መኪና እስኪያልፍ ድረስ ቆመው ይጠብቁ።

የድንገተኛ አደጋ መኪና ምልክቶችን ተጠቅሞ ወደሚሄድበት አቅጣጫ የሚሄዱ ከሆነ፤ ካልቆመ ወይም የፖሊስ መኮንን እንዲያልፉ ካልነገርዎት በስተቀር ማለፍ አይችሉም።

ወደ ድንገተኛ አደጋ መኪና፣ ጎታች መኪና ወይም በመንገድ ላይ የቆመ ሌላ አገልግሎት ሰጪ ተሽከርካሪ እየተጠጉ ከሆነ፤ ከቆመው ተሽከርካሪ አጠገብ (ቀጥሎ) ወዳልሆነ መስመር መሄድ አለብዎት። ለመሻገር የማይቻል ከሆነ፤ ወደ አስተማማኝ ፍጥነት መቀነስ እና አስፈላጊ ከሆነም ለማቆም መዘጋጀት አለብዎት።

3. ትላልቅ መኪናዎች እና አውቶቡሶች

የሚዞሩ የጭነት መኪናዎችን የመልከቱ። የጭነት መኪኖች በመስቀለኛ መንገድ ላይ አስፍተው ስለሚዞሩ፤ የበለጠ ቦታ ያስፈልጋቸዋል። ወደ ቀኝ ሲዞሩ፤ ትላልቅ መኪኖች ከመታጠፋቸው በፊት ብዙ ጊዜ ወደ ግራ ይንቀሳቀሳሉ። እርሶ፤ መስመሮችን እየቀየሩ ንደሆነ አስበው፤ በቀኝ በኩል ለማለፍ ይሞክሩ ይሆናል። ማንኛውንም የጭነት መኪና በቀኝ በኩል ማለፍ አደገኛ ሊሆን ይችላል። መኪናው ከማለፉ በፊት ለመታጠፍ እያቀደ መሆኑን ለማየት ይጠብቁ። አንድ የጭነት መኪና መስቀለኛ መንገድ ላይ ሲቆም ወይም ሲቃረብ፤ በቀኝ በኩል ለመቁረጥ በጭራሽ አይሞክሩ፤ ምክንያቱም የከባድ መኪናው አሽከርካሪው መዞር ስለሚጀምር። በሚዞረው መኪና እና በመንገዱ ኩርባ መካከል እራስዎን ተቀርቅረው ሊያገኙት ይችላሉ።

በተመሳሳይ አቅጣጫ የሚሄድ የጭነት መኪና በሚያልፉበት ጊዜ፤ በዙሪያዎ ያለውን ነገር ማየትዎን መቀጠል እንዲችሉ በፍጥነት ይለፉ። ከዚያም፤ የጭነት መኪናውን ሁለቱንም የፊት መብራቶች በኋላ መመልከቻ መስታወትዎ ማየት ሲችሉ ብቻ፤ ወደ መስመር ይመለሱ።

ብዙ መስቀለኛ መንገዶች በማቆሚያ መስመሮች ምልክት ተደርጎባቸዋል። የማቆሚያ መስመሩን አልፈው ከቆሙ፤ ተሽከርካሪዎ ከመስቀለኛ መንገድ በሚዞሩ መኪኖች መንገድ ላይ ሊሆን ይችላል። በጭነት መኪና ፊት በፍጹም አይቁረጡ። ሙሉ በሙሉ የተጫኑ መኪኖች ከ 80,000 ፓውንድ በላይ ይመዝናሉ፤ እና ለማቆም የእግር ኳስ ሜዳን የሚያክል ርዝመት ይወስዳሉ። አብዛኞዎቹ መኪኖች ክብደታቸው 2,000 ፓውንድ ብቻ ነው።

No-Zones

በጭነት መኪናዎች ዙሪያ አራት ትላልቅ “ከእይታ ውጪ” የሆኑ፤ ሌሎች ተሽከርካሪዎች ከእይታ “የሚሰወሩበት” ቦታዎች አሉ። ይህ ማለት የከባድ መኪና አሽከርካሪ እርስዎን ማየት አይችልም ማለት ነው። እነዚህ ከእይታ ውጪ ቦታዎች “no zones” ይባላሉ።



- **የጎን No-Zones፦** የጭነት መኪናዎች እና አውቶቡሶች በሁለቱም በኩል ከእይታ ውጪ የሆኑ ቦታዎች አሏቸው። የጎን መመልከቻ መስታወታቸው ውስጥ የአሽከርካሪውን ፊት ማየት ካልቻሉ፤ እርስዎን ማየት አይችሉም። የጭነት መኪናው መስመሮችን ከቀየረ፤ ከእይታ ውጪ ውስጥ ከሆኑ ችግር ሊያጋጥምዎት ይችላል። በቀኝ በኩል ያለው ከእይታ ውጪ የሆነ ቦታ የጭነት መኪናውን ተጎታች ርዝመት ያክላል እና እስከ ሶስት መስመሮች ይሰፋል።
- **የኋላ No-Zones፦** ተሽከርካሪዎችን ተጠግተው ከማሽከርከር ይቆጠቡ (ከፊትዎ ካለው ተሽከርካሪ ጀርባ በጣም በቅርብ መንዳት)። ከመኪናዎች በተለየ፤ የጭነት መኪናዎች እና አውቶቡሶች በቀጥታ ከኋላቸው ትልቅ No-Zones አላቸው። የጭነት መኪና ወይም የአውቶቡስ አሽከርካሪ፤ ከኋላ ያለ ተሽከርካሪዎን ማየት አይችሉም። መኪናው ወይም አውቶቡሱ በድንገት ከቀዘቀዘ ወይም ከቆመ፤ የሚሄዱበት ቦታ የሎትም።
- **የፊት No-Zones፦** የጭነት መኪና ወይም አውቶብስ ካለፉ በኋላ፤ ብዙም ሳይቆይ ወደ ፊትለፊታቸው አይንቀሳቀሱ። የከባድ መኪና እና የአውቶቡስ አሽከርካሪዎች፤ ለማቆም ከመኪና በእጥፍ የሚበልጥ ጊዜ እና ቦታ ያስፈልጋቸዋል። ከፊት ከመግባትዎ በፊት የአውቶቡሱን ወይም የጭነት መኪናውን ሁለቱንም የፊት መብራቶች በኋላ መመልከቻ መስታወቶት ይመልከቱ፤ እና ፍጥነትዎን አይቀንሱ።
- **ወደ ኋላ የመመለስ No-Zones፦** ወደ ኃላ ከሚመለስ የጭነት መኪና ጀርባ በጭራሽ አይሻገሩ። ወደ ኃላ የሚመለሱ የጭነት መኪናዎችን ችላ በማለት በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በየዓመቱ ይሞታሉ ወይም ይጎዳሉ። የከባድ መኪና አሽከርካሪዎች የኋላ መመልከቻ መስታወት የላቸውም እና ከኋላቸው ሲገቡ ላያዩዎት ይችላሉ።

4. የትምህርት ቤት አውቶቡሶች

አሽከርካሪዎች ለትምህርት ቤት አውቶቡሶች መቆም አለባቸው።

አንድ የትምህርት ቤት አውቶቡስ በሚያብረቀርቁ ቀይ መብራቶች በመንገዱ ላይ ቆሞ ከሆነ፤ ወደ እሱ ሲጠጉ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፦

- ከትምህርት ቤቱ አውቶብስ ጀርባ ቢያንስ 20 ጫማ ርቀው ያቁሙ፤ ከኋላው ካሉ።
- ከትምህርት ቤቱ አውቶቡስ ፊት ለፊት ቢያንስ 20 ጫማ ርቀው ያቁሙ፤ ከፊቱ ካሉ።

የትምህርት ቤቱ አውቶቡስ መንቀሳቀስ እስኪጀምር ወይም የሚያብረቀርቁ ቀይ መብራቶቹን እስኪያጠፉ ድረስ እንደገና መንቀሳቀስ ላይጀምሩ ይችላሉ።

በአካል በተጋረደ ባለብዙ መስመር መንገድ ላይ ከሆኑ፤ አውቶቡሱ ከግርዶሹ ማዶ ከሆነ አያቁሙ።

5. ሞተር ሳይክሎች

የሞተር ሳይክል ነጂዎች በመንገድ ላይ እንደሌሎች አሽከርካሪዎች ተመሳሳይ መብቶች እና ግዴታዎች አሏቸው። ነገር ግን የሞተር ሳይክል ነጂ ከመኪና አሽከርካሪ ይልቅ በአደጋ ጊዜ የመጎዳት እድሉ በስድስት እጥፍ ይበልጣል። ሞተር ሳይክሎች ከመኪኖች እና ከጭነት መኪናዎች ያነሱ ናቸው፤ ስለዚህ ፍጥነታቸውን እና ርቀታቸውን ለመገመት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል።

- **ወደ ግራ በሚታጠፉበት ጊዜ፣ ለሚመጣ ሞተር ሳይክል የመንገዱን ቅድሚያ መብት ይስጡ።** ለሞተር ሳይክል ነጂ የመንገድ ቅድሚያ መብትን መስጠት ካልቻሉ፤ ጉልህ የሆነ ቅጣት ሊያገኙ እና ከባድ ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ። ከሞተር ሳይክሎች ጋር በተያያዘ የሚደርሱ የመኪና ግጭቶች፤ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የአሽከርካሪዎች ጥፋት ነው።
- **መስመሮችን ከመቀየርዎ ወይም ወደ ትራፊክ ከመቀላቀልዎ በፊት ሁለት ጊዜ ይመልከቱ።** መስመሮችን ከመቀላቀልዎ ወይም ከመቀየርዎ በፊት ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን እርግጠኛ ለመሆን መስተዋቶችዎን ይጠቀሙ እና ትከሻዎን ይመልከቱ። ሞተርሳይክሎች ያነሱ በመሆናቸው ከእይታ ውጪ የሆኑ ቦታዎች ውስጥ ሊደበቁ ወይም በፈጣን እይታ ውስጥ ሊጠፉ ይችላሉ።
- **መስመሮችን ከሞተር ሳይክል ጋር አይጋሩ።** ሞተር ሳይክል ነጂዎች እንደ ጉድጓዶች ወይም ዘይት ፍሰት፣ በነፋስ ሳቢያ እና በሌሎች ዘንድ እንዲታዩ የመንገድ አደጋዎችን ለማስወገድ ብዙ ጊዜ በትራፊክ መንገድ ይንቀሳቀሳሉ። ሞተርሳይክል ነጂዎች ሙሉውን መስመር እንዲጠቀሙ ተፈቅዶላቸዋል።
- **ወደ ሞተር ሳይክል "ተጠግተው አያሽከርክሩ" (በጣም ቅርብ በሆነ መንገድ አያሽከርክሩ)።** በተሽከርካሪዎ እና በፊትዎ ባለው ሞተርሳይክል መካከል ቢያንስ ከ 3 እስከ 4 ሰከንድ ርቀት ይተዉ። ሞተር ሳይክሎች እንደ ጠጠር፣ እርጥብ መንገዶች፣ ወይም የባቡር ማቋረጫዎች የመሳሰሉ፤ በመኪናዎች ላይ በተመሳሳይ መልኩ ተጽእኖ ሊያሳድሩ በማይችሉ፤ የመንገድ አደጋዎች ፍጥነት መቀነስ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ሞተር ሳይክሎች ብዙውን ጊዜ የፍሬን መብራቶቻቸውን በማያበሩ መንገዶች ፍጥነትን ይቀንሳሉ። ስለዚህ፤ ንቁ ይሁኑ እና በሞተር ሳይክሎች ዙሪያ ብዙ ርቀት ይተዉ።
- **በሚያልፉበት ጊዜ በተሽከርካሪዎ እና በሞተር ሳይክልዎ መካከል ብዙ ርቀት ይተዉ።** ከሚያልፍ መኪና የሚነሳው ንፋስ ሞተር ሳይክልን ሊጎዳ ይችላል። ሞተር ሳይክል ነጂውን ካለፉ በኋላ፤ ወደ መስመርዎ ከመመለስዎ በፊት የሞተር ብስክሌቱን የፊት መብራቱን በኋለኛው መመልከቻ መስታወትዎ ላይ ማየት እንደሚችሉ ያረጋግጡ። ሞተር ሳይክል ነጂ እርስዎን እያሳለፈ ከሆነ፤ በቀላሉ ፍጥነትዎን ይጠብቁ እና ማለፋቸውን እንዲያጠናቅቁ ይፍቀዱላቸው።
- **የቡድን ሞተር ሳይክል ነጂዎች አጠገብ ሲነዱ ይጠንቀቁ።** ሞተር ሳይክል ነጂዎች ብዙ ሞተር ሳይክሎችን ሊያካትቱ በሚችሉ በተደራጁ ጉዞዎች ውስጥ ይሳተፋሉ። በእነዚህ ቡድኖች ዙሪያ ለመንዳት ጥሩ ግንኙነት እና ትዕግስት ያስፈልግዎታል። መስመሮችን ለመቀየር ወይም መውጫ ላይ ለመድረስ ከፈለጉ፤ ቀደም ብለው የመታጠፊያ ምልክትዎን ያሳዩ እና በቡድን ያሉት ነጂዎች ቦታ እስኪለቁልዎት ይጠብቁ። በአስተማማኝ ሁኔታ ለማድረግ በቂ ቦታ ሲኖር ብቻ፤ በቡድኖች ወይም በነጂዎች መካከል ይቀላቀሉ። ትንሽ ቡድን ከሆነ፤ መስመሮቹን ከመቀየርዎ በፊት ፍጥነትዎን መቀነስ እና ቡድኑ እንዲያልፍ ማድረግ ቀላል ሊሆን ይችላል።

የሞተር ሳይክል ፈቃድ እየፈለጉ ከሆነ እባክዎ የሞተር ሳይክል አንቀሳቃሽ መመሪያን ይከልሱ። በ MVA ድህረ ገጽ ላይ ሊያገኙት ይችላሉ።

6. ብስክሌቶች

በ Maryland ህግ መሰረት ብስክሌቶች ተሽከርካሪዎች ናቸው። ብስክሌት ነጂዎች መንገዱን እንዲጠቀሙ ይፈቀድላቸዋል እና ሁሉንም የትራፊክ ምልክቶችን መታዘዝ አለባቸው። ነገር ግን ብስክሌት ነጂዎች ለማየት በጣም ከባድ ናቸው፣ ጸጥ ያሉ እና እንደ ሞተር ተሽከርካሪ በዙሪያቸው መከላከያ አጥር የላቸውም። በብስክሌት ነጂዎች አጠገብ በጥንቃቄ ማሽከርከር አለብዎት – ትንሽ ስህተት እንኳን ከባድ የአካል ጉዳት ወይም ሞት ሊያስከትል ይችላል።

በመንገድ ላይ ብስክሌተኞችን ይጠብቁ

ብስክሌተኞችን እንደሚያገኙ መጠበቅ፦

- በሁሉም ዓይነት መንገዶች (በግዛት መካከል መንገዶች፣ እና አውራ ጎዳናዎች፤ እና ድልድዮች እና የክፍያ መተላለፊያ ዋሻዎች በስተቀር)።
- በመስቀለኛ መንገዶች እና በትራፊክ ክበቦች።
- በሁሉም ዓይነት የአየር ሁኔታ ውስጥ።
- በቀን እና በሌሊት ሁል ጊዜ።

ብስክሌተኞች ለደህንነታቸው ሲሉ በጉዞ መስመር ውስጥ (ሞተር ተሽከርካሪዎች ባሉበት) መንዳት ይችላሉ። ይህን የሚያደርጉት መንገዱ ጠባብ ስለሆነ፤ ወይም የመሰናክሎችን ወይም የእግረኛ መንገዶችን አደጋዎች ለማስወገድ ነው። መታጠፍያ በሌላቸው የመንገድ ዳርቻዎች፤ ወይም መኪኖች በቀኝ በኩል በሚቆሙበት ጊዜ፤ ብስክሌት ነጂ ብዙውን ጊዜ በጉዞ መስመሩ መሃል ላይ ሲጋልብ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው። በ Maryland፤ ብስክሌት ነጂ ከትራፊክ ፍጥነት በታች በከፍተኛ ሁኔታ በሚጓዝበት ጊዜም ሙሉውን መስመር ሊጠቀም ይችላል (መስመሩ የሞተር ተሽከርካሪ ብስክሌቱ በመስመሩ ውስጥ እያለ፤ በአስተማማኝ ሁኔታ ለማለፍ በጣም ጠባብ ከሆነ)።

የመኪና በር ከመክፈትዎ በፊት፤ ከኋላ ሆነው ሊመጡ የሚችሉ ብስክሌተኞች መኖራቸውን ያረጋግጡ።

የመንገድ ቅድሚያ መብት

ሞተር ተሽከርካሪ በሚያዞርበት ጊዜ ብስክሌት ነጂዎች የመንገድ ቅድሚያ መብት አላቸው፤ ስለዚህ ለብስክሌት ነጂዎች ቅድሚያ መስጠት አለብዎት።

የብስክሌት መንገድ ወይም የመንገድ ዳርቻ ላይ ሲገቡ ወይም ሲሻገሩ፤ ለብስክሌት ነጂዎች የመንገድ ቅድሚያ መብትን መስጠት አለብዎት።

ብስክሌቶች በእግረኛ መንገድ ላይ ካሉት እግረኞች ጋር ተመሳሳይ መብት አላቸው። ለብስክሌት የመንዳት መብት አለመስጠት ይህም አደጋን የሚያስከትል ከሆነ ቅጣት እና ወይም የእስር ጊዜ እና የመንዳት መዝገብ ላይ ነጥቦችን ያስከትላል።

ብስክሌተኞች በእግረኛ መንገድ ላይ

በመላ ግዛቱ ውስጥ ብስክሌቶች የእግረኛ መንገድ ላይ እንዲንቀሳቀሱ ይፈቀዳል። ለብስክሌተኞች - ብስክሌትዎን በእግረኛ መንገድ ላይ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ፣ እግረኞችን እና በአጋዥ የእንቅስቃሴ መሳሪያዎች የሚታገዙ መንገዶችን የመንቀሳቀስ መብት መጠበቅዎን ያረጋግጡ። የየአካባቢው ሕጎች በእግረኛ መንገድ ላይ ብስክሌቶችን መጠቀምን ሊከለክሉ ስለሚችሉ እባክዎ የአካባቢውን ኮድ እና ህግ አስቀድመው ይመልከቱ።

የብስክሌት አሽከርካሪ ሲከተሉ

ወደ ብስክሌት ነጂው ሲጠጉ፤ ፍጥነትዎን ይቀንሱ። ጥሩምባ (ክላክስ) አያስጬኹባቸው። ብስክሌተኞች ብዙውን ጊዜ እየቀረበ ያለውን ተሽከርካሪ መስማት ይችላሉ እና ከፍተኛ ጬኸት ያስደነግጣቸዋል፤ ይህም አደጋን ያስከትላል።

ብስክሌቶች የማዞሪያ ምልክት ስለሌላቸው ብስክሌት ነጂዎች ምን ለማድረግ እንዳሰቡ ለመንገር የእጅ እና የክንድ ምልክቶችን ይጠቀማሉ።

ብስክሌትን በጣም በቅርበት አይከተሉ። ትናንሽ ቀዳዳዎች፣ መስታወት እና ሌሎች አደጋዎች በተለይ ለብስክሌት ነጂዎች አደገኛ ሊሆኑ እንደሚችሉ ያስታውሱ። ብስክሌቶች ቆመው በፍጥነት ሊንቀሳቀሱ ስለሚችሉ አንድ ብስክሌት ነጂ የሞተር ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ሊያየው የማይችለውን የመንገድ አደጋ ለማስወገድ ሊዞር ወይም ፍጥነት ሊለውጥ ይችላል።

በጥንቃቄ ማለፍ - ቢያንስ 3 ጫማ ለብስክሌቶች ይስጡ

እንደ ማንኛውም በዝግታ የሚጓዝ ተሽከርካሪ ብስክሌት ነጂውን ይለፉ። ፍጥነትዎን ለመቀነስ ይዘጋጁ እና የሚመጣው ትራፊክ ግልጽ እስኪሆን ድረስ ይጠብቁ። ከዚያም በሚያልፉበት ጊዜ በተሽከርካሪዎ እና በብስክሌቱ መካከል፤ ቢያንስ 3 ጫማ ይተዉ። በብስክሌት መንገድ፣ በመንገድ ዳርቻ ላይ ወይም ከመኪናዎ ጋር በተመሳሳይ መስመር ላይ ብስክሌት በሚያልፍበት ጊዜ ይህን ያህል ርቀት ይተዉ። ወደ መስመርዎ ከመመለስዎ በፊት ብስክሌቱን በኋለኛ መመልከቻ መስታወትዎ ላይ ማየትዎን ያረጋግጡ።

በመስቀለኛ መንገድ፣ ድልድይ እና የመኪና መንገድ ላይ ይጠንቀቁ

ሁልጊዜ ብስክሌተኞች መዞራቸውን ካላሳወቁ በቀር በመስቀለኛ መንገድ በኩል በቀጥታ እንደሚሄዱ አስቡ። ለሌላ ማንኛውም ተሽከርካሪ እንደሚያደርጉት ሁሉ ለብስክሌቶችም ቅድሚያ ይስጡ። ብስክሌት ነጂዎች ብዙ ጊዜ በእግረኛ መንገድ እና በዱካዎች ላይ ይጓዛሉ፤ ስለዚህ የእግረኛ መንገድን ወይም ዱካውን ከማቋረጥዎ በፊት ሁለቱንም አቅጣጫ ይመልከቱ።

ያስታውሱ ብስክሌት ካልተጠበቀ አቅጣጫ ሊመጣ ይችላል። እና ልምድ ያላቸው ብስክሌተኞች ብዙ ጊዜ በጣም በፍጥነት (በ 35 ማይል በሰአት ፍጥነት) ይጓዛሉ እና እርስዎ ከሚያስቡት በላይ ቅርብ ሊሆኑ ይችላሉ።

- ብስክሌትን በመንገድ ዳርቻ ወይም በብስክሌት መንገድ ላይ ካለፉ በኋላ ወዲያውኑ ከማለፊያ መስመር ወደ ቀኝ መታጠፍ የለብዎትም። የማለፊያ መስመር ቀጥ ብሎ የሚቀጥል መስመር ነው።
- ወደ ቀኝ ሲታጠፉ በቀኝዎ ወይም በቀኝ ከእይታ ውጪ በሆኑ ቦታዎች ላይ ምንም ብስክሌቶች አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ ይሞክሩ።
- የቀኝ መታጠፊያ ከመጀመርዎ በፊት የብስክሌት መስመር፣ የመንገድ ዳርቻ ወይም ቀኝ መታጠፊያ መስመር ውስጥ በተቻለ መጠን ወደ ቀኝ ይሂዱ።

- በሚታጠፉበት ጊዜ፣፤ልክ እንደሌሎች ተሽከርካሪዎች በቀጥታ ለሚሄዱት ብስክሌቶች ቅድሚያ ይስጡ። በብስክሌት ፊት ወዲያውኑ ወደ ግራ አይታጠፉ።
- ወደ ግራ የሚታጠፍ ተሽከርካሪ ለማለፍ ወደ ቀኝ ከመሄድዎ በፊት ብስክሌቶችን በቅርበት ይመልከቱ።
- በድልድይ፣ በቆሙ መኪኖች ወይም በቀኝ በኩል ባሉ ሌሎች ከለላዎች ምክንያት መንገዱ ሲጠብ፤ ወደ የጉዞ መስመሩ በግራ በኩል ለመቀላቀል በመንገድ ዳርቻ ላይ ለሚጋልብ ብስክሌት ነጂ ይዘጋጁ።

በሌሊት ማሽከርከር

በሌሊት ደብዛዛ አንጸባራቂ ነገር ካዩ ከመንገድ የወጣ ነው ብለው አያስቡ። በጉዞ መስመር ላይ ያለ ብስክሌት ሊሆን ይችላል። የዛፍ ቅርንጫፎች፣ ጉድጓዶች፣ ፍርስራሾች እና የእግረኛ መንገዱን ጠርዝ እንኳን ለማየት አስቸጋሪ ስለሚሆን፤ ብስክሌተኞች አንዳንድ ጊዜ መኪና በሌለበት ምሽት ላይ የመንገድ ዳርቻዎችን ከመጠቀም ይቆጠባሉ። የፊት መብራቶችዎ ብስክሌተኞች በደህና ወደ መንገዱ ዳርቻ እንዲገቡ ሊያስጠነቅቅ ይችላል፤ ነገር ግን በሌሊት ጊዜ ብዙ ጊዜ ይወስዳል። ወደ ብስክሌት በሚጠጉበት ጊዜ ዝቅተኛ ጨረር የፊት መብራቶችን ይጠቀሙ።

ልጆችን ይጠብቁ

በብስክሌት ላይ ያሉ ልጆች አንዳንድ ጊዜ ያልተጠበቁ ናቸው፤ ስለዚህ ያልተጠበቀውን ይጠብቁ። ትንሽ እንደሆኑ እና ለማየት አስቸጋሪ ሊሆኑ እንደሚችሉ ያስታውሱ ። ወጣት ብስክሌተኞች ያለማስጠንቀቂያ አቅጣጫ የመቀየር እድላቸው ሰፊ ነው። ብስክሌተኞች ከመኪና መንገዶች ወይም ከቆሙ መኪኖች አጠገብ ወደ መንገዱ ሲገቡ ይጠንቀቁ። ወጣት ብስክሌተኞችን ለማየት እና በደህና ለመዞር ጊዜ ለማግኘት፤ በትምህርት ቤት እና በመኖሪያ አካባቢዎች የፍጥነት ወሰኖችን ያክብሩ።

7. Mopeds እና Scooters ተሽከርካሪዎች

የሞፔድ እና የሞተር ስኩተር አሽከርካሪዎች ሁሉንም የትራፊክ ህጎች መከተል አለባቸው። የመኪና እና የጭነት መኪና ነጂዎች ምንጊዜም ሞፔዶችን እና ስኩተሮችን በጥንቃቄ መከታተል አለባቸው ምክንያቱም መጠናቸው ለማየት በጣም አስቸጋሪ ያደርገዋል።

ሞፔዶች እና ስኩተሮች በሰዓት 50 ማይል ወይም ከዚያ ባነሰ ከፍተኛ የፍጥነት ወሰን በማንኛውም መንገድ ላይ ሲነዱ ይችላሉ። መሽከርከር የሚችሉት፥

- ጎን ለጎን ወይም ለብቻ።
- በመንገድ ላይ ወይም በመንገድ ዳርቻ ላይ።

ሞፔዶች እና ስኩተሮች በአስተማማኝ ሁኔታ በተቻለ መጠን ከመንገዱ አጠገብ በቀኝ በኩል መነዳት አለባቸው።

በተለይም በመስቀለኛ መንገዶች ላይ በሚዞሩበት ወይም ቀጥ ብለው በሚሄዱበት ጊዜ በሞፔዶች እና ስኩተሮች አካባቢ ይጠንቀቁ። እንዲሁም ለማለፍ ትንሽ ቦታ ባላቸው ጠባብ መንገዶች ላይ ይጠንቀቁ።

8. የተሽከርካሪ ቴክኖሎጂዎችን መረዳት

“የላቁ የአሽከርካሪዎች ድጋፍ ስርዓት” (Advanced Driver Assistance Systems) (ADAS) የተሽከርካሪ ቴክኖሎጂዎች ማሽከርከርን የበለጠ አስተማማኝ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ናቸው። የ ADAS ቴክኖሎጂዎች ህይወትን ለማዳን እና ጉዳቶችን ለመከላከል ይረዳሉ። በአግባቡ ጥቅም ላይ ሲውሉ፤ 40% መጋጨቶችን ይከላከላሉ።

ADAS ቴክኖሎጂ እንደሚከተሉት ባሉ የመንዳት ተግባራት ላይ እርስዎን ለመርዳት ታስቦ የተነደፈ ነው፥

- በእራስዎ መስመር ላይ መቆየት።
- ከእይታ ውጪ ቦታዎችን መቀነስ።
- ከሌሎች ተሽከርካሪዎች ደህንነቱ የተጠበቀ ርቀትን መጠበቅ።
- መጋጨቶችን ማስወገድ።
- የመኪና ማቆሚያ።

ብዙ ተሽከርካሪዎች ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን ለመለየት ቃኚ መሳሪያዎችን እና ካሜራዎችን ይጠቀማሉ። የዚህ አይነት ቴክኖሎጂ ምሳሌዎች አውቶማቲክ የአደጋ ጊዜ ፍሬን፣ በመስመር ላይ የመቆየት እርዳታ እና ከዓይን እይታ ውጪ ማስጠንቀቂያን ያካትታሉ።

ተሽከርካሪዎን ሙሉ በሙሉ ለማንቀሳቀስ በ ADAS ላይ አይተማመኑ። በማንኛውም ጊዜ ለተሽከርካሪዎ ደህንነቱ የተጠበቀ አሠራር ኃላፊነቱን ይወስዳሉ! የተሽከርካሪዎን መስታወቶች እና ካሜራዎች በመጠቀም ትራፊክን በመፈተሽ በዙሪያዎ ያሉትን ሁሉንም ነገሮች ማወቅ የእርስዎ ኃላፊነት ነው።

ይህን ያስተውሉ፥

- ቴክኖሎጂው ውስንነቶች አሉት እና በዝናብ፣ በበረዶ፣ በጭጋግ፣ በኮረብታ ላይ እና በመታጠፍያ አካባቢ ላይ በትክክል ላይሰራ ይችላል።
- ቴክኖሎጂው ከአንድ አይነት ተሽከርካሪ ወደ ሌላ አይነት ግብረመልሶችን ይሰጣል – የዳሽቦርድ ምልክቶች እንኳን ሊለያዩ ይችላሉ፡፡
- ለቴክኖሎጂው ብዙ የተለያዩ ስሞች አሉት፤ እና ስሞቹ ሁልጊዜ ቴክኖሎጂው የሚሰራውን ላይገልጹ ይችላሉ።

ሁልጊዜ፥

- የተሽከርካሪዎን ቃኚ መሳሪያዎች ንፁህ ያድርጉ እና ከጉዳት ነጻ ያድርጉ።
- የሶፍትዌር ቴክኖሎጂውን ወቅታዊ ያድርጉት እና የአምራቹን ምክሮች ይከተሉ።
- ሊያሽከረክሩት በሚፈልጉት ተሽከርካሪ ላይ ያሉትን ቴክኖሎጂዎች በደንብ ይወቁ እና በአስተማማኝ ሁኔታ እና በብቃት ይጠቀሙባቸው። እንዴት እንደሆነ፤ የተሽከርካሪ መመሪያዎን በመከለስ ወይም የመኪናዎን አከፋፋይ በመጠየቅ ይማሩ።

ከሁሉም በላይ፤ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ምንጊዜም ትኩረት ያድርጉ እና ተሽከርካሪዎን ይቆጣጠሩ።

ሊያሽከረክሩት በሚፈልጉት ተሽከርካሪ ላይ ያሉትን ቴክኖሎጂዎች በደንብ ይወቁ እና በአስተማማኝ ሁኔታ እና በብቃት ይጠቀሙባቸው።

ክፍል 8፥ መጋጨቶች እና የትራፊክ ማቆሚያዎች

1. መጋጨቶች

መጋጨቶች ውስጥ ሲሆኑ፤ ሌሎች አሽከርካሪዎችን ለማስጠንቀቅ የአደጋ ጊዜ ብልጭታዎችን ወይም መብራቶችን ያብሩ።

እግረኛ ወይም ብስክሌት ነጂን ጨምሮ አንድ ሰው በተጎዳበት መጋጨት ውስጥ ከተሳተፉ በቦታው መቆየት አለቦት፤ እና፥

- ከፖሊስ፣ ከእሳት እና ከአምቡላንስ እርዳታ ለማግኘት ወዲያውኑ 911 ይደውሉ።
- የተሳተፉትን ሰዎች ቁጥር፣ የጉዳቱን አይነት እና የግጭቱን ቦታ ሪፖርት ያድርጉ።
- ተሽከርካሪዎትን አያንቀሳቅሱ።

ከባድ ጉዳት የሚያስከትል መጋጨት ከተከሰተበት ቦታ ለቀው በመውጣት ከተከሰሱ፤ ከባድ ቅጣት ይደርስብዎታል፥

- ፍቃድዎት ይሰረዛል (ማሽከርከር አይፈቀድልዎትም)።
- እስከ 5 አመት እስር ቤት ሊገቡ፤ እና እስከ 5,000 ዶላር ሊቀጡ ይችላሉ።
- አንድ ሰው የሞተበት የመጋጨት አደጋ ቦታ ትቶ መሄድ ወንጀል ነው። እስከ 10 አመት እስር ቤት እስር ቤት ሊገቡ፤ እና እስከ 10,000 ዶላር ሊቀጡ ይችላሉ።

ጉዳቶች ከሌሉ፤ ነገር ግን ተሽከርካሪዎ መንቀሳቀስ የማይችል ከሆነ፥



- በአፋጣኝ ወደ 911 ይደውሉ፤ አደጋው የደረሰበትን ቦታ እና ምንም አይነት ጉዳት እንደሌለ ሪፖርት ያድርጉ፤ ነገር ግን የፖሊስ እርዳታ ያስፈልግዎታል።
- ታጋሽ ይሁኑ እና መንገዱን ለማቋረጥ ወይም ትራፊክ ለማቆም አይሞክሩ። ከትራፊክ መራቅዎን ያረጋግጡ።

ጉዳቶች ከሌሉ ነገር ግን ተሽከርካሪዎ መንቀሳቀስ የሚችል ከሆነ፥

- መጋጨት ከደረሰበት ቦታ በተቻለ መጠን ሳይርቁ፤ ተሽከርካሪዎን ከመንገድ ላይ ያንሱ። ይህ እርስዎን እና ሌሎችን ለመጠበቅ እና የትራፊክ ክምችቶችን ለመከላከል ይረዳል።
- በመጋጨት ወቅት ከተሳተፉ ሌሎች አሽከርካሪ(ዎች) ጠቃሚ መረጃ ያግኙ። ለሌሎች አሽከርካሪ(ዎች) ተመሳሳይ መረጃ ይስጡ። ይህ የሚያካትተው፡- ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥር፣ የሰሌዳ ቁጥር እና ግዛት፣ የመንጃ ፍቃድ ቁጥር፣ የተሽከርካሪ ስሪት እና ሞዴል እና የኢንሹራንስ መረጃ ነው።
- ምስክሮችን ስማቸውን፣ አድራሻቸውን እና የስልክ ቁጥራቸውን ይጠይቁ።
- የግጭቱ አደጋ ቦታ፣ ቀን እና ሰዓት፣ የተሳተፉት ተሽከርካሪዎች ብዛት፣ የአየር ሁኔታ እና የመንገድ ሁኔታዎችን ያስታውሱ። ከቻሉ፤ ይህንን መረጃ ይጻፉ።
- በተሽከርካሪዎች ላይ የደረሰውን ማንኛውንም ጉዳት ያስታውሱ። ከቻሉ፤ ይህንን መረጃ ይጻፉ፤ እና ፎቶ ያንሱ።
- የመጋጨት አደጋው እንዴት እንደተከሰተ እውነታውን ይፃፉ።

ያስታውሱ፣ በሚከተሉት ጊዜዎች ሁሉ ለፖሊስ መደወል አለብዎት፥

- የሆነ ሰው ሲጎዳ።
- ተሽከርካሪው መንቀሳቀስ ካልቻለ።
- አሽከርካሪው በአልኮል ወይም በአደንዛዥ እፅ ተጽእኖ ስር ያለ ከመሰለዎት።
- አሽከርካሪው ፈቃድ ከሌለው።
- አሽከርካሪው ኢንሹራንስ እና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን ሳይሰጥ ቦታውን ለቆ ለመውጣት ከሞከረ።
- የህዝብ ንብረት ከወደመ።

ያልተጠበቀ ተሽከርካሪን ወይም ሌላ ያልተጠበቀ ንብረትን ቢገጩ፤ የሚከተሉትን ማድረግ አለቦት፥

- ከሚያስፈልገው በላይ ትራፊክን ሳይገድቡ፤ ተሽከርካሪዎን በተቻለ መጠን በቅርበት ያቁሙ።
- የሆነውን ነገር ለመንገር እና መረጃዎን ለመስጠት የተሽከርካሪውን ወይም የንብረቱን ባለቤት ለማግኘት ይሞክሩ።
- የተሽከርካሪውን ወይም የንብረቱን ባለቤት ማግኘት ካልቻሉ በግንኙነት መረጃዎ ላይ ምን እንደተፈጠረ ማስታወሻ ያስቀምጡ። ማስታወሻውን በቀላሉ ማግኘት በሚችሉበት ቦታ ይተዉት።

የቤት እንስሳን በተሽከርካሪዎ ገጭተው ጉዳት ካደረሱ ወዲያውኑ ለፖሊስ መደወል አለብዎት። ውሾች፣ ድመቶች፣ ፈረሶች እና ላሞች የቤት እንስሳት ምሳሌዎች ናቸው።

2. የመንገድ ዳር ድንገተኛ አደጋዎች

ማንኛውም የመንገድ ዳር ድንገተኛ አደጋ የተለየ ነው ስለዚህ ሁልጊዜ ጥንቃቄን እና ምክንያታዊነትን ይጠቀሙ፤ የተነፈሰ ጎማን መቀየር፣ ተሳፋሪን መንከባከብ፣ ወይም ሌላም ነገር ይሁን።

በመንገድ ዳር ድንገተኛ አደጋ ሲከሰት፥

- ሁኔታውን ይገምግሙ።
- እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለብዎት ለመወሰን ጥሩ የማመዛዘን ችሎታ ይጠቀሙ።
- የመንገድ ዳር ድንገተኛ አደጋዎች በቅጽበት ሊለወጡ ስለሚችሉ ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ይጠብቁ።

ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ያግኙ

በየዓመቱ ሰዎች የተሽከርካሪ እርዳታን በመጠባበቅ ላይ እያሉ በመንገድ ዳር ይጎዳሉ ወይም ይሞታሉ። ተሽከርካሪዎ ከተሰናከለ ወደ መንገድ ዳርቻ ለማንቀሳቀስ የተቻለዎትን ሁሉ ያድርጉ። ከመወጣጫ ውጭ ወይም የመኪና ማቆሚያ ቦታ ላይ መድረስ ከቻሉ፤ በተነፈሰ ጎማ በማሽከርከር ወይም ቸርኬ ላይ ጉዳት በማድረስም ቢሆን፤ ያንን ለማድረግ ያስቡበት። ከትራፊክ የበለጠ በራቁ መጠን፤ የበለጠ አስተማማኝ ሁኔታ ላይ ይሆናሉ። መወጣጫ በመንገድ ላይ እያለ፤ ባለ ሶስት ማዕዘን ቅርፅ በተቀቡ ቀጠናዎች ውስጥ በጭራሽ አይቁሙ ወይም አያቁሙ።

በተሽከርካሪዎ ውስጥ መቆየት ከቻሉ፥

በተሽከርካሪዎ ውስጥ መቆየት ከቻሉ፤ ቀበቶ ታጥቀው ፊት ለፊት ይቆዩ። ተሽከርካሪዎ በሌላ ተሽከርካሪ ከተገጨ፤ ተሽከርካሪዎች እርስዎን እና ተሳፋሪዎችን ለመጠበቅ የሚያግዙ በርካታ የደህንነት ሁኔታዎች አሏቸው።

በተሽከርካሪዎ ውስጥ መቆየት ካልቻሉ፥

በተሽከርካሪዎ ውስጥ ለመቆየት አስተማማኝ ካልሆነ ወይም የሚቻል ካልሆነ፤ በአካባቢያ ያለውን ነገር ይመልከቱ እና ሁሉም ሰው የሚወጣበትን ጊዜ ይምረጡ። ከተሽከርካሪው አጠገብ አይቁሙ። ይልቁንም ከመንገድ በፍጥነት ይራቁ። ከግንብ፣ ከትራፊክ መከላከያ ወይም የጥበቃ ሀዲድ ጀርባ ይሁኑ። ከተቻለ፤ ወደ ከፍተኛ ቦታ ይሂዱ። ከሚመጣውን ትራፊክ ትይዩ ይሁኑ፤ እና ተሽከርካሪ ወደ መንገድዎ ቢገባ ንቁ ይሁኑ።

3. የትራፊክ ማቆሚያዎች

የሕግ አስከባሪ መኮንኖች የ Maryland የሞተር ተሽከርካሪ ህግን በመጣስ (በመስበር) ለተከሰሱ ሰዎች የትራፊክ ደረሰኝ (ትኬቶች) በጽሁፍ ይሰጣሉ። ከቆሙ ወይም ሊታሰሩ የሚችሉ ከሆነ የመኮንኑን መመሪያዎች መከተል አለብዎት።

የህግ አስከባሪ መኮንን ሲያስቆምዎ፥

- ከትራፊክ በተቻለ መጠን ወደ መንገዱ ዳር ይውጡ። ብልጭታዎችን ያብሩ።
- ሞተርዎን እና ሬዲዮዎን ያጥፉ።
- ከመኮንኑ ጋር መገናኘት እንዲችሉ መስኮትዎን ወደታች ያውርዱ።
- በተሽከርካሪዎ ውስጥ ሆነው እና የመቀመጫ ቀበቶዎን እንደታጠቁ ይቆዩ።
- እጆችዎን በግልፅ እይታ ላይ ያስቀምጡ – በመሪው ላይ በጣም ጥሩ ነው። መኮንኑ አንድ ነገር እየደበቁ ወይም እያነሱ እንደሆነ እንዲሰማው የሚያደርግ ምንም አይነት እንቅስቃሴ አያድርጉ።
- መኮንኑ ደረሰኝ ከሰጠዎት፤ ስለ ቅጣቱ ከመኮንኑ ጋር አይከራከሩ። ወደ ፍርድ ቤት ከሄዱ ጉዳይዎን ለማቅረብ እድል ይኖርዎታል።

4. የመሻገር ህግ

በ Maryland ውስጥ፣ ማንኛውም ተሽከርካሪዎች በመንገድ በሚቆሙበት፤ መብራት በሚያንጸባርቅበት ጊዜ፤ ወደ ማንኛውም ተሽከርካሪዎች ሲንቀሳቀሱ ተሻግረው መሆን አለብዎት። አስተማማኝ ካልሆነ ወይም ለመሻገር የማይቻል ከሆነ፣ ወደ አስተማማኝ ፍጥነት መቀነስ አለብዎት። ደህንነቱ የተጠበቀ ፍጥነት ሲወስኑ የአየር ሁኔታን፣ የመንገድ ሁኔታን፣ ትራፊክን እና እግረኞችን ግምት ውስጥ ያስገቡ።

ይህንን ደንብ መጣስ የሚከተሉት ቅጣቶች ያሉበት ወንጀል ነው።

- በፈቃድዎ ላይ አንድ ነጥብ እና የ110 ዶላር ቅጣት። MVA ጥሰቶችን ለመከታተል እና ቅጣቶችን ለማውጣት ነጥቦችን ይጠቀማል።
- ጥሰቱ መጋጨትን ካስከተለ የ150 ዶላር ቅጣት እና ሶስት ነጥብ።
- ሞት ወይም ከባድ ጉዳት ከደረሰ 750 ዶላር ቅጣት እና ሶስት ነጥብ።

ነጥቦቹ ወደ ፍቃድዎ መታገድ ወይም መሰረዝ ያመራሉ።

መንገድ የሚያጋራ አሽከርካሪ ይሁኑ

ህይወትን የሚያድን አሽከርካሪ ይሁኑ

የእግረኞች እና የብስክሌት ነጂዎች ደህንነት በ Maryland ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ሰው ይነካል። ብዙ አላስፈላጊ ጉዳቶች እና ሞት የሚከሰቱት አሽከርካሪዎች ወይም እግረኞች ሰክረው፣ የተሽከርካሪ ህጎችን ባለማወቅ ወይም ትኩረት ባለመስጠት ነው። መንገዶች ለሁሉም ሰው ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ መሆን አለባቸው እና ሁላችንም የድርሻችንን መወጣታችን አስፈላጊ ነው። ይህ ደግሞ ብስክሌት ነጂዎችን ይጨምራል። ብዙ ሰዎች ብስክሌቶች በ Maryland መንገዶች ላይ፤ ልክ እንደ መኪኖች ወይም የጭነት መኪናዎች፤ እንደ ተሽከርካሪ እንደሚቆጠሩ አያውቁም። ይህ ማለት አሽከርካሪዎች እና ብስክሌተኞች መንገዱን ለመጋራት መማር እና አንዳቸው ሌላውን ለመጠበቅ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ አለባቸው ማለት ነው።

SHARE THE ROAD Driver ይሁኑ - ፍጥነትዎን ይቀንሱ፣ ትኩረት ይስጡ፣ እና ሁልጊዜ ለእግረኞች እና ለብስክሌት ነጂዎች ንቁ ይሁኑ።



ሁለት ጊዜ የሚመለከት አሽከርካሪ ይሁኑ

ህይወትን የሚያድን አሽከርካሪ ይሁኑ

መኪና ወይም የጭነት መኪና እና ሞተር ሳይክል መካከል የግጭት አደጋ በሚፈጠርበት ጊዜ፤ ሞተር ሳይክል ነጂው ሁል ጊዜ ይሸነፋል። የሞተር ሳይክል አሽከርካሪዎች በመኪና ወይም በጭነት መኪና ውስጥ እንዳሉ ሰዎች በተሽከርካሪው ጥበቃ ስለማይደረግላቸው፤ ሞተር ሳይክል ነጂዎች በ 75 በመቶ በሚሆኑት የግጭት አደጋዎች ይጎዳሉ። አሽከርካሪዎች እና ሞተርሳይክል ነጅዎች መንገዱን በጥንቃቄ የመጋራት ሃላፊነት አለባቸው። በመኪና እና በሞተር ሳይክል መካከል የመጋጨት አደጋ ሲደርስ፤ ከግማሽ በላይ ለሚሆን ጊዜያት፤ ጥፋቱ የመኪናው አሽከርካሪ ነው። LOOK TWICE Driver, ይሁኑ፤ ሁልጊዜ ከመዋሃድ፣ መስመሮችን ከመቀየር እና ወደ ትራፊክ ከመግባት በፊት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ጊዜ ያረጋግጡ።

ለበለጠ መረጃ፤ ይጎብኙ፥
ZeroDeathsMD.gov.

ክፍል 9፥ ሌሎች ገደቦች፣ ጥሰቶች እና ቅጣቶች

1. ገደቦች

ማሽከርከር የተፈቀደ ልዩ መብት መሆኑን፤ እንጂ መብት አለመሆኑን ያስታውሱ። ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ማሽከርከርዎን ለማረጋገጥ MVA በእርስዎ ፈቃድ ላይ ገደቦችን የመጣል ስልጣን አለው። የማሽከርከር ገደብ፤ የመንዳት ልዩ መብቶችዎ ወሰን ነው። ገደቦች፤ ባለዎት የፍቃድ አይነት ላይ፤ ወይም በጣሱት (በተላለፉት) የሞተር ተሽከርካሪ ህጎች ላይ፤ የተመሰረቱ ሊሆኑ ይችላሉ። ገደብ(ዎቹን) በመጣስ መኪና ማሽከርከር ከባድ ወንጀል ነው። የማሽከርከር ልዩ መብቶችዎን ሊያጡ ይችላሉ።

የሚከተሉት የማሽከርከር ገደቦች ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ተመራቂዎች ተፈጻሚ የሚሆኑ ናቸው፥

የመቀመጫ ቀበቶ ገደብ

ጊዜያዊ ፈቃድ ካለዎት ሁልጊዜ የደህንነት ቀበቶ መጠቀም አለብህ። ሁሉም ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶዎችን ወይም የልጅ ደህንነት መቀመጫዎችን መጠቀም አለባቸው።

የተሳፋሪዎች ገደብ

ጊዜያዊ ፍቃድ ካሎት እና ከ18 አመት በታች ከሆኑ፤ በመጀመሪያዎቹ 151 ቀናት ውስጥ እድሜያቸው ከ18 አመት በታች ከሆኑ መንገደኞች ጋር የቅርብ የቤተሰብ አባላት ካልሆኑ በስተቀር ተቆጣጣሪ ሳይኖርዎት ማሽከርከር አይችሉም። ከእርስዎ ጋር ብቁ ተቆጣጣሪ ሹፌር ካሎት ከ18 አመት በታች ከሆነ ተሳፋሪ ጋር መንዳት ይችላሉ። የቅርብ የቤተሰብ አባላት ባለቤትዎን፣ ሴት ልጅዎን፣ ወንድ ልጅዎን፣ የእንጀራ ሴት ልጅዎን፣ የእንጀራ ወንድ ልጅዎን፣ እህትዎን፣ ወንድምዎን፣ የእንጀራ እህትዎን፣ የእንጀራ ወንድምዎን ወይም በአድራሻዎ የሚኖር ማንኛውም ዘመድዎን ሊያካትቱ ይችላሉ። ማን እንደ ተቆጣጣሪ ሹፌር ብቁ እንደሆነ መረጃ ለማግኘት፤ ክፍል 10.B. ይመልከቱ።

የምሽት ገደብ

ጊዜያዊ ፈቃድ ካለዎት፤ ከእኩለ ሌሊት 12:00 እስከ ረፋዱ ጧት 5:00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ያለ ቁጥጥር ማሽከርከር ይፈቀድልዎታል፤ የሚከተሉትን ከሆኑ ብቻ፥

- ወደ ሥራ፣ ከሥራ ወይም በሥራ ጊዜ ማሽከርከር ።
- ወደ ወይም ከ ተደራጀ የበጎ ፈቃድ መርሃ-ግብር ማሽከርከር።
- ወደ ወይም ከ ይፋዊ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ማሽከርከር።
- ወደ ወይም ከ እርስዎ እየተሳተፉበት ወዳለው የአትሌቲክስ ክስተት ወይም ተዛማጅ የስልጠና ክፍለ ጊዜ ማሽከርከር።

የገመድ አልባ መሳሪያ ገደብ

ጊዜያዊ ፈቃድ ወይም የለማጅ ፈቃድ ካለዎት፤ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ምንም አይነት ገመድ አልባ የመገናኛ መሳሪያ (ከእጅ ነፃ የሆነ ስልክን ጨምሮ) መጠቀም አይችሉም። ብቸኛው ልዩነት የ 911 የአደጋ ጊዜ ጥሪ ነው።

2. የመድሃኒት ወይም የአልኮሆል ምርመራ - አስገዳጅ ስምምነት

በ Maryland ውስጥ፤ ለህዝብ ጥቅም በሚውልበት መንገድ ላይ ወይም የግል ንብረት ላይ ሞተር ተሽከርካሪን ሲያሽከረክሩ ወይም ለማሽከርከር ከሞከሩ፤ የአደንዛዥ ዕፅ ወይም የአልኮሆል ምርመራ ለማድረግ ተስማምተዋል (ተቀብለዋል)፤በሕግ አስከባሪ መኮንን ከተጠየቁ። እነዚህ ምርመራዎች በሰውነትዎ ውስጥ ያለውን የአልኮሆል ወይም የመድሃኒት መጠን ይለካሉ።

አንድ የፖሊስ መኮንን በአደንዛዥ እጽ፣ በአልኮል ወይም በቁጥጥር ላይ ባሉ ንጥረ ነገሮች ተጽእኖ ስር ሆነው እያሽከረከሩ እንደሆነ የሚያምኑበት ምክንያት ካላቸው፤ የደም ምርመራ እንዲያቀርቡ የመድኃኒት እውቀና ባለሙያን ሊጠይቁ ይችላሉ። የደምዎ አልኮል መጠን .08 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ ፍቃድዎ ይታገዳል። የሰውነትዎ ስርዓት፤ በመድሃኒት ከተጎዳ MVA ፈቃድዎን ያግዳል።

አንድ የፖሊስ መኮንን ምርመራውን ውድቅ እንዳደረጉ፤ የተረጋገጠ መግለጫ ካቀረበ፣ MVA ፈቃድዎትን ያግዳል።

3. የሐሰት ወይም የተጭበረበረ መታወቂያ ካርድ፣ የመንጃ ፍቃድ ወይም የተማሪ መማሪያ ፍቃድ ማግኘት

የሐሰት መታወቂያ ካርድ፣ የለማጅ ትምህርት ፈቃድ ወይም የመንጃ ፍቃድ ለማግኘት ከሞከሩ፤ በፌደራል እና በግዛት ህግ ሊቀጡ እና/ወይም ወደ ወህኒ ሊወርዱ ይችላሉ።

አልኮል ለመግዛት፣ ለመያዝ ወይም ለማግኘት ስለ እድሜዎ መዋሸት በሕግ የተከለከለ ነው። ከላይ ከተገለጹት ቅጣቶች በተጨማሪ፤ የመንጃ ፍቃድዎ ሊታገድ ይችላል።

4. አስተዳደራዊ እርምጃዎች

የሞተር ተሽከርካሪ ህጎችን ከጣሱ MVA ፍቃድዎን ሊያግድ፣ ሊሽር፣ ሊከለክል ወይም ሊሰርዝ ይችላል። ይህ ከተከሰተ፣ MVA ስለሚከተሉት ነገሮች ለማሳወቅ ማስታወቂያ በፖስታ ይልክልዎታል፥

- ሊወሰድ የታቀደውን እርምጃ።
- እርምጃው እየተወሰደበት ያለው ምክንያት።
- እርምጃው እንዲቀየር ወይም እንዲቆም ማድረግ የሚችሉትን እርምጃዎች።

አብዛኛውን ጊዜ፤ አስተዳደራዊ እርምጃው ለምን መከሰት እንደሌለበት ለማብራራት፤ አስተዳደራዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ።

ፍቃድዎ ከታገደ፣ ከተከለከለ ወይም ከተሰረዘ፤ ፍቃድዎን ለ MVA መስጠት አለብዎት። ያለፈቃድ መንዳት አይፈቀድልዎትም። የእገዳ ወይም የስረዛ ወቅቶች፤ MVA የእርስዎን ፈቃድ ሲቀበል ይጀምራሉ።

የመንጃ ፍቃድ እገዳ

ፈቃድዎ ከታገደ፣ ለጊዜው የሞተር ተሽከርካሪ የመንዳት ልዩ መብት ያጣሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች፤ MVA የተገደበ የመንጃ ፍቃድ ለመስጠት ሊወስን ይችላል። የተገደበ ፈቃድ ለአንድ ዓላማ ብቻ እንዲያሽከረክሩ ይፈቅድልዎታል፤ ለምሳሌ ወደ ሥራ እና ትምህርት ቤት መድረስ እና መምጣት።

የመንጃ ፍቃድ መሻር

የ Maryland መንጃ ፍቃድ መሻር ከመታገድ የበለጠ ከባድ ነው።

ፈቃድዎ ከተሻረ፤ MVA በደህንነት እንደገና ማሽከርከር እንደሚችሉ እስካልወሰነ ድረስ ሞተር ተሽከርካሪን ማሽከርከር አይችሉም። የመንጃ ፍቃድዎ ከተሻረ፤ MVAን ወደነበረበት እንዲመልስልዎ ከመጠየቅዎ በፊት (ይመለስሎታል ማለት ነው) አነስተኛ የጥበቃ ጊዜ አለ። MVA የእርስዎን ጥያቄ ውድቅ ሊያረግ ይችላል።

የመንጃ ፍቃድ መሰረዝ

የመንጃ ፍቃድ መሰረዝ ከመታገድ ወይም ከመሻር የበለጠ ከባድ ነው። ይህ ማለት የመንዳት መብትዎ ተቋርጧል (አልቋል) እና ወደነበረበት አይመለስም ማለት ነው። MVA የሚከተሉትን ከወሰነ የመንጃ ፍቃድዎን ሊሰርዘው ይችላል፥

- ፈቃድ ሊሰጥዎት አይገባም ነበር።
- በእርሶ ፍቃድ ማመልከቻ ላይ አስፈላጊውን ወይም ትክክለኛ መረጃ አላቀረቡም።
- ፈቃድዎን ሲያመለክቱ ወይም ሲያገኙ ማጭበርበር ፈጽመዋል።

ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ፤ ወላጅዎ ወይም ህጋዊ አሳዳጊዎ MVA የመንጃ ፍቃድዎን እንዲሰርዝ ሊጠይቁ ይችላሉ (ክፍል 2.F ይመልከቱ)።

5. ቅጣቶች

ጊዜያዊ ፈቃድ ይዘው፤ በመንቀሳቀስ ጥሰት(ዎች) ከተከሰሱ ወይም “የአመክሮ ጊዜ” (PBJ) ከተሰጥዎት፥

- የአሽከርካሪ ማሻሻያ መርሃ-ግብር ማጠናቀቅ አለቦት፤ እና/ወይም
- የመንጃ ፍቃድዎ ይታገዳል ወይም ይሻራል። እገዳው ወይም ሽረቱ ካለቀ በኋላ፤ በመንጃ ፍቃድዎ ላይ የስራ ቅጥር እና የትምህርት ገደብ ብቻ ይደረጋል።

ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ላይ የሚጣሉ ቅጣቶች

ጊዜያዊ ፈቃድ ይዘው፤ ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ እና በመንቀሳቀስ ጥሰት ወንጀል ከተከሰሱ ወይም የአመክሮ ጊዜ ከተሰጥዎት፣ የሚከተሉት ቅጣቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ፥

- የ መጀመርያ ጥፋት የአሽከርካሪ ማሻሻያ መርሃ-ግብርን እንዲያጠናቅቁ ይጠይቃል።
- ሁለተኛ ጥፋት የመንጃ ፍቃድዎ ለ 30 ቀናት እንዲታገድ እና፤ ለስራ እና ለትምህርት ዓላማዎች ብቻ የሚገድብ፤ የ 90-ቀን የማሽከርከር ገደብ ይጣልቦታል።

- ሶስተኛው ጥፋት ለ180 ቀናት ፍቃድዎ እንዲታገድ እና፣ ለወጣት አሽከርካሪዎች የተዘጋጀ የአሽከርካሪ ማሻሻያ መርሃ-ግብር ላይ እንዲያጠናቅቁ፤ እና ለስራ እና ለትምህርት ዓላማዎች ብቻ የሚገድብ፤ የ 180-ቀን የማሽከርከር ገደብ ይጣልቦታል።
- አራተኛ ወይም ተጨማሪ ጥፋቶች ፈቃድዎ እንዲሰረዝ ያደርጋል። ፈቃድዎን ለማስመለስ ሁሉንም የፍቃድ ፈተናዎች ማለፍ አለብዎት።

የአዋቂዎች ቅጣቶች

ዕድሜዎ 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ፤ እና ጊዜያዊ ፈቃድ ካለዎት እና በመንቀሳቀስ ጥሰት ወንጀል ከተከሰሱ፤ ወይም የአመክሮ ጊዜ ከተሰጥዎት፤ የሚከተሉት ቅጣቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ፥

- የ መጀመርያ ጥፋት የአሽከርካሪ ማሻሻያ መርሃ-ግብርን እንዲያጠናቅቁ ይጠይቃል።
- ሁለተኛ ወንጀል የፈቃድዎን የ30 ቀን እገዳ ያስከትላል።
- ሶስተኛ ወይም ከዚያ በላይ ወንጀሎች እስከ 180 ቀን የሚደርስ እገዳ ወይም ፍቃድ መሻርን ያስከትላል።

እነዚህን ቅጣቶች፤ በፍርድ ቤት ከተከሰሱበት ቅጣት(ዎች) በተጨማሪ ይቀጣሉ። እንዲሁም፤ ከእያንዳንዱ የጥፋተኝነት ውሳኔ ወይም የአመክሮ ጊዜ በኋላ፤ ፈቃድዎን ከማስመለስዎ በፊት አዲስ የ18-ወር ከጥፋተኝነት ነጻ የሆነ ጊዜ መጀመር ይጠበቅብዎታል።

ይህን ያውቁ ኖሯል? ጠጥተው ሲያሽከረክሩ ከተያዙ፣ አልኮል ከተገኘ ተሽከርካሪው እንዳያስነሱ የሚከለክል ትንፋሽ ላይ አልኮል መፈተሻ የመኪና መቆለፊያ መጫን ይኖርብዎታል።

6. የአካል ጉዳተኞች የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን፣ የፍቃድ ሰሌዳዎችን እና የማሳወቂያ ካርዶች አጠቃቀም

የአካል ጉዳተኞች የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን፣ የአካል ጉዳተኞች ታርጋዎችን እና የአካል ጉዳተኞችን የማሳወቂያ ካርዶችን በሕገ-ወጥ መንገድ ከተጠቀሙ ከፍተኛ ቅጣት ሊያገኙ ይችላሉ። ለሚከተሉት ጥሰቶች ደረሰኝ ሊሰጥዎ ይችላል፥

- የአካል ጉዳተኛ ታርጋ ወይም በ MVA የተሰጠ ምልክት ሳይኖሮት፤ እና ተሽከርካሪ ውስጥ ያለው ሰው ለታርጋው ወይም ለማሳወቂያ ካርዱ ብቁ የሆነ አሽከርካሪ ወይም ተሳፋሪ ሳይልሆን፤ የአካል ጉዳተኛ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ላይ ካቆሙ።
- በማንኛውም የተቀረጠ ኩርባ ፊት ለፊት ላይ ወይም ከልለው ከቆሙ፤ (ምንም እንኳን የአካል ጉዳተኛ ታርጋ ወይም የማሳወቂያ ካርድ ቢኖሮትም)።
- ከአካል ጉዳተኛ የመኪና ማቆሚያ አጠገብ፤ በማንኛውም የመተላለፊያ መንገድ ላይ መኪና ማቆም (የአካል ጉዳተኛ ታርጋ ወይም የማሳወቂያ ካርድ ቢኖርዎትም) ። የመተላለፊያ መንገድ በተሽከርካሪ ወንበሮች ወይም ሌሎች ተንቀሳቃሽ መሳሪያዎች ውስጥ ያሉ ሰዎች ከተሽከርካሪያቸው ለመውጣት እና ለመግባት የሚጠቀሙበት ቦታ ነው።
- ጉዳተኝነት የማሳወቂያ ካርድን፤ ጊዜው ካለፈበት በኋላ መጠቀም።
- የአካል ጉዳተኛው ሳይገኝ እና ትክክለኛ መለያ ሳይደረግበት፤ የአካል ጉዳተኛ ታርጋ ወይም የማሳወቂያ ካርድ በመጠቀም።
- ለአካል ጉዳተኛ ታርጋ ወይም የማሳወቂያ ካርድ ሲያመለክቱ፤ ማንኛውም አይነት ማጭበርበር ወይም የተሳሳተ መረጃ።

ስለ የአካል ጉዳተኞት መኪና ማቆሚያ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ወደ MVA ድህረ ገጽ ይሂዱ።

ክፍል 10: ሌላ ጠቃሚ መረጃ

1. ለ MVA ሪፖርት ለማድረግ የሕክምና ሁኔታዎች

ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ውስጥ አንድ ወይም ብዙ የጤና ሁኔታዎች ካሉዎት፤ የመንጃ ፍቃድዎን ሲያመለክቱ ወይም ሲያሳድሱ፤ ለ MVA ማሳወቅ አለብዎት። ሁኔታው የታወቀው፤ ፈቃድዎ መውሰድዎ በኋላ ከሆነ፤ እንተመረመሩ ለ MVA ያሳውቁ። የመንዳት ችሎታዎ ላይ ተጽእኖት በሚያደርጉ ከሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ካለብዎት፤ በ MVA የአሽከርካሪ የጤና እና ደህንነት ክፍል፤ እና/ወይም በህክምና አማካሪ ቦርድ ለፈቃድ መጽደቅ አለቦት፥

- ባለፉት 6 ወራት ውስጥ ከሌላ ሰው እርዳታ ያስፈልገው፤ ዝቅተኛ የደም ስኳር ቅጽበትን ያስከተለ የስኳር በሽታ።
- የሚጥል በሽታ ወይም የሚያንቀጠቅጥ በሽታ።
- ባለፉት 6 ወራት ውስጥ የንቃተ ህሊና መሳት ያስከተለ የልብ ህመም።
- ስትሮክ።
- የማዞር ስሜት፣ ራስን መሳት ወይም ከንቃት መቋረጥ እንዲፈጠር የሚያደርግ ሁኔታ።
- የእንቅልፍ ማጣት ወይም ናርኮሌፕሲ(narcolepsy)።
- የአሰቃቂ የአንጎል ጉዳት ታሪክ (TBI)።
- የማሽከርከር ችሎታዎን ሊጎዳ የሚችል፤ በእጆችዎ፣ በእግሮችዎ፣ ወይም በመርገጫዎችዎ ላይ የሚታይ፤ የድካም፣ የመንቀጥቀጥ፣ ወይም የዝለት/የመደንዘዝ ሁኔታ።
- የማሽከርከር ችሎታዎን ሊጎዳ የሚችል፤ እጅ፣ ክንድ፣ መርገጫ ወይም እግር የሌሎት፣ የተቆረጠ፣ ወይም መስራት የማይችል ከሆነ::
- ቢያንስ በአንድ አይን የተስተካከለ ዝቅተኛ የ 20/70 የአይን እይታ፤ ወይም ቢያንስ በ 110 ዲግሪ የባይኖኩላር መስክ ላይ የተስተካከለ፤ የአይን እይታን የሚያውክ የአይን ችግር።
- የአልኮል አጠቃቀም ችግር::
- የመድሃኒት አጠቃቀም ችግሮች::
- የማሽከርከር ችሎታዎን ሊጎዳ የሚችል የአእምሮ ጤና ሁኔታ።
- የአይምሮ ህመም (Schizophrenia)።
- የመርሳት በሽታ።

2. ተቆጣጣሪ ሹፌር - መስፈርቶች እና ኃላፊነቶች

የ Maryland የለማጅ ፍቃድ ካሎት በተማሪዎ ፍቃድ ላይ የተገለጹትን ተሽከርካሪዎች ወይም የተሽከርካሪዎች ክፍል ብቻ ማሽከርከር ይችላሉ። ከእርስዎ ጋር ተቆጣጣሪ ሹፌር ሊኖርዎት ይገባል። ተቆጣጣሪ ሹፌር:-

- ቢያንስ 21 ዓመት የሆነ።
- በአሁኑ ጊዜ በ Maryland ወይም በሌላ ግዛት ውስጥ፤ እርስዎ እያሽከረከሩ ያሉትን ተመሳሳይ ተሽከርካሪዎች መደብ ለማሽከርከር፤ ቢያንስ ለሶስት ዓመታት ፈቃድ ያለው።
- ተሽከርካሪው ሞተር ሳይክል ካልሆነ በስተቀር፤ ከጎንዎ ይቀመጣሉ።

3. የአካል ክፍሎች ለጋሽ

የ Maryland ነዋሪዎች ከሞቱ በኋላ የአካል ክፍሎችን ወይም ሕብረ ሕዋሳትን በመለገስ የህይወት እና የጤና ስጦታ ለሌላ ሰው መስጠት ይችላሉ።

- እድሜው 18 ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ማንኛውም ሰው የአካል ለጋሽ ሊሆን ይችላል።
- ወላጅ ወይም አሳዳጊ በጽሑፍ ስምምነት (ከተስማሙ)፤ ቢያንስ 16 ዓመት የሆናቸው ልጆች የአካል ለጋሾች ሊሆኑ ይችላሉ።

እባክዎ በፍቃድ ማመልከቻዎ ወይም በእድሳት ማሳወቂያዎ ላይ የሚከተለውን መግለጫ ይመልከቱ፥

“እባክዎ ሲሞቱ የአካል ለጋሽ በመሆን ሌሎችን መርዳት እንደሚፈልጉ ያረጋግጡ። “አዎ” ላይ ምልክት በማድረግ ሁሉንም አስፈላጊ የግል መረጃዎች፤ ወደ Maryland የጤና መምሪያ እንዲተላለፋ እና በ Maryland የአካል ለጋሽ መዝገብ ውስጥ እንዲቆዩ ፈቃድ ይሰጣሉ።” ከተስማሙ፤ ፈቃድዎ የአካል ለጋሽ መሆንዎን እንዲያመለክት መምረጥ ይችላሉ።

ስለ አካል ልገሳ መርሃ-ግብር ተጨማሪ መረጃ በ MVA ድህረ ገጽ ላይ ይገኛል።

4. ድምጽ ለመስጠት ይመዝገቡ

የ1993 ብሔራዊ የመራጮች ምዝገባ ህግ፤ ብዙ ጊዜ “የሞተር መራጭ” ተብሎ የሚጠራው የፌደራል ህግ ነው። ብቁ የሆኑ ደንበኞች የመንጃ ፍቃድ ወይም የፎቶ መታወቂያ (መታወቂያ) ካርድ ሲያገኙ፤ ድምጽ ለመስጠት እንዲመዘገቡ፤ ወይም የድምጽ አሰጣጥ መረጃን እንዲከታተሉ፤ MVA ይፈልጋል።

5. የኢንሹራንስ መስፈርቶች

በ Maryland ውስጥ የተመዘገቡ ሁሉም የሞተር ተሽከርካሪዎች፤ በ Maryland ውስጥ ፈቃድ ባለው ወኪል ድርጅት መድን ማግኘት አለባቸው። የሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት ከሆኑ፣ ለግል ጉዳት እና ለንብረት ውድመት ተጠያቂነት፤ በሕግ በሚፈለገው መጠን መድህን ሊገቡለት ይገባል። ስለእነዚህ መጠኖች መረጃ ለማግኘት የ MVA ድህረ ገጽን ይመልከቱ።

ሞተር ተሽከርካሪ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ሁል ጊዜ የሚሰራ የመድህን መታወቂያ ካርድ ከእርስዎ ጋር ሊኖርዎት ይገባል። ይህ ካርድ በኤሌክትሮኒክ መልክ ሊሆን ይችላል። የሕግ አስከባሪ መኮንን የመድህን ካርድዎን ከጠየቁ፤ ለእነሱ ማሳየት አለብዎት። እምቢ ካሉ፤ ሊቀጡ ይችላሉ።

6. የመቀመጫ ቀበቶ ህግ



በህጉ መሰረት፤ የሞተር ተሽከርካሪ አሽከርካሪ እና ሁሉም ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ መታጠቅ ወይም በህጻን ደህንነት መቀመጫ ላይ መታሰር አለባቸው።

7. የልጆች ደህንነት መቀመጫዎች

ሁሉም ከ 8 አመት በታች የሆኑ ህጻናት ህፃኑ 4’9” ወይም ከዚያ በላይ ካልሆነ በስተቀር፤ በልጆች የደህንነት መቀመጫ ላይ መቀመጥ አለባቸው። ዕድሜያቸው ከ 2 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች በአምራቹ የተገለጸውን ቁመት ወይም ክብደት እስኪደርሱ ድረስ፤ የፌዴራል መመሪያዎችን በሚያሟሉ ከኋላ በሚቀመጡ የልጅ ደህንነት መቀመጫ መቀመጥ አለባቸው። በልጅዎ የደህንነት መቀመጫ እና በተሽከርካሪዎ አምራች፤ የቀረበውን ሁሉንም መመሪያዎች መከተል አለብዎት።

የልጆች ደህንነት መቀመጫዎች፤ የመኪና መቀመጫዎች እና ሌሎች በፌዴራል ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው የልጅ ደህንነት መሳሪያዎችን ያካትታሉ።

የልጅ ደህንነት መቀመጫ መግዛት ወይም ማግኘት ካልቻሉ፤ እባክዎን Kids In Safety Seats (KISS) ን፤ ከ Maryland የጤና መምሪያ በ800-370-SEAT ያግኙ። KISS በግዛቱ የተለያዩ አካባቢዎች የመኪና መቀመጫዎችን ወይም መቀመጫዎችን መግዛት ለማይችሉ ቤተሰቦች በዝቅተኛ ወጪ የኪራይ መርሃ-ግብሮችን ያስተባብራል። መቀመጫዎች በሁሉም ቦታ በማንኛውም ጊዜ ላይ፤ ላይገኙ ይችላሉ።

8. የአየር ቦርሳዎች

የአየር ቦርሳዎች በአደጋ ጊዜ እርስዎን የሚከላከሉ አስፈላጊ የደህንነት መሳሪያዎች ናቸው። ለበለጠ ጥበቃ፥

- በተሽከርካሪዎ የጭን እና የትከሻ ቀበቶዎች ጋር ይጠቀሙባቸው።
- በተቻለ መጠን ከመሪው ራቅ ብለው ይቀመጡ። በመሪው እና በደረትዎ መካከል ከ10-12 ኢንች ርቀት እንዲኖር ይምከሩ።
- ነፍሰ ጡር ሴቶች የመቀመጫ ቀበቶውን የጭን ክፍል ከሆድ በታች፤ በተቻለ መጠን ዳሌ ላይ እና የላይኛው ጭን ላይ መታጠቅ አለባቸው። የትከሻ ቀበቶውን በሆድ ዙሪያ መታጠቅ አለባቸው።
- ከኋላ ያለው የመኪና ወንበር ላይ፤ ፊታቸውን ወደ መቀመጫው አዙረው የሚቀመጡ ልጆች፤ የተሳፋሪ አየር ቦርሳ ባለው የተሽከርካሪ የፊት ወንበር ፊት ለፊት በፍጹም መቀመጥ የለባቸውም።
- ዕድሜያቸው ከ13 ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት በህጻን ደህንነት መቀመጫ ውስጥ ወይም በመቀመጫ ቀበቶ ውስጥ ከኋላ ወንበር ታጥቀው መቀመጥ አለባቸው።

9. ፍሬን በፀረ- መቆለፊያ የፍሬን ሲስተም (Braking with Anti-lock Braking System) (ABS)

ፀረ-መቆለፊያ የፍሬን ሲስተም (ABS) መኪናዎን መቆጣጠር እንዲችሉ ጎማዎችዎ እንዳይቆለፉ ያግዛል። የተሽከርካሪዎ ኮምፒዩተር አንድ ወይም ከዚያ በላይ ጎማዎች መቆለፋቸውን ባወቀ ጊዜ፤ ABS እንዳይቆለፉ ብሬክን በፍጥነት መንካት ይጀምራል። ABS በስራ ላይ ሲሆን፣ ከፍሬን ድምፅ ሊሰሙ ይችላሉ፤ እና የፍሬን መርገጫው ከእግርዎ በታች ይንቀጠቀጣል። ስለ ABS ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የተሽከርካሪዎን የባለቤት መመሪያ ይመልከቱ።

10. የጆሮ ማዳመጫዎችን ማድረግ የተከለከለ ነው

በሁለቱም ጆሮዎች የጆሮ ማዳመጫዎች በማድረግ ማሽከርከር አይችሉም። የመስሚያ መርጃ መሳሪያዎች ተፈቅደዋል።

11. ትይዩ የመኪና ማቆሚያ

የማሽከርከር ፈተና ሲወስዱ ትይዩ ማቆሚያ አያስፈልግም። ሆኖም፤ ስለእሱ በ MVA የመንዳት ትምህርት ኮርስ ውስጥ ይማራሉ ። ፈቃድ ለማግኘት በሚወስዱት የማሽከርከር ኮርስ ፈተና ወቅት፤ የ “ተገላቢጦሽ ባለ ሁለት ነጥብ መዞሪያ” እንዳደረጉት፤ ለትይዩ የመኪና ማቆሚያ የሚያስፈልጉ ተመሳሳይ ክህሎቶች ተሸፍነዋል፡፡ ይህ የሚያጠቃልለው፡-

የአይታ ችሎታዎች፣ የርቀት ግምት፣ የመስታወት እና የመዞሪያ ምልክቶች፣ የመሪ ፣ የፍሬን እና የፍጥነት መቆጣጠሪያ አጠቃቀም።

12. ወደፊት የሚያስገባ የመኪና ማቆሚያ፣ ወደ ኋላ የሚያስገባ የመኪና ማቆሚያ እና ባለ ሶስት ነጥብ መታጠፊያ

በማሽከርከር ፈተናዎ ጊዜ ወደፊት የሚያስገባ የመኪና ማቆሚያ፣፣ ወደ ኋላ የሚያስገባ የመኪና ማቆሚያ እና ባለ ሶስት ነጥብ መታጠፊያ በተሳካ ሁኔታ ማከናወን መቻል አለብዎት። በፈተና ወቅት፤ የመኪና ማቆሚያው ባለ 10’ በ 20’ ቦታ ላይ ይከናወናል፤ እና መዞሪያው ባለ 16’ በ 20’ ቦታ ነው። እነዚህ እንቅስቃሴዎች ምን ያህል በጥሩ ሁኔታ፤ ርቀትን እንደሚገምቱ፣ መስተዋቶችን እና መዞሪያ ምልክቶችን እንደሚጠቀሙ፣ መሪ እንደሚያሽከረክሩ፣ ፍሬን እንደሚይዙ እና ተሽከርካሪዎን እንደሚቆጣጠሩ ያሳያሉ። እንዲሁም፤ የእርስዎን የአይታ፣ ወደኋላ የመመለስ እና አጠቃላይ የመንዳት ችሎታዎን ይፈትሻሉ።

13. የብስክሌት ነጂዎች ህጎች እና ምክሮች

እንደ ሞተር ተሽከርካሪ አሽከርካሪዎች፤ ብስክሌተኞች መንገዱን በደህንነት የመጠቀም መብት እና ግዴታዎች አሏቸው። አስተማማኝ እና ሰውን አክባሪ ብስክሌት ነጂ በመሆን የድርሻዎን ይወጡ።

የመንገድ ህጎችን ያክብሩ፥ ሲገመት በሚችል መልኩ በቀጥታ እና በነጠላ መንገድ ያሽከርክሩ። ከትራፊክ ጋር እና ክፍት የመኪና በሮች ለመጋፈጥ፤ አስቀድመው እቅድ በማውጣት፤ እና የመንገድ አደጋዎችን ለማለፍ ጊዜ ይስጡ፡፡ ለእግረኞች ቅድሚያ ይስጡ እና ሁሉንም የትራፊክ ምልክቶችን ያክብሩ።

በትራፊክ ማሽከርከር፥ ሁልጊዜ በቀኝ በኩል ይጋልቡ። እግረኞችን እና ብስክሌቶችን በቀኝ በኩል በሚያልፉበት ጊዜ ይጠንቀቁ። ወደ መስቀለኛ መንገድ ሲመጡ በሚሄዱበት አቅጣጫ (በግራ፣ ቀጥ፣ ቀኝ) ተገቢውን መስመር ይጠቀሙ።

በሁሉም መዞሪያዎች ምልክት ያሳዩ፥ መስመሮችን ከመቀየርዎ ወይም ከመታጠፍዎ በፊት ወደኋላ ይመልከቱ። ምን ለማድረግ እንዳሰቡ ለሌሎች ለማሳወቅ የእርስዎን የመዞሪያ ምልክቶች ይጠቀሙ፥



በግራ እጆች በጥንቃቄ ይታጠፉ፥

- በጉዞ መስመሩ በግራ በኩል (ወይም በግራ መታጠፊያ መስመር) በመንቀሳቀስ እንደ ሞተር ተሽከርካሪዎች ወደ ግራ መታጠፍ፤ ወይም
- በማቆም፤ ከብስክሌትዎ በመውረድ እና የእግረኛ መንገድ ላይ በመሄድ እንደ እግረኛ ይሻገሩ።

ለሚያንሸራትቱ የመንገድ ሁኔታዎች ተዘጋጁ፥

በዝናብ ወይም በበረዶ ውስጥ ፍሬን በሚይዙበት ጊዜ፤ ለመቆም ተጨማሪ ርቀት ይፍቀዱ፤ እና የእግረኛ መንገድ ምልክቶችን እና የመገልገያ ሽፋኖችን ይፈልጉ፣ ይህም የሚያዳልጥ ሊሆን ይችላል።

የሚታዩ ይሁኑ - በምሽት መብራቶችን ይጠቀሙ፥

በምሽት በሚነዱበት ጊዜ፤ የ Maryland ግዛት ህግ በብስክሌትዎ ላይ ነጭ የፊት ለፊት መብራት እና ከኋላ ቀይ አንጸባራቂ እንዲኖር ያስገድዳል። ቢያንስ ከ600 ጫማ ርቀት ሆነው መታየት አለባቸው። በተጨማሪም፤ በቀን ውስጥ ብሩህ አለባበሶችን እና ለምሽት ጉዞ የሚያንፀባርቁ ልብሶችን እንዲለብሱ ይመከራል።

የብስክሌት መሳሪያዎች፥

የጭንቅላት መከላከያ፤ እድሜያቸው ከ16 ዓመት በታች ለሆኑ ሁሉ ብስክሌት ለመንዳት ያስፈልጋል። ይህ ብስክሌቱን የማይዘውሩ ተሳፋሪዎችንም ይጨምራል። የጭንቅላት መከላከያ፤ በሁሉም ዕድሜ ላሉ ሰዎች በጥብቅ ይመከራል።

በህጉ መሰረት ሁሉም ብስክሌቶች የሚከተሉትን ሊኖራቸው ይገባል፥

- ብስክሌቱ በሰዓት 10 ኪሎ ሜትር በደረቀ፣ በተስተካከለ፣ በንጹህ መንገድ ላይ በሚሄድበት ጊዜ በ15 ሜትር ውስጥ ሊያስቆመው የሚችል ፍሬን።
- ሌሊት ወይም በዝቅተኛ ብርሃን ሲነዱ፤ ከ 500 ጫማ ርቀት ላይ ሊታዩ የሚችሉ ነጭ የጨረር የፊት መብራቶች እና በ 600 ጫማ ርቀት ላይ ሊታዩ የሚችሉ ቀይ የኋላ መብራቶች።
- ከትንሽ ልጅ ጋር የሚጓዙ ከሆነ፤ በብስክሌት ላይ በጥብቅ የታሰረ፤ የደህንነት መቀመጫ ወይም ተጎታች ።
- ትንንሽ እቃዎችን ሲይዙ፤ ሁለቱም እጆች በእጅ መያዣው ላይ እንዲቆዩ፤ የቢስክሌት ቅርጫት፣ መደርደሪያ ወይም ቦርሳ።

14. ዝቅተኛ ፍጥነት ያላቸው የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች (ፍቺዎች)

የኤሌክትሪክ ብስክሌቶች

- በኤሌክትሪክ ሞተር እርዳታ በሰው ኃይል ይንቀሳቀሳሉ።
- ሙሉ በሙሉ የሚሰሩ ፔዳሎች ይኑርዎት።
- ሁለት ወይም ሶስት ጎማዎች ይኑርዎት።
- 750 ዋት ወይም ያነሰ ደረጃ ያለው ኤሌክትሪክ ሞተር ይኑርዎት።

የኤሌክትሪክ ብስክሌቶች ዓይነቶች

ክፍል 1፡ ብስክሌት ጋላቢው ፔዳሎችን በሚያሽከረክርበት ጊዜ እርዳታ የሚሰጥ፤ እና ብስክሌቱ በሰዓት 20 ማይል በሚደርስ ፍጥነት በሚደርስበት ጊዜ እርዳታ መስጠቱን የሚያቆም፤ ሞተር ይኑርዎ።

ክፍል 2፣ ብስክሌት ጋላቢው ፔዳሎችን ቢያሽከረክርም ባያሽከረክርም እርዳታ የሚሰጥ፤ እና ብስክሌቱ በሰዓት 20 ማይል በሚደርስ ፍጥነት በሚደርስበት ጊዜ እርዳታ መስጠቱን የሚያቆም፤ ሞተር ይኑርዎ።

ክፍል 3፣ ብስክሌት ጋላቢው ፔዳሎችን በሚያሽከረክርበት ጊዜ እርዳታ የሚሰጥ፤ እና ብስክሌቱ በሰዓት 28 ማይል በሚደርስ ፍጥነት በሚደርስበት ጊዜ እርዳታ መስጠቱን የሚያቆም፤ ሞተር ይኑርዎ።

ዝቅተኛ-ፍጥነት የኤሌክትሪክ ስኩተሮች

- አሽከርካሪውን ብቻ ለማጓጓዝ የተሰሩ ናቸው።
- ከ100 ፓውንድ በታች ይመዝናሉ።
- የፊት እና የኋላ ጎማ በትይዩ መስመር ላይ፤ ወይም አንድ ጎማ ከፊት እና ሁለት ከኋላ ይኑርዎት።
- አሽከርካሪው የሚይዘው እጀታ እና የሚቆምበት መርገጫ ይኑርዎት።

ያስታውሱ፤ ያለ ተሽከርካሪ መድህን ማሽከርከር በህግ የተከለከለ ነው! በሁሉም ተሽከርካሪዎች ላይ መድህን ካላስቀመጡ፣ በየአመቱ ለአንድ ተሽከርካሪ እስከ 2,500 ዶላር ይቀጣሉ።

- የሚንቀሳቀሱት በኤሌክትሪክ ሞተር እና በሰው ኃይል ነው።
- በሰዓት እስከ 20 ማይል ፍጥነት መስራት ይችላል።

ማስታወሻ፥ ዝቅተኛ ፍጥነት ያለው የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የሚጠቀሙ ከሆነ ሌሎች የአካባቢ ገደቦች እንዳሉ ያረጋግጡ።